# "ኢሕአዴግ ዘምሟል"

## መግለጫዎቹ የገለጡት እውነት

### እንዳርጋቸው ተናግሯል፤ ግን በመጠኑ አደናግሮናል

ጌታቸው ስሜ (ኢንግላንድ)

### በወቅታዊ ጡዘቶች የተናጠች ሃገር

ፍቅርተ ተሾመ




መለያችን ኢትዮጵያዊነታችን!

# ግዮን

በየሳምንቱ ቅዳሜ

ግዮን ቅጽ 1 ቁጥር 65 ሐምሌ 2011 ዓ.ም

ዋጋ 14.99


## "እንደ ሀገር የመጨረሻው ቁስል ላይ ደርሰናል"

የሰብአዊ መብት ተሟጋቹ አቶ ኦባንግ ሜቶ

# በኢጄቶ የምትናጠው ሲዳማና የሐዋሳው ግጭት!


















# “እንደ ሀገር የመጨረሻው ቁስል ላይ ደርሰናል”

የሰብኣዊ መብት ተሟጋቹ

## አቶ ኦባንግ ሚቶ




ቁጥር 64 ዕትም

ግዮን

ቀጣይ ዕትም
ቅዳሜ ሐምሌ 20
ይጠብቁን!

የአምለሰት ሙጬ “ምን አለሽ” ፊልም ተመረቀ!
.... 2 ....

በኢጀቶ የምትናጠው ሲዳማና የሐዋሳው ግጭት!
.... 3 ....

“ጭር ሲል አልወድም” የሕወሓትና የአዴፓ ሰሞነኛ ውዝግብ!
.... 4 ....

“ኢሕአዴግ ዘምሟል”
መግለጫዎቹ የገለጡት እውነት
መሳክ ቢ.
.... 6 ....

ኢትዮጵያዊነት በዘመናት ተላውጦ
ኄናክ ገስታው
.... 11 ....

ቅምሻ
.... 13 ....

አንዳርጋቸው ተናግሯል፤ ግን በመጠኑ አደናግሮናል
ጌታቸው ስሜ (ኢንግላንድ)
.... 14 ....

“ኢትዮጵያ ወይም ሞት!”
ተሾመ ሺፈራው
.... 16 ....

አራት ቢሊዮን ችግኝ”
ቅዠት ወይስ ሌላ?
መታሰቢያ መልአከ ሕይወት
.... 18 ....

የአበራሽን ጠባሳ ያየ በእሳት አይጫወትም!
ኢዮብ ሳሰሞት
.... 19 ....

በወቅታዊ ጡዘቶች የተናጠች ሃገር
ፍቅርተ ተሾመ
.... 20 ....



“አወዛጋቢው” ዕጩ ፕሬዚዳንት ማናቸው?
.... 23 ....

ዜና

# የአምለሰት ሙጩ “ምን አለሽ” ፊልም ተመረቀ!




የድምጻዊ ቴዲ አፍሮ ባለቤትና ሞዴልና አክትረስ አምለሰት ሙጩ ለዓመታት ስትደክምበት የቆየችውን “ምን አለሽ” የተሰኘ አዲስ ፊልም በብሔራዊ ቴአትር አዳራሽ አስመረቀች፡፡

አምለሰት ሙጩ የጻፈችውና ፕሮዲዩስ ያደረገችውን፣ እንዲሁም በመሪ ተዋናይነት የተሳተፈችበት አዲስ ፊልሟን ባለፈው ሰኞ ሐምሌ 8 ቀን 2011 ዓ.ም ባስመረቀችበት ወቅት፤ የክብር እንግዳዋ እንዲሆን ያሰበችው ባለቤቷ ድምፃዊ ቴዎድሮስ ካሳሁን (ቴዲ አፍሮ) ከአገር ውጪ በመሆኑ መገኘት ባይችልም፤ የመልካም ምኞት መልዕክቱን ግን አስተላልፏል፡፡

በድህነት ውስጥ የምትዳክር ምስኪን የመርካቶ ሸንኮራ ቸርቻሪ ሆና፣ የኑሮን አስቸጋሪ መሰናክል ለማለፍ ብዙ ፈተናዎችን የምትጋፈጥ አንዲት ጠንካራ ሴት፤ ከነበረችበት ህይወት ወጥታ እንዴት በዓለም ሁሉ ስሟ የሚጠራ ታዋቂ አትሌት መሆን እንደቻለች የሚተርከውና እጅግ መሳጭ በሆነ የሲኒማ ቴክኒክ የሚታይበት አዲሱ የአምለሰት “ምን አለሽ” ፊልም ተሰርቶ ለመጠናቀቅ ረጅም ዓመታትን መውሰዱ ሲታወቅ፤ የሲኒማቶግራፊ ስራውን ያካሄዱት ከሆሊውድ የመጡ የውጭ ሀገር ባለሙያዎች እንደሆኑ ለመረዳት ተችሏል፡፡

የመርካቶ ሸንኮርት ነጋዴዋን ጎስቋላ ሴት ገጸባህሪ ለመላበስ እንዲያግዛ ብላ በወቅቱ የተከተለችው ራሷን በዚያች ሴት አምሳያ የመወከል ጥረቷ፤ ለከፋ ድንገተኛ ህመም ዳርጓት በአስቸኳይ ወደ ኬኒያ ሄዳ እስከመታከም የተገደደችበት አጋጣሚ መፈጠሩን ከውስጥ አዋቂ ምንጮች ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህ መስዋዕትነት የከፈለችበት ፊልም ተሰርቶ እስኪጠናቀቅ በሚሊዮኖች የሚቆጠር የገንዘብ ወጪ መጠየቁም ተሠምቷል፡፡

በምረቃ ፕሮግራሙ ላይ የመልካም ምኞት መልዕክቱን ያስተላለፈው ድምፃዊ ቴዲ አፍሮ በፕሮግራሙ ለተገኙት ሁሉ “የከበረ ሰላምታዬ ይድረሳችሁ” በማለት ሰላምታ አቅርቦ “ውዷ ባለቤቴ አምለሰት ሙጩ ለረጅም ጊዜ የደከምሽበት የፊልም ስራ ተጠናቆ ፍሬውን ለማየት ስላበቃሽ እንኳን ደስ ያለሽ” የሚል መልዕክት አስተላልፏል፡፡ ከዚሁ ጋር በማያያዝም “ በስራ አጋጣሚ በቦታው ባልገኝም የምርቃት ስነ ስርዓቱ ያማረ እንዲሆን ከፍተኛ ጥረት ላደረጋችሁ እና በምረቃ በዓሉ ላይ ለተገኛችሁ ታደሚዎች፣ ጥሪ የተደረገላችሁ ክቡራን እንግዶች ከፍ ያለ ምስጋናዬን ለማቅረብ እወዳለሁ” ብሏል፡፡

ከሁለት ልጆቿ ጋር በቀይ ካባ ተውባ ፊልሟን ያስመረቀችው አምለሰት ሙጩ ለእለቱ ታዳሚያንና አብረዋት ለደከሙ ሁሉ ልባዊ ምስጋናዋን አቅርባ ለፊልሙ የከፈለችውን ዋጋም በአጭሩ ተናግራለች፡፡

## ሜሪጆይ «የ25 ዓመት የበጎ ሥራ ዓመታት እና የነገ ብሩህ ተስፋ » በሚል የምክክር መድረክ አዘጋጀ

ሜሪጆይ የልማት ማህበር በኤሊያና ሆቴል ሐምሌ 11 ቀን 2011 ዓ.ም ፍቃድ ያገኘበትን 25ኛ ዓመት የብር ኢዮቤልዩ በዓልን አስመልክቶ ከጋዜጠኞች ጋር ምክክር አድርጓል፡፡ ጋዜጣዊ መግለጫም ሰጥቷል፡፡

በመክፈቻው የሜሪጆይ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሲስተር ዘቢደር ዘውዴ የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክት ለእንግዶች በማስተላለፍ ለዚህ ቀን በመብቃታቸውም ፈጣሪያቸውን አመስግነዋል፡፡ ትውልደ አሜሪካዊቷ ኢትዮጵያዊት ወጣት ዣምራዊት ደረጀ በአሜሪካ የ”ጉድዊል አምባሳደር” መሆኗን እና ከኦስትሪያ ቬየና 25ኛ ዓመቱን አስመልክቶ በተባለው አገር ድርጅቱን በአምባሳደርነት ያገለገሉት ጥንዶችም በክብረ በዓሉ በመገኘት ልምዳቸውን አጋርተዋል፡፡

አቶ ይስማሸዋ ስዩም የሜሪጆይ የዳይሬክተሮች ቦርድ ሰብሳቢ የ25 ዓመት የሜሪጆይን የልማት ማህበር አጭር ሪፖርት አቅርበው፣ ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተዋል፡ ፡ አርቲስት ቴዎድሮስ ተሾመና ሰዓሊ አብያለው አሰፋ፣ ድምፃዊት ፀደኒያ ገ/ማርቆስ አርቲስቶችን በመወከል፣ አቶ ዮናስ ቬጋስ (ዲያስፖራውን በመወከል) ቀኛዝማች ኃይሉ ቃለወልድና ሌሎችም ጥያቄ አቅርበው መልስ ከመድረኩ ተሰጥቷል፡፡ መድረኩን በአጋፋሪነት የባህል ዝግጅት ክፍል አስተባባሪው ጌታቸው እሸቱ በበቂ ሁኔታ መርቶታል፡፡ ለሜሪጆይ ለተሰጠው ዕውቅናና ላስመዘገበው ውጤት ላበረከታቸው አስተዋፅኦዎች ዓለም አቀፍ እና ሀገር አቀፍ ድርጅቶችና እውቅናና ምስጋና ቢሰጥም፤ ለስኬቶቹ የጀርባ አጥንት የሆኑት ተወድሰዋል፡፡ በቀጣይ 5ዓመት ከህዋሳ የስልጠናና የስብሰባ ማዕከል መገንባት፣ የአዲስ አበባ ህክምና ማዕከልን ወደ ሆስፒታል ደረጃ ማሳደግ፣ በ6 ወራቶች ጊዜ ውስጥ በተለያዩ ዝግጅቶች እንደሚተገበር ተጠቀሟል፡፡

## 35 ተቋማት ከቀረጥ ነፃ መብት የመፍቀድ መብት መያዛቸው ሀገሪቱን ለዝርፊያ ዳርጓታል

የገቢዎች ሚኒስትር ሚኒስትሯ ወ/ሮ አዳነች አቢቤ ባለፈው ሳምንት መገባደጃ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ “በአሁኑ ወቅት 35 ተቋማት ከቀረጥ ነፃ የመፍቀድ መብት ያላቸው በመሆኑ ቁጥጥር ሳይደረግ በሀገሪቱ ሀብት ላይ ትልቅ ዝርፊያ ሲፈፀም ቆይቷል” ብለዋል፡፡

ሚኒስትሯ የ2011 ዓ.ም የገቢ ግብር አሰባሰብ አፈፃፀምን በሚመለከት በአገር ውስጥ ጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ፣ ከአገር ውስጥ ገቢ እና ከታክስ 198 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር መሰብሰቡን፤ እንዲሁም በመጪው 2012 ዓ.ም 248 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር ለመሰብሰብ እቅድ መያዙን አመልክተዋል፡፡

የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በቀጣይ ሳምንታት ያፀድቀዋል ተብሎ የሚጠበቅ አዲስ የንግድ ሕግ ከቀረጥ ነፃ የሚገቡ ምርቶች ላይ ማፅከላዊ አሰራ እንዲኖር ያደርጋል የሚል ዕምነት እንዳላቸው የገለፁት ሚኒስትሯ ወ/ሮ አዳነች እስካሁን በነበረው አሰራር 35 ተቋማት ከቀረጥ ነፃ የመፍቀድ መብት ይዘው መቆየታቸው በቢሊዮን ብሮች የሚገመት የሀገሪቷ ሀብትን ለዝርፊያ መዳረጉን አስታውቀዋል፡፡ አዲሱ ህግ መዕደቅ ለነፃ ቀረጥ ጥያቄ የጊዜ ገደብና የመጠን ገደብ የሚያበጅ በመሆኑ ህጉ ዝርፊያውን ለማስቆም እንደሚያግዝም ተናግረዋል፡፡

## “የአድዋ ማዕከል” ግንባታ በአዲስ አበባ ተጀመረ

በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ወጪ የሚገነባው የአድዋ ማዕከል ግንባታ መጀመሩ ታውቋል፡፡ የአድዋን ታሪካዊ ድሉን በሁለንተናዊ ይዘት ለትውልድ ለማሻገርና የአድዋ ጀግኖችን መዘከርን ታሳቢ ባደረገ መልኩ ነው የማዕከሉ ግንባታ የሚካሄደው፡፡

የዓድዋ ማዕከል ግንባታ ሲጠናቀቅ ከሚሰጠው ማህበራዊና ታሪካዊ ፋይዳ በተጨማሪ በውስጡ የአድዋ ሙዚየም ጨምሮ ከ2 ሺህ ሰው በላይ የሚይዝ ትልቅ አዳራሽ ይኖረዋል፡፡ ሁለት ዓመት የሚፈጀውን የማዕከሉን ግንባታን የቻይናው ጂያንግሱ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚና ቴክኒካል ግሩፕ ያካሂደዋል፡፡

400 ሰው የመያዝ አቅም ያላቸው ተጨማሪ ሶስት አዳራሾች፣ የሲኒማ አዳራሽ፣ ቤተ መጽሐፍት፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችና የአካል ብቃት እንቅስቃሴ መስሪያ ጂም የህፃናት መጫወቻ እና ስፍራዎች፤ እንዲሁም አረንጓዴ ስፍራ፣ ካፌና ምግብ ቤቶች፣ ዘመናዊ ፓርኪንግን የዓድዋ ማዕከሉ እንደሚያካትት ከከንቲባ ጽህፈት ቤት የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡







# በኢጄቶ የምትናጠው ሲዳማና የሐዋሳው ግጭት !

## በዝግጅት ክፍሉ

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ሰሞኑን "የየራሳችን ክልላዊ የመንግስት አስተዳደር ይኑረን፣ ደቡብ ክልል በሚለው የጋራ ክልላዊ አስተዳደር ስር መሆናችን ቀርቶ በየራሳችን ነፃ ክልል ሆኖ የመመዝገብ መብታችን ይከበር" በሚሉ የልዩ ልዩ ብሔሮች ጥያቄ፣ ይህንኑም ተከትሎ በክልሉ አስተዳደር እና በማዕከላዊ መንግሥት በተሰጡ ምላሾች ከፍተኛ ውጥረት ነግሶበት ሰንብቷል።

በደቡብ ክልል ውስጥ ሰፊ የመሬት ክልል እና የላቀ የሕዝብ ቁጥር ያለው የሲዳማ ዞን ተወላጆች "ህገ መንግስታዊ መብታችን ይከበር" በሚል ያነሱትን "የክልል እንሁን" ጥያቄ ተከትሎ ወደ ሌሎች የክልሉ ብሔሮችም የተዛመተው ተመሳሳይ ህዝባዊ እንቅስቃሴ አጠቃላይ የደቡብ ክልልን ወዳልተረጋጋና የግጭት ቀጠና ወደመሆን እየወሰደው በሚገኝበት በአሁኑ ወቅት ጥያቄዎቹን ባነሱ የብሔሩ ተወላጆች፣ በክልሉ መንግሥትና በማዕከላዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ዘንድ እየተወሰዱ ያሉ እርምጃዎች ነገሩን ወደ ከረረ ግጭትና ደም መፋሰስ እየገፉት ነው የሚገኘው።

የደቡብ ብሔሮች ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል ከሚለው የጋራ መታወቂያ ይልቅ ራሱን የቻለ የክልልነት መጠሪያ ይኑረን የሚል አቋም በመያዝ ቀድሞ ጥያቄውን በይፋ ያቀረቡት የሲዳማ ብሔር ተወላጆች ሲሆኑ፣ በቅርቡ በሐዋሳ ከተማ ባደረጓቸው ተደጋጋሚ ህዝባዊ ሰልፎች "የክልል እንሁን" ጥያቄያቸው በአፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጠውና ክልል የመሆን መብታቸው እንዲከበር በአደባባይ ጠይቀዋል። ይህንኑ የሲዳማ ተወላጆች ጥያቄ ተከትሎም በወላይታ፣ ጋሞ፣ ጉራጌ እና ሌሎች የክልሉ ብሔሮች ዘንድ ተመሣሣይ ፍላጎት መኖሩን የሚያንፀባርቁ አቋሞች በይፋ ተንፀባርቀዋል፡ ምንም እንኳን የሁሉም ብሔሮች ጥያቄ ህገ መንግሥታዊ ድጋፍ ያለው የመብት ጥያቄ ቢሆንምና ጥያቄያቸው ተገቢነት ያለው መሆኑ ላይ ማንም ተቃውሞ የሚያቀርብበት መሠረታዊ መነሻ አለው ተብሎ ባይታሰብም ጥያቄው የቀረበበት ወቅት በራሱ ሀገሪቱ በመንግሥታዊ ሥርዓት የለውጥ ሽግግር ውስጥ ያለችበት መሆኑና ለእነዚህ ጥያቄዎች ይፋዊ ምላሽና ዕውቅና የመስጠት መብት ያላቸው መንግሥታዊ ተቋማት (እንደ ምርጫ ቦርድ ያሉት) ገና በአዲስ መልክ እየተደራጁና ለዚህ ትልቅና አንገብጋቢ ጉዳይ ምላሽ መስጠት በሚችሉበት አቅምና ብቃት ላይ የደረሱ አለመሆናቸው ህዝባዊ የመብት ጥያቄዎቹ በአፋጣኝ ምላሽ የሚያገኙበትን ዕድል አልፈጠረም። ጥያቄ አቅራቢዎቹ በተለይም የሲዳማ ብሔር ተወላጆች ግን ለዚህ ሁኔታ ብዙም ቦታ የሰጡትና ምክንያቱን የተቀበሉት አይመስሉም። እንቅስቃሴውን በዋናነት እየመራው ነው የሚባለውና የሲዳማ ወጣቶች ስብስብ የሆነው ኢጄቶ የሚባለው ቡድንም አገራዊ ሁኔታዎች የፈጠሩትን ጫና እና ጥያቄውን በፍጥነት ለመመለስ የገጠሙ መንግሥታዊ ተግዳሮቶችን ባለመቀበል የሲዳማ ክልል የመሆን መብትን ህዝብ በራሱ የሚወስንበትን ቀን ይፋ አድርጓል። ከ11/11/11 (ሐምሌ 11 ቀን 2011 ዓ.ም) ጀምሮ የሲዳማ ሕዝብ ሲዳማ ክልልን በራሱ እንደሚመሰርትም አሳውቋል።

ከ56 ብሔሮችና ብሔረሰቦች በላይ የሆኑ ህዝቦች በአንድ ላይ ታቅፈው በጋራ ሲኖሩበት የቆየው የደቡብ ክልል አጠቃላይ የሕዝብ ቁጥር ከ15 ሚሊዮን በላይ እንደሆነ ይገመታል። ከዚህ ውስጥ ከ7.4 በላይ የሚሆነው ወንድ ከ7.6 በላይ የሚገመቱት ደግሞ ሴቶች እንደሆኑ ይታመናል። ከጠቅላላ የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር አንፃር ሲታይ 16 በመቶ አካባቢ የሚሸፍን የህዝብ ቁጥር ያለው ደቡብ ክልል 105.887.18(አንድ መቶ አምስት ሚሊዮን ስምንት መቶ ሰማኒያ ሰባት ነጥብ አስራ ስምንት) ስኩዌር ኪሎ ሜትር ስፋት ያለው ሲሆን ከፍተኛውን የህዝብ ቁጥርና የቆዳ ስፋት የሚይዙት ሲዳማ፣ ወላይታ፣ ሀድያ፣ ጉራጌ፣ ጋሞ፣ ከፊቾና ስልጤ እንደሆኑ የማዕከላዊ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ የቆየ ሪፖርት ያሣያል።

### የሲአን ውርስ፤

ከ56 ብሔሮች በላይ በሚወከሉበት ከአጠቃላይ የክልሉ ሕዝብ አንፃር ሲሰላ ወደ 20% (ሀያ ከመቶ) የሚጠጋውን የህዝብ ቁጥር የሚሸፍነው የሲዳማ ልዩ ዞን በብሔሩ ተወላጆች በኩል የክልል እንሁን ጥያቄን ሲያነሳ የቆየው ከብዙ ዓመታት በፊት ጀምሮ እንደነበር በሰፊው ሲወሳ ይደመጣል።

በደርግ ዘመነ መንግሥት በ1970 ዓ.ም እንደተመሰረተ የሚነገርለት የሲዳማ አርነት ንቅናቄ (ሲአን) ሊቀመንበር የሆኑት አቶ ዱካሌ ለሚሶ በቅርቡ የሲዳማ ተወላጆች ያነሱትን ጥያቄ በሚመለከት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ‹‹... የሲዳማ ራስን በራስ የማስተዳደር ጥያቄ ነው። ከዛሬ 41 ዓመት በፊት ጀምሮ የነበረ ጥያቄ ነው። ሌላው መነሳት ያለበት የደቡብ መዋቅር ህግን በጣሰና ህገወጥ በሆነ መንገድ የተዋቀረ ነው። በደርግ የሲዳሞ አካባቢ አስተዳደር፣ የጋሞ አስተዳደር፣ ሀይቆች፣ ቡታጅራ፣ የካፋ አካባቢ አስተዳደር ናቸው ያለ ፍላጎታቸው አንድ ላይ እንዲጨፈለቁ የተደረገው። በዚህ ጭፍለቃ ላይ አብረው የሚዋቀሩ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ማን ከማን ጋር ይዋቀር፣ ህዝቡ እንዴት እንሁን ብሎ ተመካክሮ የመወሰን ስልጣን ያለው ህዝቡ ነው። የህዝብ ፍላጎት ከግምት ሳይገባ ያለ ህዝብ ፍላጎት የተመሰረተ ክልል በመሆኑ ነው ሲዳማ ራሱን በራሱ ለማስተዳደር ጥያቄ ያቀረበው። ...በዚያን ወቅት በአቶ ወልደአማኑኤል የሚመራው ሲአን፣ በፕሮፌሰር በየነ የሚመራው የሀዲያ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት፣ በአሰፋ ጫቦ

ቀሪውን በገጽ 26 ይመልከቱ

# "ጭር ሲል አልወድም" የሕወሓትና የአዴፓ ሰሞነኛ ውዝግብ !

ከመንበረ ስልጣኑ የተገፋው ሕወሓት በከተመበት ትግራይ ሆኖ የለውጥ ሂደቱን አደፍራሽ በሆነ ሰሞነኛ መግለጫውም ለ27 ዓመታት በስልጣን፣ ከዛም ቀደም ባሉት ጥቂት የማይባሉ ዓመታት በጫካ ትግል አብሮት የቆየው አዴፓን ወንጅሏል፡፡

"ሽምቅ ተዋጊው ቡድን" በበረሃ ዘመኑ ከያኔው ኢህዴን፣ በኋላ ብ.አ.ዴ.ን ሆኛለሁ ካለው (አዴፓ) ጋር ከፍተኛ ቁርኝት ነበረው፡፡ የመለስ ዜናዊ መንግስት በለስ እየቀናው መጥቶ ስልጣን ሲይዝ፤ ሰፊውን የአማራ ህዝብ እንደልቡ ረግጦ ለመቆጣጠር ያስቻለው ዘንድ "ታማኝ አገልጋዮችና አስፈፃሚዎቹ" አድርጎ በቀረፃቸው ታምራት ላይኔ፣ በረከት ስምዖን፣ አዲሱ ለገሰና መሰል የቀድሞ የድርጅቱ አመራሮች አማካይነት ነበር፣ የድርጅቱን ሕልውና አስቀጣይ የሆነውን መሰረት በጫካ የጣለው፡፡

ይህ የኹለቱ ድርጅቶች ፍቅር ባለፉት ዓመታትም ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ ሕወሓት ለሁለት ሲሰነጠቅ፣ በአባል ድርጅቶቹ መሀል መፈረካከስ ሲከሰት፤ የአቶ መለስ ዜናዊ ቡድን የስልጣን ሚዛኑን ጠብቆ እንዲጓዝና እነ ስዬ አብርሃ ዘብጥያ እንዲወርዱ ዓይነተኛውን ሚና በመጫወት፣ አምባገነኑ ስርዓት በፈላጭ ቆራጭነቱ ለተጨማሪ ዓመታት እንዲቀጥል ያደረገው ብአዴን/አዴፓ እንደነበር አይዘነጋም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ ተቀምጦ፣ ሕዝብን አፍኖና ረግጦ ከመግዛት የአገር ሀብትና ንብረት እስከመመዝበር ድረስ ሁለቱ ድርጅቶች "ስውር ቃል ኪዳን" ያላቸው እስኪመስል ድረስ በጋራ በርካታ ወንጀሎችን ሰርተዋል፡፡

የሕወሓት ቀኝ እጅ የነበሩት ነባር የአማራው ድርጅት አመራሮች ከኃላፊነት እየራቁና በአዳዲሶቹ እየተተኩ፣ አቶ ገዱ አንዳርጋቸውና በሕይወት የሌሉት (ዶ/ር አምባቸውንና አቶ ተስፋዬ) የመሳሰሉ የአዴፓ መሪዎች ከሕወሓት ታዛዥነት ይልቅ የሕዝብን ጥያቄ ወደ ማድመጥ አዲስ መንገድ ሲሸጋገሩ ነበር ኹለቱ ድርጅቶች የዘመናት ፍቅራቸው ተቀዛቅዞ፣ አንዱ በሌላው ላይ ጣት መቀሳሰርን ያመጡት፡፡

በተለይም ከሁለትና ሶስት ዓመታት በፊት በተጠናከረ ሁኔታ የተስተዋለው የአማራና ኦሮሚያ ሕዝብ "ጭቆናን የማውገዝ ትግል" በበረኸኞቹ ተንበርካኪ የነበሩት ብአዴንና ኦህዴድን (በቀደመ ስማቸው) የበለጠ እንዲቀራረቡ ሲያደርጋቸው፤ በአንፃሩ ሕወሓትን ከኹለቱ እንዲነጠል አስገድዶታል፡፡ በለውጡ ማግስትና ከስልጣን ከተገፋበት ጊዜ አንስቶ ደግሞ ሕወሓት ከእነዚህ ድርጅቶች ጋር በጠላትነት መገፋፋቱን ስራዬ ብሎ ተያይዞታል፡፡

በአማራ ክልል መሪዎች የሰከነ አስተሳሰብ ሕልሙ ሊሳካለት ያልቻለው ሕወሓት፣ ከጥቂት ሳምንታት በፊት በባህርዳር የተከሰተውን የአመራሮች ግድያ በተመለከተ ለደረሰው ችግር ሁሉ ተጠያቂው አዴፓ እንደሆነና በዚህም በይፋ ይቅርታ ሊጠይቅ እንደሚገባ የሚያመላክት መግለጫ አውጥቷል፡፡

ሕወሓት አዴፓ ይህንን የማያደርግ ከሆነም ለመዘናት የቆየ ወዳጅነታቸው እንደሚቋረጥና ቀጣይ ሂደቶችም በችግር የተሞሉ ሊሆኑ እንደሚችሉ አስታውቋል፡፡ እውነታው ግን በግልፅ የሚታይ ነው፡፡ ኹለቱ ድርጅቶች ሆድና ጀርባ፤ አንዱ አልሚ፣ ሌላው አጥፊ ከሆኑ ሰነባብተዋል፡፡ አገሪቱን ወደ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለመውሰድ አዴፓና አጋር ድርጅቶቹ ሲደክሙ፣ ሕወሓት በከተመበት መቀሌ ሆኖ "ለውጡ አልተሟላም፣ ክፍተቶችና ችግሮች ተሞልቷል" በማለት የፖለቲካው ምህዳ መስፋትን ያጣጥላል፡፡ ለዚህም ይመስላል አዴፓ ለሕወሓት በሰጠው ምላሽ ለውጡን ለመቀልበስ ከመውተርተር ባሻገር በተለያዩ የሰብኣዊ መብት ጥሰቶች ወንጀል የሚፈለጉ፣ የአገርና የሕዝብ ሀብት በመዝረፍ በሌብነት የተጠረጠሩ ግለሰቦችን በጉያው ሸሽጎ በመያዝ፤ ወንጀል ፈፃሚ መሆኑን በተግባር ያረጋገጠው የትግራዩ ነፃ አውጪ ቡድን እንደሆነ ያስረዳው፡፡

"ጭር ሲል አልወድም" ዓይነት የሆነው የሕወሓት መግለጫና ከኦዴፓ ጋር የፈጠረው ውዝግብ፤ በምንም መንገድ ቢታይ ተገቢ ካለመሆኑ ባሻገር ወቅቱን የጠበቀ ነው ማለትም አይቻልም፡፡ በተገኘው መንገድ የአማራና የትግራይ ሕዝብን ወደ ጦርነት ለመክተት የሚጣደፈው ሕወሓት ሰሞነኛ ነገር ትንኮሳውና ማሳሰቢያ ድርጅቱ በአገራዊ ግጭቶች መሀል ወደ ስልጣኑ ለመመለስ የሚጓጓለትን የመከነ ሕልሙን ለመተግበር መሞከሩ እንደሆነ በፖለቲከኞች ይነገርለታል፡፡

በኹለቱ ድርጅቶች አለመግባባት (ለዚያውም አላስፈላጊ በሆነ መግለጫ) ለዘመናት ተጋብተው፣ ተዋልደው፣ ተፋቅረወና ተሳስረው የኖሩ ሕዝቦችን ወደ ጦርነት መክተት ፈፅሞ እንደማይቻል እየገለፅን፤ የሕወሐትን ትንኮሳ በማውገዝ ደ.ኢ.ህ.ዴ.ን (የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ) የአዴፓ አጋር መሆኑን እንዳሳየበት ዓይነት መግለጫ፤ ፌደራል መንግስቱም በመስጠት ለውጡን የማስቀጠል ሕዝባዊ ኃላፊነት እንዳለበት ለመጠቆም እንወዳለን፡፡


**ግዮን መጽሔት**

**ኢትዮ ሐበሻ ኅትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር**

**በየሳምንቱ ለኅትመት የምትበቃ መጽሔት**

**ማኔጂንግ ዳይሬክተር**
ፍቃዱ ማ/ወርቅ

**ዋና አዘጋጅ**
ሮቤል ምትኩ

አድራሻ፡- የካ ክ/ከተማ ወረዳ 2
የቤት ቁጥር 475

**ከፍተኛ አዘጋጅ**
አለማየሁ ባዘዘው
ብሩክ መኮንን

**አዘጋጅ**
ፍቅርተ ተሾመ
ሙሉጌታ አክሊሉ

**አምደኞች**
ፍቅሩ ኪዳኔ **(ከሲውዘርላንድ)**
ዶ/ር ዘሪሁን ሙላቱ
ተስፉ (ኢትዮጵያ) አልታሰብ
መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

**ጸሐፊ**
ሠላም ግርማ

**ክርኤቲቭ ዲዛይን**
ፍፁም ንጉሴ


**የዝግጅት ክፍሉ አድራሻ**
አራዳ ክ/ከ ወረዳ 09 የቤት ቁጥር 552/1
አምባቸው ህንፃ 2ተኛ ፎቅ ቢሮ ቁ. 207
ፖስታ ቁ. 676 ኮድ 1029
ስልክ ፡ +251 911 227661 +251 912 165606
+251 118 12 2333
ኢ-ሜይል፡
enqu2013@ gmail.com
Ghion2011meg@gmail.com
Facebook
Gihon-meg Fekadu
www. facebook.com/enqu2013

**አታሚ**
ቴዎድሮስ ገብሩ ማተሚያ ቤት ፤ አራዳ ክፍለ ከተማ
ወረዳ 10 የቤ.ቁ. 066/ሀ
0911223335/ 0911420506



በዚህ መጽሔት ላይ የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ ማተሚያ ቤቱን አይመለከትም

# “እንደ ሀገር የመጨረሻው ቁስል ላይ ደርሰናል”



## የሰብኣዊ መብት ተሟጋቹ አቶ ኦባንግ ሚቶ

*“ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ” መስራችና የሰብኣዊ መብት ተሟጋቹ ኦባንግ ሚቶ ከሚኖርበት ካናዳ በድጋሚ ወደ ሀገር ቤት መጥቷል፡፡ “ሰው በሰውነቱ ብቻ ሊከበር ይገባዋል” በሚለው መርኹና የብሔር ፖለቲካን አምርሮ በመቃወም የሚታወቀው ኦባንግ በዘረኝነት ልክፍት የሚባዝኑ ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን ለመታደግ የሚያስችል አዲስ ፕሮጀክት ቀርጾ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል፡፡*

*በባህር ማዶ ሲንቀሳቀስ የቆየው የኦባንግ የሰብኣዊ መብት ድርጅት ሰሞኑን በሀገር ቤት ህጋዊ ምዝገባ በማካሄድ ቢሮውንም ከፍቷል፡፡ በጋምቤላ ስላለው አስከፊ የደቡብ ሱዳን ስደተኞች እንቅስቃሴና በአገሪቱ ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ከሰብኣዊ መብት ተሟጋቹ ኦባንግ ሚቶ ጋር የግዮን ጋዜጠኛ ፍቃዱ ማ/ወርቅ ያደረገውን ቆይታ እንደሚከተለው አቅርቦታል፡፡*

**ግዮን፡- ባለፈው ከበርካታ ዓመታት በኋላ ወደ ሀገር ቤት በመጣህበት ወቅት የመጽሔታችን እንግዳ እንደነበርክ ይታወሳል፡፡ በቅርቡ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ መጥተኻል፡፡ የአሁኑ አመጣጥህ ምክንያት ይኖረው ይሆን?**

ኦባንግ፡- እንዳልከው ከአስራ ስድስት ዓመት በኋላ ነበር ለውጡን ተከትሎ ባለፈው ወደ ሀገሬ የመጣሁት፡፡ አሁን የተመለስኩት ደግሞ በሰብዓዊ መብት ዙሪያ የሚሰራው የእኛ ድርጅት፣ በዚህ ሀገር በሕጋዊነት ተመዝግቦ እንዲንቀሳቀስ ነበር፤ እሱን አሳክተናል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ህጋዊ ምዝገባውን ተከትሎ አገር ውስጥ ቢሮ ለመክፈት ነው፡፡

በተጨማሪም በአገሪቱ ውስጥ የተፈጠረውን ለውጥ ለማገዝ፣ የድርሻችንን ለመወጣትም ፍላጎት አለን፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞም ያሰብነው ፕላን አለን፡፡ በሀገራችን ብዙ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ቢኖሩም፤ እኛ የበለጠ ትኩረት ሰጥተን የምንሰራው በተማሪዎቹና በወጣቶች አካባቢ የአስተሳሰብ ለውጥን ማምጣት ነው፡፡

ባለፈው በመጣንበት ጊዜ ወደ ሰባት ክልሎችና አስራ አራት ዩንቨርስቲዎች ተጉዘን፣ የአገር ሽማግሌዎችን አነጋግረናል፡፡ እንደየክልሎቹ ባህልና እምነት ተሰሚነት ያላቸው የአገር ሽማግሌዎች በስፋት አወያይተናል፡፡ ከመንግስት ባለስልጣናትም ጋር በተመሳሳይ ተገናኝተን በጉዳዩ ላይ መክረናል፡፡

አሁን ዋነኛ ትኩረታችን ወጣቶች ላይ ነው፡፡ ምክንያቱም ዩንቨርስቲዎች የዕውቀት ፍሬ መቅሰሚያ መሆናቸው ቀርቶ የግጭት ሜዳ ሆነዋል፡፡ ተማሪዎች ከት/ቤት ወደ ወላጆቻቸው ሲመጡ ዲግሪ ይዘው እንጂ ሌላ ብሔር የደበደቡበትን ዱላና ድንጋይ ይዘው መሆን የለበትም፡፡ አሁን እንዲህ ዓይነቱን ክስተት በአገራችን ዩንቨርስቲዎች ውስጥ በስፋት እየተመለከትን ነው፡፡

**ግዮን፡- የእንዲህ ዓይነት ግጭቶች መንስኤ ምንድን ነው ብለህ ታምናለህ?**

ኦባንግ፡- በነገራችን ላይ እኔ በእነዚህ ልጆች ላይ ብቻ አልፈርድም፤ በተወሰነ ደረጃ ስህተት ቢኖርባቸውም፡፡ ገበሬ እንደሚለው ሰው የዘራውን የሚያጭደው ፤ ባለፉት ሀያ ሰባት ዓመታት ስልጣን ላይ በነበረው መንግስት አማካይነት የተዘራው ሰዎችን በብሔር የመከፋፈል፣ የመለያየትና የጥላቻ ፕሮፐጋንዳ ነው፡፡ በእነዚህ ዓመታት ስለ አገር ፍቅር፣ አንድነትና አብሮነት ፈፅሞ አልተሰበከም፡፡ ዛሬ በዚህ መልክ የተዘራውን ነው ልጆቻችን እያጨዱ ያሉት፡፡

እንደምናቀው “ልዩነታችን ውበታችን “ የሚሉ የማብያያና ማስመሰያ ቃላት፣ የተንኮል አስተሳሰቦች ነው በዚህች ሀገር ላይ ወያኔ ሲሰበክ የኖረው፡፡ አንድትን ሳታጠናክር “ልዩነታችን ውበታችን” እያልክ የምታወራ ከሆነ ውጤቱ ጊዜውን ጠብቆ የሚደርስ ይሆናል፡፡ ባለፉት 27 ዓመታት በኢትዮጵያ ስልጣን ላይ የነበረው ሲስተም እንኳን አገር ሊመራ ቀርቶ ቤተሰብ ሊያስተዳድር የማይችል ነበር፡፡

እነዛ አካላት የአገር ገዢ ቢሆኑም ኢትዮጵያ የምትባል አገር እንድትኖር ግን ፈፅሞ አይፈልጉም፡፡ ደርግ ከወደቀ በኋላ ምንም የተወለጠ ነገር የለም፤ የገዢነት መንፈስ ነው የነበረው፡፡ ወያኔ/ኢህአዴግ ኢትዮጵያዊነትን ከማለዳው ነው ማጥፋት የጀመረው ኢትዮጵያዊነትን ቢኮሩበት ኖሮ፤ በሕገ መንግስቱ ውስጥ የአገሪቱን አንድነት የሚጠብቁ የተለያዩ ህጎችን ያስቀምጡ ነበር፡፡ እነሱ ግን “እኛ ብቻ” በሚል መንፈስ፣ ሆን ተብሎ በተንኮል የተሞላ ስራ ነው ሲሰሩ የቆዩት፡፡ እሱ ነው ለልጆቻችንን መደባደብና መገዳደያነት የተረፈው፡፡

ወያኔ አደገኛ የሆነ ፕላን ነው የነበረው፡፡ ሰዎችን በብሔር ከፋፍሎ የፈጠራ ታሪኮችን እየተረከ፣ እርስ በርሱ በማጋጨት ስልጣኑን ማራዘም ነበር ፍላጎቱ፡፡ ዛሬ ላይ እናቶች ወደ ዩንቨርስቲ የላኳቸው ልጆች ተመርቀው ይመጡ ይሆን? አስከሬናቸው ይደርሰኝ ይሆን? የሚል ስጋት ውስጥ ገብተዋል፡፡ ዛሬ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ከየቦታው ለመፈናቀል የተገደዱት በድርቅ ወይም በችግር ሳይሆን የተሰራብን ፖለቲካ የፈጠረው ጥላቻ ነው፡፡

ዛሬ እንደ ሀገር የመጨረሻው ቁስል ላይ ደርሰናል፤ ከመቁሰልም አልፈን በስብሰናል፡፡ አሁንም የሚሰሙ አሳዛኝ ነገሮች አልቆሙም፤ ምንም ሳይሰሩ “ክልል እንሆናለን” የሚል ጥያቄዎች በስፋት እየቀረቡ ናቸው፡፡ እነኚህ ነገሮች ሁሉ የሚያስከትሉት ችግር መጠነ ሰፊ ነው፡፡ ከእነዚህና ከሌሎች መሰል የአገሪቱ ችግሮች አኳያ እንደ ድርጅትም፣ እንደ ዜጋም የራሳችንን አስተዋፅኦ ለማበርከት ነው ወደ እዚህ የመጣነው፡፡

**ግዮን፡- በሀገር ውስጥ ላስመዘገባችሁት ድርጅታችሁ ምን የሚል ስያሜ ሰጣችሁት? ቢሮአችሁንስ በየትኞቹ ክልሎች ነው የምትከፍቱት?**

ኦባንግ፡- ድርጅቱ አስቀድሞ በሚታወቀው “ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ” በሚል መጠሪያችን ነው የተከፈተው፡፡ ይህን ድርጅት ቀደም ባሉት ዓመታት በውጭው ዓለም የነበርን አገር ወዳዶች የዛሬ አስራ ሁለት ዓመት ገደማ ነው የመሰረትነው፡፡ በፊት ከአገር ርቀን የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን በአገራዊ ጉዳዮች ላይ እናደርግ ነበር፡፡አሁን ሀገር ቤት መጥተን ህጋዊ ምዝገባ አድርገናል፡፡ ሳርቤት አካባቢም ቢሮአችንን ከፍተናል፡፡

እኛ ከፖለቲካ ፓርቲነት በተለየ መንገድ በሰብዓዊ መብት መከበር ዙሪያ የምንሰራ ብንሆንም፤ እግረ መንገዳችንን ልጆቻችን ▶

ስልጣን ላይ የነበረው መንግስት በዘራው የጥላቻ መንገድ እንዳይጓዙ፣ ስለብሔራቸው ከማሰብ ይልቅ ስለ አገራቸው እንዲያልሙ፣ እንዲጨነቁ ትኩረት ሰጥተን እንሰራለን። የትኛውም አገር ላይ የዜግነት ስሜት፣ እንጂ የብሔር ፍላጎት የሚባል ነገር የለም። እንዲህ ዓይነት የጥፋት ፕሮፓጋንዳዎችን ሲያሰርፅና ሲያስተጋቡ የኖሩት የእኛ አገር መሪ ነን ባዮች ብቻ ናቸው።

ሌላው በተበላሸ አስተሳሰብ ውስጥ እንዲዋልሉ የተደረጉ ወጣቶችን ማነፅና ከማስተካከል ባሻገር በየቦታው እየተዘዋወረን የነቃ ተሳትፎ ሊያደርጉ፣ መሪ ሊሆኑ የሚችሉ ልጆችን መርጠን አንድ ላይ በማሰባሰብ በቂ ስልጠና እንሰጣለን። የሀገር ፍቅር ማለት ምን እንደሆነ ሊረዱ በሚችሉበት፤ ብሎም የነገ አገር ተረካቢና መልካም መሪ መሆን በሚያስችላቸው መንገድ እንዴት መጓዝ እንዳለባቸው ሊያውቁ በሚችሉበት ሁኔታ ላይ በቂ ትምህርት እንሰጣለን። ለዚህ ደግሞ ትክክለኛ ባለሙያዎችን እናስመጣለን።

በተጨማሪም ከዚህ ቀደም በብሔር ልዩነትና ጥላቻ ወደ አስከፊ ግጭት የተገፉ፣ ለምሳሌ በሩዋንዳ የሚኖሩ ሰዎችን በማምጣት፤ ዘረኝነት ምን ዓይነት ጉዳትና ጥፋት እንደሚያመጣ፣ አገርን እንዴት እንደሚያፈራርስ በአካል ተገኝተው ለእነዚህ ለመረጥናቸው ልጆች የሚያስተምሩበትን ሁኔታ እናመቻቻለን። በዚህ መልክ በተጨባጭ፣ በመልካም ዲሲፕሊን የሚታነፁት ልጆች ወደየመጡበት ክልል ሲመለሱ፤ የአካባቢያቸውን ወጣት በማስተማርና በማስተባበር መሪ ይሆናሉ ማለት ነው። በስምንት ክልሎች ውስጥ ይህንን የመተግበር ዕቅድ አለን።

ዋነኛ ትኩረታችንን ያደረግነው በሃያ ስድስት ዩንቨርስቲዎች ላይ ነው። በእነዚህ ቦታዎች ብሔራዊ መግባባት ማለት ምን እንደሆነ፣ በጥልቀት ለማስረዳት እንሞክራለን። መስከረም ላይ ተቋማቱ ትምህርት ሲጀምሩ እኛም ይህንን ተግባር ላይ እናውላለን ብለን እናስባለን።

***ግዮን፡- የሲዳማ ሕዝብ ያቀረበውን የክልልነት ጥያቄ ሰሞኑን በራሳችን መንገድ እውን እናደርጋለን ሲሉ ታይተዋል፤ መንግስት በበኩሉ አካሄዱን እንደማይቀበል ጥብቅ ማሳሰቢያ ሰጥቷል። አገሪቱ ችግር ላይ እያለች እንዲህ ዓይነት ተጨማሪ ነገር መምጣቱን እንዴት አየኸው?***

አባንግ፡- ችግሩ የመነጨው ዛሬ ሳይሆን በእነዚህ ሰዎች አስተሳሰብ ላይ የዛሬ ሃያ ሰባት ዓመት መሰራት በጀመረበት ወቅት ነው። አስቀድሜ እንዳልኩት እነዛ የኢትዮጵያ ጠላት የነበሩት ሰዎች የሰሩት ክፉ የቤት ስራ ነው ዛሬ እንዲህ ዓይነቱን ጥያቄ ያስከተለው። ወያኔዎቹ እኮ ከጫካ ሲገቡ የያዙትን የነፃ አውጪ ስያሜ ዛሬም አልቀየሩም። ነፃ የመውጣት ፍላጎታቸው ደግሞ አንድነቷ የፀና ከነበረው ኢትዮጵያ ነው። አማራ፣ ትግሬ፣ ኦሮሞ፣ ደቡብ እያሉ የከፋፈሉት እነሱ በሚመቻቸው መንገድ እንጂ በትክክል ሕዝቡን ተጠቃሚ ባደረገ ሁኔታ አልነበረም።

**. . .ዛሬ ክልል እንሁን እያሉ የሚጮኹት ሰዎች በጥቅም የተያዙ ናቸው፤ ተበታትነን ልናልቅ እኮ ነው፤ በእኛ አገር ያለው ሰንደቅ ዓላማ ብዛት ራሱ ያሳዝናል። ሁሉም ክልል ነኝ እያለ የራሱን ባንዲራ ይሰቅላል፤ ምን ማለት ነው ይሄ? አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የአገር ሉዓላዊነት ሳይሆን የብሔር ሉዓላዊነት ነው፤ "የብሔር የበላይነት" ነው የሚታየው . . .**

ሆን ተብሎ ታቅዶ በተንኮል የተሰራ ሲስተም መጨረሻው ዛሬ ወደምናየው ነገር ነው የሚያደርሰው። መለስ ዜናዊና ጓደኞቻቸው ያስቡ የነበረው ስለ አገር ሉዓላዊነት አይደለም። የሀገር ፍቅር ስሜትና ባህሪይም ፈፅሞ በውስጣቸው የለም። ባህል፣ ታሪክ፣ እሴት አይገባቸውም። እነሱ አገር አስገንጣይና በታኞች ነበሩ። ስልጣን ከያዙበት ጊዜ አንስቶ የሚቀርጿቸው ሕጎች በሙሉ በዚህ እሳቤ የተጠነሰሱ በመሆናቸው፣ ስር የሰደደው ልዩነት ጊዜውን ጠብቆ ተከታታይ ችግሮች በተከታታይነት እንዲፈጠሩ ዓይነተኛ ሚና ተጫውቷል።

***ግዮን፡- ግን ጥያቄው በትክክል በዚህ ወቅት መነሳት ነበረበት?***

አባንግ፡- አሁን ክፍተት ተገኘ፤ ለዛ ነው ሩጫው። የሚገርመው ነገር ያኔ ሕገ መንግስቱ ሲረቀቅ ከደቡብ ሰዎች የጠየቀ ነበር ወይ? ማንም የለም። ጥቂት ሰዎች በራሳቸውና በአሻንጉሊቶቻቸው ታጅበው ነው ሕገ መንግስት አፅድቀናል ያሉት። እነዛ ኢትዮጵያን የማይወዱ ሰዎች በሰሩት ስህተት ነው አሁን እኛ ዋጋ እየከፈልን ያለነው። ሰላማችንን አሳጥተውናል።

የሲዳማዎቹ ጥያቄ ዛሬ ሳይሆን ከ27 ዓመት በፊት ነበር መቅረብ የነበረበት፤ በሰዓቱ ግን ሲዳማዎችም ሆነ ደቡብ ውስጥ ያሉ ወላይታ፣ ከምባታ፣ ሀዲያ የመሳሰሉ ብሔሮች አልተጠየቁም። በሌላ መንገድ እንየው ከተባለ አናሳ ከሚባሉት ብሔሮች መሀል አንዱ የሆነው የሶማሌ ሕዝብ ከትግራይ ክልል በሕዝብ ብዛት ይበልጣል፤በመሬት ስፋትም ይበልጣል። ግን በፖለቲካ አወቃቀር ከአራቱ ዋነኛ የኢህአዴግ ድርጅቶች ጋር አልተመደበም፤ ለምን አጋር ፓርቲ ተባለ? በመልክ ነው? በቋንቋ? በምንድን ነው? ሶማሌ፣ አፋር፣ ቤኒሻንጉል ገለል ተደርገው "የአጋር ድርጅት" ታፔላ የተለጠፈባቸው ለምንድን ነው? ያኔ ከጅምሩ ነው ስህተት የተሰራው፤ በፊት አንድም ነገር ያልተነፈሱ ሰዎች ጸጥ ብለው ኖረው፤ ዛሬ ግን ቀዳዳው እየሰፋ መጥቶ አስከፊ ችግር ላይ እንድንወድቅ አድርጎናል።

***ግዮን፡- አሁን ምን መደረግ አለበት?***

አባንግ፡- በመወያየትና በመነጋር፣ ጥያቄ ዎችም ወደ ሌላ መንገድ ከመጓዛቸው በፊት በመመካከር ነገሮችን መፍታት ይቻላል። ይሄን ጉዳይ በተመለከተ መንግስት ራሱ አስቀድሞ ኃላፊነቱን መወጣት ነበረበት። እኔ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እንደተመረጡ የጠበቅሁት ዋነኛ ነገር የብሔር ፖለቲካን መልክ ያስይዙታል ወይም ያስተካክሉታል የሚል ነበር። ሁላችንም በዚህ የዘረኝነት በሽታና ህመም ውስጥ ነን። ይሄንን በሽታ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ ያክሙታል ብዬ ገምቼ ነበር፤ ግን አልሆነም።

እንደውም በአንፃሩ ባለፉት አስራ ሁለት ወራት የብሔር ፖለቲካ በኢትዮጵያ ተጋጋለ። ለበሽታ መፍትሔ አለመፈለጋችን አሁንም ችግሩ የባሰ እንዲሆን አድርጓል። የብሔር ፖለቲካውን ማርገብና ማስወገድ አለመቻላችን ታይቶ በማይታወቅ መልኩ በአጭር ጊዜ ውስጥ መፈናቀሎች በስፋት እንዲከሰቱ፤ ከጋራ ስሜት የመጡና ግለኝነት ላይ ያተኮሩ "ኬኛ" ፣ "ኬኛ" የሚሉ እንቅስቃሴዎች እንዲወለዱ መንገድ ጠርጓል።

አሁን ያለው የሲዳማ ጥያቄም ይህንኑ የግለኝነት ኢንተረስት መሰረት ያደረገ፤ ከደቡብነት ራስን ለማራቅ የቀረበ ሀሳብ ነው። በደቡብ ውስጥ ከሲዳማ ጋር አስራ አንድ ዞኖች ናቸው የክልልነት ጥያቄ ያቀረቡት። በዚህ መልክ ሄደን ሄደን የት ላይ ልንቆም ነው? የእዚህ ትልቁ ችግር በተለይም በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የብሔር ፖለቲካን መቆጣጠር አለመቻሉ ነው። ይሄ ቁጥጥር ያስፈልገው ነበር። ከዚህ በኋላ የክልል አወቃቀርን የሚያስተካከል አሰራር በህግ ማዕቀፍ ውስጥ፣ (እስከ ፓርላማው ድረስ በማቅረብ) ማካተት ካልተቻ ከምናየው የበለጠም ነገር ሊከሰት ይቻላል። የትኛውም ዓለም ብትሄድ እንስሳ ነው እንጂ ሰው አይካለልም።

በጆኦግራፊ ብንሄድ ኢትዮጵያ ውስጥ ጋምቤላ ብሔር አይደለም፤ ጂኦግራፊ ነው። ሲዳሞ፣ ጋምቤላ፣ አፋር፣ የሚለው ነገር በብሔር ከሚሆን ይልቅ ጂኦግራፊን መሰረት ያደረገ ቢሆን የተሻለ ውጤት ይገኛል። ምናልባት በሚሰሙት ዓይነት እንቅሰቃሴዎች አገሪቷ እንድትቆራረስና ችግር ውስጥ እንዳንገባ፣ ከዚህ በፊት የነበረውን ሲስተም በማስወገድና በማፈራረስ፤ በጥንቃቄ አዲስ አሠራር መዘርጋት ይኖርብናል።

ቀሪውን በገጽ 24 ይመልከቱ

# "ኢሕአዴግ ዘምሟል"

# መግለጫዎቹ የገለጡት እውነት

መላክ ቢ.

የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) ከመመስረቱ በፊት ለትጥቅ ትግል ወጥተው የጋራ መንገድ ያገናኛቸው ሁለት ሃይሎች፤ ትግሬውን የወከለው የትግራይ ህዝብ ነጻ አውጪ ግንባር (ትህነግ / የዛሬው ሕወሓት) እና ኢትዮጵያን የወከለው የኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህዴን/የዛሬው አዴፓ) ናቸው። በቆይታ ግንባር የመመስረት ሃሳብ ያቀረበችው ሕወሓት ኢህዴንን የኢትዮጵያዊነት ካባውን እንዲያወልቅና በአማራ ብሔር ስር ገብቶ ብሔራዊ ፓርቲ እንዲሆን ስትሞላው ኢህዴን ሞተ። ከከተማ እስከ አሲምባ ለዴሞክራሲ እና ለነጻነት ሲታገሉ የዘለቁ ጓዶችን ያቀፈው ድርጅት፣ አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ባንዲራውን ጥሎ ላይቤሪያ ከአሜሪካ እንደቀዳችው ሰንደቁን ከነፍስ አባቱ ሕወሓት ቀድቶ ወደ ብአዴንነት ተለወጠና "አማራውን የምታገልለህ እኔ ነኝ" ብሎ ከሰፊዋ ኢትዮጵያ ጓዙን ጠቅልሎ ወደክልል ገባና ቁጭ አለ። ። እነሆም "ብሄረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ" ስሙ ሆነ።

በርግጥ አማራን ትምክህተኛ እና ጨቋኝ ህዝብ ነው ብላ የፈረጀችው ሕወሓት የትግሏን ማጠንጠኛ በማኒፌስቶዋ ጭምር በጸረ አማራ ንቅናቄ ላይ የከመረች ድርጅት ናት። ትህነግ "ትግሬውን ከአማራ አገዛዝ ነጻ ለማውጣት" በሚል ስም 'ነጻ አውጪ ግንባር' ብላ ራሷን ብትሰይምም ብአዴን ግን ወዲህ አማራ በባርነት ውስጥ ነኝ ብሎ የሚያምን ህዝብ አይደለምና ፣ ወዲህም ገዢ የሚባለው አማራ 'ተገዢ ህዝብ ነው' የሚል የርዕዮት ድጋፍ በዘመኑ አልነበረምና ነጻ አውጪ መባሉን ትቶ ስሙን በዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ አጽንቶ መታገል ጀመረ። "ብአዴን በጊዜው ለአማራ ህዝብ የዋለለት ውለታ ይህ ብቻ ነው" ይላሉ ዝክረ-ብአዴን ተራኪዎች። ብአዴን እንደኦነግ እና ትህነግ ፣ ኋላ እንደመጡትም ኦብነግ እና ጋህነን ወዘተ ነጻ አውጪ ግንባር ያልሆነበትን ምክንያት የሚተነትኑ ሰዎች ሲናገሩ፤ ብአዴን አማራን ነጻ አወጣለሁ ብሎ በእምነት ወደስራ ለመግባት ጉሮሮውን ያነቀው አማራ አለመሆኑ ነበር። ሕወሓት "እንደ ሲጋራ መሬት ጥለን ረግጠነዋል፣ ቀብረነዋል" ያለችውን የአማራን ብሄርተኝነት (በነርሱ አጠራር ትምክህተኝነት) እስከወዲያኛው እንዳያንሰራራ ለማድረግ የአስርተ አመታት ዕቅድ ይዛ ንቅናቄውን አማራ ባልሆኑ የፓርቲው መሪዎች እጅ ውስጥ ጣለችው። ብአዴን አማራን በመምራት የሽፋን ሃሳዊ ስመ-አማራነቱን ይዞ በዴሞክራሲ ስም አማራን አገለግላለሁ ብሎ ከተመ። ሕወሓትም የመደብ ጠላቷ አድርጋ የያዘችውን አማራን በብአዴን በኩል በሪሞት ኮንትሮል እየተቆጣጠረች ዘለቀች።

አማራን የሚሳደቡ መሪዎችን ይዞ በመላው አማራ 28 ዓመታት የመራው ይህ ፓርቲ ሁሌም በሕወሓት አሽከርነት እና ተልዕኮ አስፈጻሚነት እየተወቀሰ እና እየተሰደበ ቆዳውን የዝሆን ቆዳ አድርጎ የዘለቀ ድርጅት ነው። ነጻ አውጪ መሆን ቆራጥነትን ብቻ ሳይሆን ግልጽ ግብን እና የሚታወቅ አላማን ስለሚሻም ብአዴን በዴሞክራሲ ንቅናቄ ስም ለአማራው ቆሜያለሁ ብሎ በተግባር ግን የሕወሓት አጀንዳ አራጋቢ ሆኖ ኖረ። ከመሃል ብቅ የሚሉ የአማራ ብሄርተኞችን "ትምክህተኛ" በሚል ቃል እያሸማቀቀ እና እያጠፋ በዚህ ሰፊና ትልቅ ህዝብ ላይ የዘመኑን ታላቅ ቀልድ ሲቀልድበት እና ሲያስቀልድበት ኖረ።

ኢህአዴግን ለመመስረት የአማራው እና የትግሬው ፓርቲ ወሳኝ ድርሻ ቢኖራቸውም በጽንሰሃሰብ ደረጃ ኢህአዴግን የመሰረተችው ሕወሓት መሆኗ ግን አንድ ሁለት ክርክር አያስፈልገውም። በድል አጥቢያ ስትራተጂ ትግራይን ገንጥሎ ወዴትም መሄድ እንደማያዋጣ ያወቀችው ሕወሓት የታላቋን ትግራይ ሪፐብሊክ ለመመስረት አንድም በቂ ሃብት ማካበት ሁለትም በፖለቲካ ሻጥር በቂና ወሳኝ የእርሻ መሬት ማጠር አስፈላጊ መሆኑን ስላመነች የበረሃ ስሟን ሳትቀይር በኢህአዴግ ብርድልብስ ውስጥ ኢትዮጵያዊ ሆና መጣች። አማራውንም፣ ኦሮሞውንም፣ ደቡቡንም በዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ ስም አደራጅታ ብቻዋን ነጻ አውጪ ስሟን እንደያዘች ኢህአዴግን መሰረተች። ብአዴንን በአማርኛ ተናጋሪ ትግሬዎች እና ኤርትራዊያን እንዲሁም ጥቂት አማሮች አዋቅራ ፣ ኦህዴድን ደግሞ ኦሮምኛ ተናጋሪዎችን መልምላ አሰባስባ ፣ደኢህዴንን ደግሞ ለድል ሩብ ጉዳይ ላይ በደቡብ ተወላጆች መስርታ ሁሉንም ወንዝ ለወንዝ አማማለችና ራሷን መሪ አድርጋ በግንባርነት ጠቀለለቻቸው። እነሆም ኢህአዴግ በተባለ የሕወሃት ንብረት ውስጥ ሶስቱም አሻንጉሊት ድርጅቶች ለ28 ዓመታት ሙሉ ለሕወሓት ሰጥ ለጥ ብለው ሲገዙ መኖራቸው ምክንያቱ ይኸው ነው።

ሕወሓት ለቀጣዮቹ 40 ዓመታት የሚኖረውን ቅርጽ እና የፖለቲካ አሰላለፍ የሰሩት የድርጅቱ ስትራተጂስት መለስ ዜናዊ ድንገት ከሞቱ በኋላ ድርጅቱ ጎኑ በሰፊው ▶

ተከፈተ። እንኳን የያዘውን ስልጣን ለሌላ ብሄር ሊለቅ ቀርቶ ለራሱ ጓዶች እንኳን የራሱን አመራር ጥበብ ማውረስ ሳይችል ያለፈው የመለስ ዜናዊ አስተዳደር፤ ድንገት መብራቱ ሲጨልም ሕወሓትን ጎነ ክፍት ድርጅት አደረጋትና ደፋሪዋ በዛ። ለተወሰኑ አመታት አሻንጉሊት ጠቅላይ ሚኒስትር አስቀምጣ ሃይሏን ባለበት ለማኖር ብዙ የጣረችው ሕወሓት 2010 ዓ.ም ላይ በቃን ብለው ውስጧን በፈለቀቁት አማራ እና ኦሮሞ የለውጥ ሃይሎች ግብዓተ መሬቷ ተፈጸመ። እንደታለመው ትግራይን ከሪፐብሊኩ ዘወር ለማድረግ በቂ ነው ባይባልም የማይናቅ ሃብት ሰብስባ፣ አንዳንድ የአማራ ክልል መሬትንም "የኔ ነው" ብላ ወደራሷ አካትታ የቀደመ ዘመን ፈጣሪዎቿን መቀሌ ላይ ሰብስባ ተቀምጣለች። ከፋኝ ባለች ጊዜ ሰበብ ፈልጋ ለመምዘዝ የአንቀጽ 39ን ካርታ እያሽሞነሞነች ከወዲሁ "ህገመንግስቱ ይከበር" እያለች ነው። ሕወሓት አስቀድማ እንዲህ ያለ ችግር ቢገጥማት ህገመንግስቱ የነፍስ ማዳኛ ሰነድ እንዲሆናት አድርጋ ሰርታዋለችና ማስፈራሪያዋም ማደናገሪያዋ እሱው ሆኗል።

እሷ የፈለፈለቻቸው ድርጅቶች ግን በየዘርፋቸው ብዙ ጉድ ሲያስተናግዱ ነው የኖሩት። በኦሮማራ ጥምረት ለሕወሓት መዘርጠጥ መሰረታዊውን ትግል የመሩት ብአዴን እና ኦህዴድ ስማቸውን ለውጠው አዴፓ እና ኦዴፓ ሲባሉ ደኢህዴን ደግሞ ክልሉ ተበታትኖ ዘጠኝ ትናንሽ ሊሆኑበትና የራሱን ህልውና ሊያከትሙበት የሚተራመሱበትን ድርጅቶች ሲያግድ ቆየ። ቄሮን የፈጠረው ኦዴፓ ኦነግን በጓሮ በር አስገብቶ ኋላ ግን ከርሱው ጋር አይንና ናጫ ሆኖ ሲፋለም፣ የፋኖው አዴፓ ደግሞ አብንን ፈጥራ የአማራ ብሄርተኝነትን አገነነችው። ሕወሓት ከማዕከሉ ተባርራ የየዕለት እርግማንና እና ትችት እየዋጠች ጸጥ ብላ የተቀመጠች መሰለች። በተግባር ግን ሃገሪቱን አንዴ በብሄር ግጭት፣ አንዴ በሃይማኖት ግጭት፣ አንዴ እርስ በርስ አንዴ አንዱን ከሌለው አንደቀትር የወንዝ መንፈስ እያጋጨች እና እያቃጠለች ማገዶውን እየሞቀችው ነው። ይህ "ስቴፕ ቱ" ዘዴ ግን ተመልሶ ለራሷ ጦር ሆነባትና አሁን ራቁቷን ቆመች።

ሕወሓት በግልጽ እና በአደባባይ ራሷ ያቋቋመችውን ኢህአዴግን ገሸሽ ማድረጓን ተናገረች። በዚህ ድርጅት ውስጥ መቀጠል እንቸገራለን አለች። የትግራይ ህዝብ መገንጠልን አጀንዳ እያደረገ ነው ብላ በራሷ የተመዘዘ ምናልባትም አዲስ ካርታዋን ወደህዝብ ጥያቄ ለመግፋት ስራ ጀመረች። የጠ/ሚ/ር ዐቢይ አስተዳደር ያደረገው ለትርጉም ክፍት የሆኑ ንግግሮች እና የወሰዳቸው ዘር ተኮር የመሰሉ እርምጃዎች ሕወሓት የትግራይን ህዝብ "እኔ ከሌለሁ ጅብ ይበላሃል" ብላ የተረተችለት ተረት እውነት እንደሆነ ለማሳመኛ ተጠቀመችበት። ህዝቡ "ጥላ ድርጅቴ አንቺው ነሽ፣ በአጥንትሽ ይገንዙኝ፣ በስጋሽ ያጅሉኝ" ብሎ ሌላ ድርጅት በክልሉ እንዳይንቀሳቀስ የራሱን ልጆች እስከ መደብደብ ደረሰ።

አዴፓ በበኩሉ ጨዋታው ሲፈርስ እና ዳቦ ሲቆረስም ቢሆን ሕወሓትን የከፋ ንግግር ተናግሯት አያውቅም ነበር። ሕወሓት አንዴ "ጠባብ"፣ አንዴ "የትምክህት ሃይሎች"፣ አንዴ "ምናምን" እያለች ስትዘልፈውና ንቀቷን በአደባባይ ስታሳየው እንኳን ዝም ነበር ያላት። የቀድሞ የትግል አጋሩ፣ በአንድ ጉድጓድ እንቀበር ተባብለው የተማማሉ የበረሃ ጓዱ ፣ ትግራይን ከደርግ ነጻ ለማውጣት አማራው የሞተው፣ አማራውን ነጻ ለማውጣት ትግሬውም የሞተበት ዘመን ወዳጆች ዛሬ የአንድነታቸው ማብቂያ ሆኖ ቀሚስ ተገላልበው ተነጋገሩ። ለውጡ ከመጣ በኋላ አንድ አመት እንኳን በቅጡ ሳይኖሩ ሁለቱ የኢህአዴግ መስራች ድርጅቶች ጨዋታውን አፈረሱት። እስከዶቃቸው ተነጋግረው በመግለጫ ተቀጣቀጡ። እሱን ተከትሎም በየራሳቸው ቴሌቪዥንና ራዲዮ ፕሮፓጋንዳቸውን አጦፉት። ጸባቸው አሁን ሁለት ነገሮች አይቀሬ መሆናቸውን አወጀ። አንድም አዴፓ እና ሕወሓት የደረስኩበት አትድረስ ተባብለው በጸብ ተለያዩ፣ ሲቀጥልም እነሱው ያቆሙት ኢህአዴግ ሊፈርስ በጽኑ መዝመሙ እውነት ሆነ። የሚቀድመው የቱ ይሆን? የፓርቲዎቹ ግልጽ ግጭት ወይስ የኢህአዴግ መፍረስ?

ሕወሓት በግልጽ እና በአደባባይ ራሷ ያቋቋመችውን ኢህአዴግን ገሸሽ ማድረጓን ተናገረች። በዚህ ድርጅት ውስጥ መቀጠል እንቸገራለን አለች። የትግራይ ህዝብ መገንጠልን አጀንዳ እያደረገ ነው ብላ በራሷ የተመዘዘ ምናልባትም አዲስ ካርታዋን ወደህዝብ ጥያቄ ለመግፋት ስራ ጀመረች።

## የመጨረሻው መጀመሪያ

ሕወሓት መግለጫ አወጣች። ይህ መግለጫዋ ከወትሮው መግለጫዎቿ ምን ለየው ቢሉ ሁለት ምክንያቶች ግልጽ ሆነው ይወጣሉ። "እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል" ማለቷ እና "የአማራውን መሪ ፓርቲ አጣጥላ ብሄሩን ለማዳከም መዳዳቷ። ሲጀምር ሕወሓት ከፌዴራሉ ስልጣን ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ ከተነጠለች በኋላ ስራ አስፈጻሚዋም ሆነ ማዕከላዊ ኮሚቴዋን መቀሌ አስቀምጣ ትሰጥ የነበረው መግለጫ "አለሁ፣ ሃገሪቷም ሃገሬ ናት፣ ህዝቡም ህዝቤ ነው" አይነት ይዘት ያለው ከቀደመው ብዙም ያልተለየ ነበር። በመግለጫዋ መልካም ቃላትን እየተናገረች በባለስልጣናቷ አፍ ደግሞ ተንኳሽ ቃላት እየዘራች ቆይታ በዘንድሮው አመታዊ ድርጅታዊ ስብሰባ ያወጣችው መግለጫ ግን በአማራ ክልል በተፈጠረው የአመራሮች ህልፈት የህዝቡን አንድነት እና የክልሉን ጥምረት መላላት በማየት በክፍተቱ ሽብልቅ ለመጠቀም ያሰበች አስመስሏታል። ከዚህ በተጨማሪም ቀድሞ አፍና በያዘችው የደቡብ ህዝቦች ክልል እንሁን ጥያቄ ላይ ደርሶ ቅቤ አንጓች በመሆን "መብታቸው ይከበርላቸው" ስትል መሞገቷ፣ በመላው ሃገሪቱ ሰላም እንደሌለ በማጉላት ህገመንግስቱ ይከበር ማለቷ፣ አወዛጋቢውን የ2012 ምርጫ በማንሳት "ምርጫው በጊዜው ይካሄድ" ብላ መመጻደቋ እና አዲስ አበባ ላይ አብራ አጨብጭባ ያጸደቀችውን የኢህአዴግ ውህደት ሃሳብ ማጣጣሏ የተዘጋጀችባቸውን ተንኮሎች ያሳያሉ ይላሉ መግለጫውን ያጤኑ ወገኖች።

አሳምነው ጽጌን ጨምሮ አምስት ወሳኝ አመራሮቹን በአንድ ጀምበር ያጣው አዴፓ ሆድ በባሰው በዚህ ጊዜ ሕወሓት ያወጣችው መግለጫ የባሰ አቅሉን አስቶት ለከፍተኛ ብስጭት ዳርጎት ታይቷል። "በሰው ቁስል እንጨት ስደድበት" ሆኖብኛል በማለትም ሕወሓትን ከቀደመ ዘመን ሴራዋ እና አማራ ላይ ከነበራት አቋሟ ጭምር ተነስቶ አብጠልጥሏታል። ባልተገባ አማርኛም "ጥንብ እርኩሷን አውጥቶታል" ። በታሪኩ አንዴ እና ለመጀመሪያ ጊዜ በሕወሓት ላይ ዱላ ቀረሽ የሆነ መግለጫ ያወጣው አዴፓ "ሞኝ ካመረረ በግ ከበረረ " እንዲሉ ሆኖ ጉዳዩን አልለቅ ብሎ በመገናኛ ብዙሃኑ ጭምር አጀንዳ በማድረግ የኢትዮጵያን ክልሎች ሁሉ ለመግለጫው ድጋፍ ለማስገኘት ሲዞር ሰንብቷል።

ለመንደርደሪያ ያህል በዚህ ከተነሳን ኢህአዴግን "ለመፍረስ ሩብ ጉዳይ" አድርገው ያዘመሙት የሁለቱ ፓርቲዎች መግለጫዎች ይዘት ምን እንደሚመስል እና የሚያስከትለው ውጤት ምን ሊሆን እንደሚችል ለማየት እንሞክር።

## ተንኳሹ የህወሃት መግለጫ “አዴፓ ትምክህተኛ ነው”

የህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት) ማዕከላዊ ኮሚቴ ያካሄደውን አስቸኳይ ስብሰባ ሃምሌ 3 ቀን 2011 ዓ.ም ሲያጠናቅቅ ማሳረጊያውን በተንኳሽ መግለጫ ነበር ያጀበው:: በዚህ መግለጫው ቀጥታ ጦሩን ወደአዴፓ በመስበቅ ከዚህ ቀደም ሲጠቀምበት የነበረውንና “የአማራውን ህዝብ አንገት ለማስደፋት እና በሌሎች ብሄሮች እንዲጠላ ለማድረግ የፈጠረው ነው” ተብሎ የሚታማበትን “ትምክህተኛ” የሚል ቃል አፈሩን አራግፎ ዳግም ይዞት መጥቷል:: በኢህአዴግ ባህል በሚካሄዱ ግምገማዎች “ትምክህተኝነት” ምህረት አልባ ቅጣት የሚያስከትል ባህሪ ነው:: ኢህአዴግም አምርሬ እታገለዋለሁ የሚለው ቁልፍ ችግር ነው:: ይህንን ደግሞ ሁሉም አባል ድርጅቶች ያውቁታል:: ሕወሓት ግን ዛሬ አዴፓን በግለጽ እና በአደባባይ ከትምክህት ሃይሎች ጋር ደርቦ ወቅጦታል:: የዚህን ቃል ከባድ ተርጉም አሳምሮ የሚያውቀው አዴፓ ደግሞ ስሙ በዚህ መሪር ጸረ ህዝብ ባህሪ ጋር ታክኮ መነሳቱ አንገብግቦታል:: ናላውን በማዞር ባልተጠበቀ መልኩ ምላሽ እንዲሰጥ ያደረገውም ይኸው ነው::

ሕወሓት በመግለጫው፤ “በአሁኑ ጊዜ አገሪቷን ሊበታትን ያለው ከዚህም ከዚያም የተሰባሰበ የትምክህተኞች ቡድን ነው፤ ይህ ኃይል እንደፈለገ እንዲንቀሳቀስ እድል የሰጠው ደግሞ አዴፓ ስለሆነ አዴፓ በአጠቃላይ ስለ ጥፋቱ የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ ይጠይቅ፣ በፓርቲው አመራር ላይ የተፈፀመውን ግድያ በዝርዝር ገምግሞ ራሱን ተጠያቂ ያድርግ” ብሏል::

ሕወሓት በመግለጫው አዴፓን ሲተች “ውስጣዊ ችግሮቹን ከመገምገም ይልቅ በነገሩ የሦስተኛ አካል እጅ አለበት” በማለት ጥፋቱን ለመሸፋፈን እየሞከረ ነው ይለዋል:: “አዴፓ ሕዝቡን ማደናገር ማቆም አለበት” ሲልም አምርሮ ይወነጅለዋል:: “ስለዚህ አዴፓ ውስጣዊ ችግሮቹን ፈትሾ አቋሙን እንዲያሳውቅ እንጠይቃለን” ያለው ሕወሓት ይህንን ሃሳብ ያሳረገው ከዚህ ድርጅት ጋር ከዚህ በኋላ ቁጭ ብዬ አብሬ አልሰራም ከሚል ዓይነት ማስጠንቀቂያ ጋር ነው:: “…[አዴፓ] ይህንን ማድረግ ካልቻለ ግን ሕወሓት ከፓርቲው ጋር ለመሥራትና ለመታገል ይቸገራል “ በማለት ነው በመግለጫው በግልፅ ያስቀመጠው:: “….የውስጥ ችግርን ለመሸፈን ሲባል ጥፋቱ የሦስተኛ አካል እጅ አለበት፣ ረጃጅም እጆች ያሉበት ነው እያሉ ህዝብን ማደናገር ሊቆም ይገባል:: እንዲህ እያሉ መኖር እንደማይቻል ህዝብም ተገንዝቦታል:: ስለዚህም አዴፓ ሁሉንም ውስጣዊ ችግሮቹን በዝርዝር ገምግሞ ግልጽ አቋሙን እንዲያስታውቅ ጥሪ እናቀርባለን:: ይህን ማድረግ ካልቻለ እንዲህ ካለው ኃይል ጋር አብሮ ለመስራትና ለመታገል እንደሚቸገር ሊታወቅ ይገባል::” በማለት በአዴፓ ላይ የያዘውን አቋም አስምሮበታል::

## በሌለ ኢህአዴግ ተስፋ ማድረግ ያለውን መንግስት ማሳጣት

“እስካሁን ድረስ ያጋጠመው መሰረታዊ ችግር በኢህአዴግ ውስጥ በተፈጠረው የአሰላለፍ መደበላለቅና በጠራ ውግንና ላይ የተመሰረተ ትግል እየተተወ፤ ሁሉም ዓይነት ጥገኛ እና ደባል አመለካከቶችን ተሸክሞ የሚኖር ድርጅት እየሆነ በመምጣቱ ነው:: ስለሆነም የሀገራችንን ህልውናና ደህንነት ለማስጠበቅ ኢህአዴግ ወደተለመደውና ወደሚታወቅበት ባህሪና እምነት ተመልሶ፤ ከጎራ መደበላለቅ የጠራና በግልጽ ውግንና ላይ የተመሰረተ ትግል ያካሂድ” ይላል ሕወሓት በመግለጫው:: ሕወሓት እየተፈረካከሰ ባለው ኢህአዴግ ውስጥ ሚና የሌለው ይመስል “ኢህአዴግ እርምጃ ይውሰድ” አይነት ማሳሰቢያም ሰጥቷል በመግለጫው:: “እስካሁን ያጋጠሙ መሰረታዊ ችግሮች በኢህአዴግ ውስጥ የተፈጠረው የአሰላለፍ መደበላለቅና ኢህአዴግ ሁሉንም አይነት ጥገኛ አመለካከቶች ተሸክሞ የሚኖር ድርጅት እየሆነ ስለመጣ ነው:: ቀድሞ ወደሚታወቅበት ባህል ተመልሶ በሕግና በደንቡ መመራት ይገባዋል” ይላል መግለጫው:: ሃገሪቱም ልክ ባልሆነ አመራር ውስጥ መውደቋን እና ባጎረስኩ ተነከስኩ አይነት ብሂል በርሱ ላይ እንደደረሰ ለመናገር የተጠቀመበት አንቀጽ መረር ይላል::

“….ትናንት የሀገራችንን ህልውናና ክብር አሳልፈው የሰጡ፤ የኢትዮጵያን መበታተን እውን ለማድረግ ቀንና ሌሊት አንቀላፍተው የማያውቁ ኃይሎች በለውጥ ስም ግንባር በመፍጠር አሰላለፍ በማይለይ ሁኔታ ሁሉም ተደበላልቆ አንድ ላይ እንዲኖር በመደረጉ፤ በጥፋት ላይ ጥፋት እየተደራረበ እዚህ ደረጃ ላይ ደርሰናል” ነው የሚለው:: “በአንጻሩ ደግሞ፤ ለዚህች ሃገር ክብርና ህልውና ዕድሜ ልካቸውን የታገሉት የሚታደኑበት፣ የሚታሰሩበትና ጥላሸት የሚቀቡበት ሁኔታ ተፈጥሯል” ብሏል::

“…በአሁኑ ወቅት የአገራችንን ህልውና ከመጥፎው ወደ ባሰ ሁኔታ ሊወስድ የሚችል በመጠኑና ስፋቱ እጅጉን አሳሳቢ የሆነ ሁኔታ ላይ ደርሰናል::ሃገር ጠባቂ አጥታ የጽንፈኞች መፈንጫ እየሆነች ፀረ ሕገ-መንግሥትና የፌደራል ሥርዓት የሆኑ ጫፍ የረገጡ የትምክህት ኃይሎች እንደፈለጉ የሚፈነጩበት ሁኔታ ተፈጥሯል” የሚለው መግለጫው በግልጽ አነጋገር የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አስተዳደር ሃገር መምራት አልቻለም የሚል አንደምታ በውስጡ ይዟል::

**በኢህአዴግ ባህል በሚካሄዱ ግምገማዎች “ትምክህተኝነት” ምህረት አልባ ቅጣት የሚያስከትል ባህሪ ነው። ኢህአዴግም አምርሬ እታገለዋለሁ የሚለው ቁልፍ ችግር ነው። ይህንን ደግሞ ሁሉም አባል ድርጅቶች ያውቁታል። ሕወሓት ግን ዛሬ አዴፓን በግለጽ እና በአደባባይ ከትምክህት ሃይሎች ጋር ደርቦ ወቅጦታል**

## የሚሆነውን እያለሙ ምርጫውን መናፈቅ

ሕወሓት የ2012 ምርጫ እንዲካሄድ በጽኑ ይፈልጋል:: ብዙዎች እንደሚሉት ይህንን የሚፈልግበት ምክንያትም ምርጫው በሰላም እና በተረጋጋ ሁኔታ ሊካሄድበት የሚችልበት ዕድል ጠባብ በመሆኑ የመራዘም ሁኔታው እያደላ መምጣቱን በመገንዘቡ ነው:: ይህ ምርጫ አሁን ተካሄደ ማለት ሊፈጥር የሚችለው ቀውስ ከፍ ስለሚል ውሳኔ ላይ ከመድረስ በፊት መንግስት እያሰበበት ስለመሆኑ ማሳያ አለ:: ሕወሓት ግን ይህንን ቅርቃር በኢህአዴግ ላይ በማላከክ ምርጫው ካልተካሄደ ህገመንግስቱ ተጥሷል ብሎ ለመቃወም እና ሰበብ ፈልጎ ከፓርቲው ለመገንጠል ሲል ጥየቄ አንስቷል ተብሏል:: “ኢህአዴግ እንደ ግንባርም ሆነ እንደ መንግሥት በቀጣዩ ዓመት መደረግ ስላለበት አገራዊ ምርጫ ያለውን ቁርጥ ያለ አቋም ያሳውቅ” ይላል መግለጫው::

## ግልፍተኛው የአዴፓ መግለጫ “የተጫረ ክብሪት”

አዴፓ ከኢህዴንነት ዘመኑ ግማሹን ፣ ብአዴን ሆኖ ሲኖርም ሙሉውን ዕድሜውን በሕወሓት ቁጥጥር ስር የኖረ ፓርቲ ነው::

► አዴፓ ሲሆንም ለአንድ አመት ያህል የዘመናት አለቃውም ሲናገር አቅም አልነበረውም። ነገር ግን በህልውናው ላይ ድንገት የመጣችበትን ሕወሓትን ቀሚስ ገልቦ ጥግ ድረስ በስድብ ሲያስታጥቃት ቀድማው አብሬው አልሰራም ብትልም እርሱም መለያየቱን በቃሉ ያጸና አስመስሎታል።የአዴፓ ቁጣ ለረጅም ጊዜ ሲወጣ ሲገባ ቆይቶ ድንገት እንደተጫረ ክብሪት ቦግ ብሏል። በአመራሮቹ መገደል ጨው ካስመሰለው ድንጋጤው ሳያገግም የሕወሓት ዱላ የተሰነዘረበት አዴፓ የሚይዘው የሚጨብጠውን ያጣው ያለፈ ዘመን ብሶቱ አንገፍግፎት እንደሆነም ብዙዎች ይገምታሉ።

”...በከፍተኛ አመራሮቻችን ላይ በተፈፀመው የግፍ ግድያ ምክንያት የማዕከላዊ ኮሚቴያችን በወቅታዊ ጉዳይ እና ቀጣይ የትግል አቅጣጫዎች ግምገማ ለማድረግ ሐምሌ 4 ቀን 2011 ዓ.ም እየመከረ ባለበት፣ የአማራ ህዝብና የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ከጥልቅ ሃዘናችን ባልተላቀቅንበት በዚህ ነባራዊና ህሊናዊ ሁኔታ ውስጥ ሆነን “በሰው ቁስል እንጨት ቢሰዱበት” እንዲሉ፣ የትህነግ/ሕወሓት ማዕከላዊ ኮሚቴ ሐምሌ 3 ቀን 2011 ዓ.ም ባወጣው መግለጫ የትህነግ/ሕወሓትን የነበረና እየቀጠለ ያለ አሳፋሪ የሴራ ፖለቲካ እርቃኑን በአደባባይ ያጋለጠ የአቋም መግለጫ አውጥቷል” በማለት ሕወሓትን ይከስሳል አዴፓ።

## “ህወሃት ገርፎ ጪሂ ፓርቲ ነው”

አዴፓ ሕወሓትን “አገራችን አሁን ለምትገኝበት የፖለቲካ ብልሽት ዋና ተጠያቂ” ይለዋል። በቀደመ የአማርኛ ስሙ ሕወሓትን ትህነግ ብሎ መጥራት የቀናው አዴፓ “....የትህነግ/ሕወሓት መግለጫ ከሐዘን ባልወጣንበት ሁኔታ ከአንድ እህት ፓርቲ የማይጠበቅ አሳፋሪ ድርጊት ነው” ይላል። “እራሱ ነካሽ፣ እራሱ ከሳሽ” ብሎ በሚያጣጥለው ህወሃትን የሚነቅፍ መግለጫው ድርጅቱን በፀረ-ለውጥ እንቅስቃሴው አገራዊና ክልላዊ ለውጡ በጥርጣሬ እንዲታይ ከጥፋት ሃይሎች ጀርባ መሽጐ አመራር እየሰጠ ነው” ብሎም በግልጽ ይከስሰዋል።

“’ሕወሓት የዘመናት አስመሳይነቱን ያጋለጠ፣ እራሱን ብቸኛ የኢትዮጵያ ጠበቃ አስመስሎ መቅረቡ የሞራል እና የተግባር ብቃት የሌለው ድርጅት መሆኑ የሚታወቅ ነው።” በማለትም አብጠልጥሎታል።

“... ወቅታዊ ጉዳታችንን እንደ ዘላቂ ሽንፈትና ውድቀት በመቁጠር፣ ዛሬም የአማራን ህዝብ አንገት ለማስደፋት “የተቀበረውን የትምክህት ትርክቱን ዳግም ይዞ ብቅ ማለቱ ድርጅቱ መቼም ቢሆን መፈወስ የማይችል በሽታ ያለበት መሆኑን ያጋለጠ ተግባር ነው” ይለዋል። “ በፅናት የሚታገሉትንና ከኔ ጎን አይሰለፉም የሚላቸውን ኃይሎች ሲሻው ትምክህተኛ፣ ሲሻው ጠባብና አሸባሪ በማለት ታርጋ እየለጠፈ የሚያሸማቅቅ ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ድርጅት መሆኑ መላ የኢትዮጵያ ህዝብ ያውቀዋል። በመሆኑም የትህነግ/ሕወሓት መግለጫ አዲስ ነገር ይዞ የመጣ ሣይሆን የተለመደ ፖለቲካዊ ሴራ ማሳያ ነው። ” በማለትም ይደመድማል።

## ተገንጣይ ድርጅት ?

አዴፓ ሕወሓትን የመገንጠል ፍላጎት ያለው እና ለዚህም ሲሰራ የኖረ ድርጅት መሆኑን በመግለጫው ጠቆም ሲያደርግ” ትህነግ/ህወሓት ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ የሁለት አገረ-መንግስት እይታ ያለው፣ አንድም ቀን ለህዝቦች አንድነት የማይጨነቅ...” ብሎታል። “የኾሮዋኾሮዌ ፖለቲካን” የሙጥኝ ያለ እምነት የማይጣልበት ድርጅት ነው” ሲልም ተሳልቆበታል። ራሱን ሲያንቆለጳጽስም “...የአማራ ህዝብና ድርጅታችን አዴፓ ሆን ተብሎ የተበላሸውን አገራዊ ፖለቲካዊ ሁኔታችን እንዲታረም፣ ከሌሎች የለውጥ ሃይሎች ጋር ሆኖ ፊት ለፊት የተፋለመና የለውጡን ውጤቶች ጠብቆ ለመዝለቅ ሌት ከቀን የሚታትር ድርጅት እንጂ እንደ ትህነግ/ሕወሓት በከፋፋይት በሽታ የተጠመደ ድርጅት አይደለም” ይላል።

## “እንኳን ዘንቦብሽ”

አዴፓ ሕወሓት አብሮት ለመስራት እንደሚቸገር ያወጣውን መግለጫ በመንተራስ የሰጠው የመልስ ምት “እንኳን እናቴ ሞታ እንዲሁም አልቅስ አልቅስ ይለኛል” እንዳለው ሰውዬ አይነት ነው። “... ድርጅታችን አዴፓ በኢህአዴግ ግንባር ውስጥ ከትህነግ/ሕወሓት ጋር አብሮ እየታገለ መቆየቱን የመረጠው ለትግራይ ህዝብ ካለን ክብር እንዲሁም ትህነግ/ሕወሓትም እራሱ ተፀፅቶ እራሱን ያርማል በሚል ተስፋ ቢሆንም ትህነግ/ሕወሓት በነበረበት ተቸክሎ የሚዳክር ድርጅት በመሆኑ ድርጅታችን አዴፓን ይቅርታ ይጠይቅ” ብሏል።


## ኩንታል ሙሉ ስድብ

አዴፓ ሕወሓትን “ ከብልሹ ፖለቲካ የማይፈወስ ድርጅት” ፣ “ የህዝባችን የጉን ውጋት”፣ “ እኩይ ወንጀለኛ”፣ “በተንኮሎች የተጠመደ” ፣ “ የማይማር እና የማይድን” ፣ “በእብሪተኝነት የተወጠረ” “በሬ ወለደ አሉባልተኛ”፣ “ ተንኳሽ እና ጦር ሰባቂ” በሚሉ ቃላት በኩንታል ሙሉ ስድብ “ልክ ልክ” ነግሮታል። ሙሉ መግለጫውን በህወሃት ላይ ያደረገው አዴፓ ማሳረጊያውንም “በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የትህነግ/ሕወሓትን የፖለቲካ ደባ የምታስፈፅሙ ተላላኪ የፖለቲካ ሃይሎችና ቡድኖች ከዕኩይ ድርጊታችሁ ተቆጠቡ” በማለት ዘግቶታል።

## ኢህአዴግ ዘምሟል

ብዙዎች በሚሰጡት አስተያየት እነዚህ ሁለት የድርጅቱ ዐዕማድ የሆኑ እህትማማች ፓርቲዎች በመጣላታቸው ብቻ ኢህአዴግ ለመፍረስ ዘምሟል። ድርጅቱ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ውሁድ ፓርቲ ለመሆን ጉዞ መጀመሩ መገለጹ እንዳለ ሆኖ ፣ አሁን መስራቾቹ ሲወላልቁ መሰረቱ መናጋቱ አይቀሬ ነው። በኢሃን ፓርቲ ሊቀመንበር የሆኑት ኢንጂነር ይልቃል እንደሚናገሩት “የኢህአዴግ ፓርቲዎች ዞሮ ዞሮ እየተዳከሙ ይሄዳሉ። በአገር ደረጃም ጉዳት ካደረሱ በኂላ ግን መፈራረሳቸው አይቀርም። ሽኩቻውና መነታረኩ ይቀጥላል። ከሕዝብ ጥያቄ ጋር ተዳምሮ የኢህአዴግ ፍጻሜ ይሆናል” ይላሉ። በርግጥ ኢህአዴግ መዘመሙ እውነት ነው። ይፈርሳል ወይስ ይታደሳል? የሚለው ግን የዞረ ጥያቄ ሆኖ ይቆየን።

> ”...በከፍተኛ አመራሮቻችን ላይ በተፈፀመው የግፍ ግድያ ምክንያት የማዕከላዊ ኮሚቴያችን በወቅታዊ ጉዳይ እና ቀጣይ የትግል አቅጣጫዎች ግምገማ ለማድረግ ሐምሌ 4 ቀን 2011 ዓ.ም እየመከረ ባለበት፣ የአማራ ህዝብና የኢትዮጵያ ብሄር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ከጥልቅ ሃዘናችን ባልተላቀቅንበት በዚህ ነባራዊና ህሊናዊ ሁኔታ ውስጥ ሆነን “በሰው ቁስል እንጨት ቢሰዱበት”



ጌኖክ ገለታው

# ኢትዮጵያዊነት በዘመናት ተለውጦ

"ኢትዮጵያ ነበረች ፤ አለች ፤ ትኖራለችም " ይህ መቼም ከአልቦ አመክንዮ የሚመነጭ ተራ ፉከራ ሆኖ በአንድ ወገን መደመጡ አይቀርም። ዘመን አሁንም ፊቱን ያዞረ ይመስላል። የጊዜው ተደማጭ ትርክት ከሀቅ የሚቀዳው ኢትዮጵያዊ እውነት ሳይሆን አታግሎ መንበር ለመቆናጠጥ የሚነዛው የጎሣ ማኒፌስቶ ሆኗል። ጉድ ሳንሰማ በማናድርባት የዛሬዋ ኢትዮጵያ ለዚህ አስረጅ አቅርብ የሚለኝ ካለ አቶ ሌንጮ ባቲን ሹክ ብዬ ባልፍ ኩነኔ አይሆንብኝም። ኢትዮጵያ በሥም ኖራ ለጊዜው በግብር ብትሸነፍም ፤ ኢትዮጵያዊ ብሔረተኞች ግን ያለፈውን ሩብ ክፍለ ዘመን የተነጠቅነውን የትርክት የበላይነት መልሰን ለመቆናጠጥ ዛሬም አቅማችንን እያሟጠጥን አይመስልም። ለዚህ ደግሞ ከፖለቲካዊ የተዋስዖ መድረኮች አንስቶ እስከ መገናኛ ብዙኃን ሽፋን ድረስ ትልቁ የኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት መልክ አንድም ተገፍቶ፣ ሲሻም ጎድፎ፣ ሲቀጥልም ኮስሶ እንዲታይ ስለፈቀድን ነው። ይህን መንደርደሪያ ስናጠቃልል የእምዬ ምኒልክ በርጩማ ታደሰልኝ ብሎ የኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነት ትጉሉን በ"ሩጫዬን ጨርሻለሁ" ስሜት ከገታው ስፍር ቁጥር ከሌለው ኃይላችን ጋር ብዙ መነጋገር ያስፈልገናል፤ በደንብ።

ለጊዜው ግን ኢትዮጵያ ከነሙሉ ክብሯ እንድትቀጥል የሞራልም ሆነ የታሪክ ኃላፊነት ለወደቀብን ኢትዮጵያዊ ብሔርተኞች "… ከታሪካችን በወረስናቸው የተዛቡ ግኑኝነቶች" ብሎ መቅድሙን ለሚያረዳን የቁጩ ሕገመንግሥት ነገረፈጅ ሆኖ አንቀጽ ለማረም እየጎፈነነው ላለው የዛሬው መንግሥት፤ የዳግማዊ አጤ ቴዎድሮስ ዜና ከታቢ አለቃ ዘነብ በ"መጽሐፈ ጨዋታ ሥጋዊ ወመንፈሳዊ" መጽሐፋቸው ሦስተኛ ገጽ ያሰፈሩትን አስቀምጠን እኛም ይህን ገጽ እንጠፍ። "ሕዝብና ሕዝብ ደጋና ቆላ ናቸው። ንጉሡ ግን ገበያ ነው ፤ሁሉን ያገናኛልና። ሽክላ ከተሰበረ በኋላ ገል ነው፤ መኳንንትም ከተሻሩ በኋላ ሕዝብ ናቸው"

## እንደ መሸጋገሪያ

ከዚህ ቀደም በዚችው "ግዮን" መጽሔት "ነገረ ኢትዮጵያዊነት" እና "የኢትዮጵያዊ ብሔረተኝነት ካስማዎች" በሚሉ ርዕሶች በተመሳሳይ የይዘት አምድ(Category) ሊቀመጡ የሚችሉ ኢትዮጵያዊ አጀንዳዎችን ጽፌ ነበር። ይህ የዛሬው አጭር ጦማር ደግሞ ከተጠቀሱት ኢትዮጵያዊ አጀንዳዎች ጋር ተሰናስሎ የሚታይ ሌላ መልክ ነው። ርዕሱን "ኢትዮጵያዊነት በዘመናት ተላውጦ" በሚል ለመሰየም የተገደድሁትም በ"ብሔር ፤ ብሔረሰብ" ሀቲት በምትታመሰው የዛሬዋ ኢትዮጵያ "ነገርን ከሥሩ ውኃን ከጥሩ" እንዲሉ የጭቆናና የበደል ትርክት የተጣባው የሃምሳ ዓመቱ የማርክሲስት ፖለቲካ የጦስ ዶሮ ባደረጋቸው "ብሔር ብሔረሰቦች" ውስጥ ኢትዮጵያዊ ማንነት የነበረውን ውድ ቦታና የተከፈለለትን ክቡር ዋጋ በአጭሩ ለማሳየት ነው። ለዚህ አጭር ጽሑፍ የመረጃ ምንጭ አድርጌ የተጠቀምሁት የዶክተር ላጺሶ ጌ.ድሌቦ "የኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም" የተሰኘውንና በ1983 ዓ.ም የታተመውን ሥራ ነው (በነገሬ ላይ በ"ደጉ" ዘመን የእኚሁ ምሁር ተማሪ የነበረ አንድ ወዳጄ "ለመሆኑ ዶክተር ስምዎት ላይ ላጺሶ ጌ.ድሌቦ ብለው "ጌ"ን በአህጽሮት ለመጠቀም የፈለጉት ለምን ይሆን?" ብሎ ላቀረበላቸው ጥያቄ "ጌ" ማለት "ጌታነህ" መሆኑን ገልጸው "መሬቴ ተወስዶ፣ ሃብቴ ተቀምቶ የባላባት ርስት በሆነበት ጌታነህ ብዬ መጠራት በራሴ ላይ የመሳለቅ ያህል ስለሆነብኝ ነው" ብለው እንደመለሱለት የነገረኝ ታሪክ አግራሞትን እንደጫረብኝ ዛሬም አለ)

## አደሬዎችና ሱማሌዎች

ታሪክን አጣሞ ፤ ሲያሻም ፈልስሞ እርባና ለሌለው የጎሣ ፖለቲካ ጭዳ የማድረግ ዘልማድ እግሩን ካሳረፈባቸው የሀገራችን አካባቢዎች በምስራቅ የሚገኙት አደሬና ሶማሌ ይጠቀሳሉ። የጭቆናና የተበዳይነት ትርክቱ በተጠቀሱት ቦታዎች በዘመናት ተላውጦዎች ውስጥ ለኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት የተከፈሉ ክቡር መስዋዕትነቶችን ከመጋረዱም በላይ የመነጠልና የተገንጣይነት መንፈሶች የረበቡበት ከባቢ አድርጎ በመሳል ኢትዮጵያዊ መልኩ እንዲደበዝዝ ሆነ ተብሎ ተሰርቷል።

ቅድመ ዘመነ መሣፍንት (መካከለኛው የኢትዮጵያ ታሪክ) የአደሬና እስከ ሞቃዲሾ ጫፍ የሚደርሰው የሱማሌ ሕዝብ የኢትዮጵያው ንጉሠ ነገሥት የግዛት አካል ሆኖ የኖረበት በርካታ የታሪክ ማስረጃዎች ባሉበት ፤ በዘመናዊው የኢትዮጵያ መልሶ አንድ የመሆን (Reunification) ሂደት ውስጥ ከግብጾች የአሥር ዓመታት ቅፍደዳ (Annexation) በኋላ ተረኛዋ ፈረንሳይ ከጅቡቲ ተስፈንጥራ ሐረርን ለመያዝ ሁለቴ ባላሰበችበት የታሪክ አጋጣሚ ውስጥ፤ የሸዋው ንጉሥ ምኒልክ ጦር ገስግሶ ወደ ግዛቱ መቀላቀሉ "ሲፋጅ በማንኪያ፣ ሲበርድ በእጅ" ሆነና የጎሣ ፖለቲከኞችና ልሂቃን የሙሿቸው አሜጋ ሆኖ ቀጥሏል። በዚህ የታሪክ አጋጣሚዎችን ለፖለቲካ ጥቅም የማዋል(Making politicize) መጥፎ ልማድ መነሻነት ታሪካዊቷ የሐረር ከተማ በመልሶ አንድ መሆን(Reunification) የኢትዮጵያ መንግሥት የግዛት አካል መሆን "ጨለንቆ" የተባለውንና በሸዋው ንጉሥ በኩል ሰባ አምስት በመቶ የሸዋና ጅማ ኦሮሞ ዘማች ፤ በሐረሩ አሚር አብዱላሂ በኩል ደግሞ የአደሬ ተወላጆች የተሳተፉበትን ውጊያ አንድን ዘር የማሳሳት (Ethnic Cleaning) አድርጎ ከማቅረብም በዘለለ "አስከፊ የብሔር ጭቆና" የተተከለበት መጥፎ የታሪክ ምዕራፍ አድርጎ በመሳል ረገድ ተስተካካይ አይገኝለትም። እውነትን ገልጦ ከመመርመር ይልቅ የተነገረውን እንደ በቀቀን ለማስተጋባት ቁጥሩ ቀላል ባልሆነ ትውልድ ውስጥ ኩሸታቸው የደነደነ ቢመስልም ሀቁ የታሪክ በር ሲከፈት ግን የምናየው ተቃራኒ መሆኑን ሳይሰለቹ መንገር ፤ ሳይታክቱ መጮህ ያስፈልጋል።

ከፍ ባለው መሸጋገሪያዬ የዛሬው አጭር ጦማሬ የመረጃ ምንጭ የሆኑት ዶክተር ላጺሶ ጌ.ድሌቦ "በኢትዮጵያ የገባር ሥርዓትና ጅምር ካፒታሊዝም" በተሰኘው ሁለተኛ የታሪክ ምርምር ሥራቸው፤ በ1879 ዓ.ም ከጨለንቆ ጦርነት በኋላ በንጉሥ ምኒልክና በአደሬ የሀገር ሽማግሌዎች መካከል በተደረገው ስምምነት የብሔረሰቡ ሃይማኖት፣ ቋንቋ፣ ሕግና ባህልን በሚመለከት እስከ ሁለተኛው የኢጣልያ ወረራ ዘመን ድረስ አደሬዎች በማዕከላዊ መንግሥቱ ሥር የውስጥ አስተዳደር ሥልጣን እንደነበራቸው ይተርካሉ። እስከ ተጠቀሰው የኢጣልያ ወረራ ድረስም ሐጂ የሱፍ ባርከሌ፣ ሐጂ አብደላህ አሊሰዲቅ፣ ቀኛዝማች ሐጂ አሕመድ አቦንና የመሳሰሉት የአደሬ ተወላጅ የመንግሥት ሹሞች ነበሩ።

በሌላ በኩል ከ1917-1927 የኢትዮጵያ መንግሥት በአዲስ አበባና በክፍለ ሃገር ከተሞች የውጪ ሀገር መምህራንና ዘመናዊ ትምህርትን በፈረንሳይኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የሚያስተምሩ ከሃያ በላይ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሰራበት ወቅት፤ አደሬዎች በሐረር የራሳቸውን ልማት ማኀበር አቋቁመው በፕሮግራማቸው መሠረት በ1921ዓ.ም የራሳቸውን ዘመናዊ "የሐረር ሙስሊም ት/ቤት" አቋቁመው ለወጣቶች በአማርኛ፣ አረብኛና እንግሊዝኛ ዘመናዊ ትምህርት ማስተማር እንደጀመሩ የትምህርት ቤቱ የመጀመርያ ምሩቃን አንዱ የነበሩትና በ1980ዎቹ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ከፍተኛ ጉባዔ ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበር ሐጂ ኢብራሂም አብዱሰላም ለመጽሐፉ ደራሲ ዶክተር ላጺሶ መናገራቸው ተጠቅሷል።

ይህ እንግዲህ ከዚህ ቀደም በጻፍሁት ጦማር ላይ ሩሲያዊው አሳሽ አሌክሳንደር ቡላቶቪች ኢትዮጵያውያን ግዛት በማዋሀድና በማስገበር ውስጥ "ውጠት" (Assimilation) ፈጽሞ ባህሪያቸው እንዳልሆነና ውስጣዊ ነጻነትን መስጠት ሁነኛው ከአውሮውያን መለያቸው ስለመሆኑ የገለጸበትን ዓውድ እንድናስታውስ ይገፋናል።

የፋሽስት ኢጣሊያ የአምስት ዓመታት የወረራ ▶

ቆይታ ታዲያ በዘረኛና ከፋፋይ ፕሮፓጋንዳ ምክንያት በኢትዮጵያና ኢትዮጵያውያን ማኅበረ ፖለቲካዊ ስሪት(Landscape) ላይ ቀላል የማይባል ጉዳት አስከትሏል። ይህ ከንቱ የኢጣሊያ ነጣጣይና ከፋፋይ ቄሳራዊ መርዝ በተንኮለኛዋ እንግሊዝም ተሞክሮ መክሸፉን የምንረዳው ደግሞ ተከታዩን ደማቅ ታሪክ ስንመለከት ነው።

በመጋቢት 1933 ዓ.ም በጀነራል ካኒንግሀም አዛዥነት በኬንያ ደቡብ ግንባር ወደ ኢትዮጵያ የገባው የእንግሊዝ ጦር የሐረር ከተማን ከፋሽስቶች ከወሰደ በኋላ የእንግሊዝ ጦር ባለሥልጣኖች የአደሬ ብሔረሰብ ተጠሪዎችን ሰብስበው እንዲህ የሚል ጥያቄ አቀረቡላቸው "ከኢትዮጵያ ተለይታችሁ በእንግሊዝ ድጋፍ የራሳችሁን ነጻ ሀገር ለማቋቋም ትፈልጋላችሁ ወይ?" የአደሬ ሕዝብ በውል ያልተነገረው ደማቅና ታሪካዊ ምላሽ ግን "እኛ ኢትዮጵያውያን ስለሆንን በኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማና ንጉሥ ላይ የውጭ ድጋፍ አንፈልግም" የሚል ነበር። (ገጽ 155)

ይህ በእንዲህ እንዳለ ሆኖ ጠላት ከሀገራችን ከወጣ በኋላ በእንግሊዝ ጦር ባለሥልጣኖች በሚተዳደረው ሶማሊያ(የሞቃዲሾው) በሚያዝያ 27 ቀን 1935 የሀገሩ ዜጎች "የሶማሌ ወጣቶች ክበብ" የሚል ማኅበር አቋቁመው፣ " ከኢትዮጵያ ጋር አንድ ለመሆን እንፈልጋለን " በማለት ለእንግሊዙ ዋና አስተዳዳሪ ዊክሃም ጥያቄ አቀረቡ። አጼ ኃይለሥላሴንም "ንጉሣችን" ናቸው በማለት ተናገሩ። በተጨማሪም በወቅቱ ለኢትዮጵያና ሶማሊያ አንድነት የሚታገል፣ በሱማሌ ተወላጁ ኡመር ኢብራሂም መሪነት "የኢትዮጵያና ሶማሌ አንድነት ማኅበር" ተቋቁሞ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ትግል ያካሂድ ነበር። ይህ ማኅበር "የሶማሌዎች ጩኸት" በሚል ርዕስ፣ በ1939 ዓ.ም በፓሪስ ከተማ በቀድሞ የኢጣልያ ቅኝ ግዛቶች ሊቢያና ኤርትራ ጉዳይ ለተሰበሰበው የመንግሥታቱ ማኅበር ያቀረበው የአቤቱታ ደብዳቤ ታሪካዊ በመሆኑ እዚህ ጋር መጠቀሱ ጠቃሚ ነው የሚል እምነት አለኝ። የደብዳቤው ቃል፡-

*"እኛ የኢጣልያ ሶማሊያ ይባል የነበረው ሱማሌ ተወላጆች ስለ ሰላምና ስለዓለም ሕዝቦች ነጻነት በፓሪስ ከተማ በጉባኤ ላላችሁ ባለቃልኪዳን መንግሥታት ከእናት ሀገራችን ጋር አንድ እንድንሆን ቁርጥ ሀሳባችን መሆኑን እየገለጽን፣ የሀገራችን ዕድል እስከ አንድ ዓመት ድረስ እንዲቆይ የቀረበውን ሀሳብ በፍጹም የማንቀበለው መሆናችንን በማክበር እናመለክታለን። በዘር፣በልማድ፣በባህል፣በታሪክ፤ በሀዘን በደስታ ኢትዮጵያውያን ነን። እናት እያለችን ሞግዚት ልንቀበል አንችልም። ጉባዔው ሳይመለስ የኢጣሊያ ይባል የነበረው ሱማሌ ከእናቱ ከኢትዮጵያ ጋር አንድነትን እንዲያገኝ እንጠይቃለን።"*

*ፊርማ፤ የኢትዮጵያና የሶማሌ አንድነት ማኅበር ፕሬዚዳንት*

*ኡመር ኢብራሂም (ገጽ 158) የሚል ነበር።*

ይህ ብቻ ሳይሆን በወቅቱ ተቀማጭነታቸውን በአዲስ አበባ ያደረጉ የኢትዮጵያና የኤርትራ አንድነት ማኅበር፣የኢትዮጵያና የሶማሌ አንድነት ማኅበራት ለፓሪሱ የመንግሥታቱ ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ ያቀረቧቸው የ"አንድ እንሁን" አቤቱታዎች ቃል በተጠቀሰው መጽሐፍ ሰፍሮ መገኘቱን ስናጤን "ኢትዮጵያዊነት" ብዙ የተከፈለበት ውድና እጹብ ማንነት መሆኑ ላይ መግባባት እንድንፈጥር ይገደናል። የምስራቁ የሀገራችን ክፍል የዘመናት የኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት የተጋድሎ አውድማነቱ ተጋርዶ፣በእርባና ቢሱ የጎሣ ፖለቲካ ምክንያት በተዋስያዋችን መድረክ ኮስሶ የመነጠል ትርክት ማስፈራሪያ መሆኑን ዛሬ ላይ ልብ ስንል አሳዛኝ ቁጭት ላይ መውደቃችን ባህሪያዊ ነው።

## የጌዲዮ ሕዝብ

ከጌዲዮ የትውፊት ባለሙያዎች እና የሀገር ሽማግሌዎች በተገኘ የታሪክ መረጃ መሠረት በምንሊክ ዘመን በኢትዮጵያ ማዕከላዊው የአጼ መንግሥት ሥር ከመሆኑ በፊት በውጪ ሰዎች "ደራሳ" ተብሎ የሚጠራው የጌዲዮ ሕዝብ፤ የራሱ የሆነ "ገዳ" የሚባል ባህልና ሕዝባዊ የአስተዳደር ሥርዓት እንደነበረው ላጺሶ በመጽሐፋቸው ይገልጻሉ። ከ1882-1887 ዓ.ም የጌድዮ ሕዝብ በጦርነት ከተሸነፈ በኋላ በማኅበረሰቡ የበላይ ሶንጎ ውሳኔ በሉባ ሹንዶ ካሮ በተመራ የተወካዮች ቡድን

> **"ሕዝብና ሕዝብ ደጋና ቆላ ናቸው። ንጉሡ ግን ገቢያ ነው ፤ሁሉን ያገናኛልና። ሸክላ ከተሰበረ በኋላ ገል ነው፤ መኳንንትም ከተሻሩ በኋላ ሕዝብ ናቸው"**

አማካኝነት ለኢትዮጵያ መንግሥት እንደራሴ ለደጃዝማች ልዑልሰገድ አጥናፍ ሰገድ በሥነ ስርዓት ገበረ። ከዚያም በ1890ዎቹ አዲሱ የሲዳሞ ገዥ ደጃዝማች ባልቻ አባነፍሶ "የቤት አሽከር" የተባለ የግል ጦራቸውን ይዘው የአስተዳደር መዋቅር በመዘርጋት ለወታደሮቻቸውና አብረዋቸው ለዘመቱት በጋሻ ቀላድ መሬት እያስለኩ ከነጻ ገባር ጋር ማደል ጀመሩ። ነገር ግን ከዚህ የደጃች ባልቻ የመሬት ፖሊሲ ጋር የጌዲዮ ሕዝብ መሪዎችና ተወካዮች ሳይስማሙ ቀሩ። በመሆኑም በአቶ ዶሪ መሪነት አንድ የመልዕክተኛ ቡድን አዲስአበባ ወደ አጼ ምኒልክ ተልኮ "በሀገራችን የውጭ ሰፋፊ ሳይገባና በመሬታችንም የጋሻ ቀልድ ሳይጣል የሚፈለግብንን ግብርና አገልግሎት ለማዕከላዊው መንግሥት እኛ ራሳችን በቀጥታ እየሰጠን እንድንኖር ይፈቀድልን" በማለት በአገሩ ሥም አቤቱታውን ለንጉሡ አቀረበ። በአቤቱታውም መሠረት በንጉሡ ተፈቀደላቸው (በሰነድ ተደግፏል)። ይሁን እንጂ ደጃች ባልቻ በምንሊክ ትዕዛዝ መሠረት ለጌዲዮ ሕዝብ መሬታቸውን ሳይመልሱ በሚያዝያ 1900 ዓ.ም ወደ ሀረርጌ በሹመት መዛወራቸውን እናነባለን።

በዚህ አጋጣሚ በዘመናዊት ኢትዮጵያ ሀገር የማቅናት ታሪክ ውስጥ አካባቢያዊ ባላባቶች ከማዕከላዊው መንግሥት ፍላጎት በተጻራሪ ምን ያህል የራሳቸውን ምኞት ብቻ ገቢራዊ ያደርጉ እንደነበር እንድናምን ያስገድደናል። በአንድ ወቅት ነፍሳቸውን ይማርና ሥመ መልካሙ የጋሞው ኢትዮጵያዊ አሰፋ ጫቦ "በእኛ አካባቢ እኔ የማውቀው የኦሮሞ ነፍጠኛን ብቻ ነው" ማለታቸው ከዘመናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ በስማ በለው ሳይፈተሽ የታለፈው እንቆቅልሽ ብዙ እንደሆነ ይነግረናል። የሆነው ሆኖ በዚህ የጌዲዮ ሕዝብ "በምንሊክ ውሳኔ መሠረት መሬታችን ይመለስልን" ጥያቄ መሠረት ትግሉ ምንሊክ ካለፉ በኋላም ሆነ ሀገረ ገዢዎቹ በተለዋወጡ ማግስት ጠንክሮ ቀጠለ። በሂደቱ የጌዲዮ ሕዝብ ተወካይ አቶ ዶሪን የተኳቸው ባላባቱ ጭምቡሮ ሹንዶ አስገራሚ ታሪክ ደግሞ የሚከተለው ነው።

ጭምቡሮ ሹንዶ በደጃች ባልቻ ምትክ ሀገረ ገዥ የሆኑት ራስ ብሩ ወልደገብርኤል ዘንድ ደጋግመው በምንሊክ ውሳኔ መሠረት መሬታቸው እንዲመለስ ሕዝቡን አስተባብረው መጠየቃቸውን ቀጠሉ። በዚህም የተነሳ የጌዲዮ ተሚጋቹ ባላባት ጭምቡሮ ሹንዶ በራስ ወልደገብርኤል ውሣኔ በአገረ ሰላም ከተማ፣ በአደባባይ አርባ ጅራፍ ቅጣት ተቀጥቶ ከአዲስ አበባ በመጣ ትዕዛዝ እስኪፈታ ድረስ በወህኒ ቤት ታሠረ። ይህ የጌዲዮ ባላባት ጭምቡሮ ሹንዶ ምንም ያህል ግርፊያና እስር ከአካባቢው ገዥዎች ቢደርስበትም በሀገር ላይ የሚያኮርፍ ሥነልቦና እንዳልነበረው የምንረዳው ግን ማዕከላዊ መንግሥቱ ላይ የነበረውን እምነትና ፍቅር ስንረዳ ነው። ለዚህ ደግሞ በ1909 ዓ.ም ሰገሌ ላይ በአጼ ኃይለሥላሴና በንጉሥ ሚካዔል መካከል በተደረገው ውጊያና በ1928 ዓ.ም ከፋሽስቶች ጋር በዶሎ ሲዳሞ በነበረው ጦርነት በራሱ ስንቅና ጦር ለኢትዮጵያ ብሔራዊ አንድነትና ነጻነት በግንባር ተሰልፎ እስከ መጨረሻ መዋጋቱን ስናነብ ነው። ጭምቡሮ ሹንዶ ከጦርነቱ መልስ ግን "የመሬት ይመለስልን" ጥያቄውን ከፍ አድርጎ መታገሉ "ሀገር" የተባለችው ቁምነገር ትልቅ ጉዳዩ መሆኗን ከየትኛውም ሕብረተሰባዊም ሆነ መደባዊ ጥያቄ ጋር ቀላቅሎ አለመመልከቱን በማጤን ነው። እንደ ጭምቡሮ ሹንዶ ዓይነት የውስጥ ጉዳይን ከሀገር ብሔራዊ አንድነትና ሉዓላዊነት ጋር ሳይቀላቅል መመልከት የቻለን ጀግና የታሪካችን አብሪ ምልክት ሳናደርግ መቆየታችን የሚያስቆጭ ቢሆንም፤ እርሱና አብረውት በራሳቸው ስንቅና ጦር ለሀገር አንድነትና ነጻነት መስዋዕት የሆኑ የጌዲዮ ጀግኖችን ባሰብን ቁጥር ግን "ኢትዮጵያዊ" መስመራችን ሁሌም ልክ እንደሆነ መተማመኛ ይሆነናል።

ኢትዮጵያዊነት ትልቁ አሰባሳቢ ክቡር ማንነት መሆኑን በደም ዋጅቶ ዛሬ እንደደረሰ በሺጎ ማስረጃዎች እያበለጸግን ማስተጋባታችንን እንቀጥላለን።

***ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!***

# አንደበት

"ብዙ ቦታ ይተቹ የነበረውም "ዐፄ ምኒልክ ለኦሮሞ ብለው አማራውን እየገፉ ነው" በሚል ነበር፡፡ "ምኒልክ ኦሮሞውን እንደ ሰው አልቆጠሩትም" የሚለው ትርክት ውሸት ነው፡፡ ምኒልክ ኦሮሞን እንደ ሰው አክብረውታል፡፡ እንደ ሰው ቆጥረው ተጋብተውታል፡፡ ምኒልክ እናታቸው ኦሮሞ ናት፡፡ እንደ ሰው ቆጥረውት የልጅ ልጃቸውን ሸዋረጋን የዳሩ ለወሎ ኦሮሞ ኢማም መሐመድ አሊ ነው፡፡ የጦር ሚኒስትራቸው ፊታውራሪ ሀብተጊዮርጊስ ዲነግዴ ኦሮሞ ናቸው፡፡ ምኒልክን የከበቧቸው ወይም በዙሪያቸው ወሳኝ ቦታዎችን ይዘው የነበሩት ኦሮሞዎች ናቸው፡፡"



*አቶ ታየ ቦጋለ /የመራራ እውነት መጽሐፍ ደራሲ/*
*አዲስ አድማስ ጋዜጣ ሐምሌ 6 ቀን 2011 ዓ.ም*

"እዚህ ምክር ቤት ውስጥ የሐሳብ ፍጭት ቢደረግ ኖሮ አሁን አገሪቱ የገጠማት ቀውስ ውስጥ ሳትገባ ትችል ነበር፡፡ ቀደም ብሎ የሐሳብ ፍጭት የሚደረግበት ምክር ቤት ቢሆን ኖሮ የገጠመን ቀውስ በዚህ በኩል ይቀጣ ነበር፡፡ ማንኛውም ሐሳብ ቀርቦ ፍጭት ከተደረገበት በኋላ ጭሱ በዚህ ምክር ቤት በኩል መውጣት አለበት፡፡ ይህንን ሁኔታ በቀጣይ እንፈጥራለን፡፡ ለዚህም ሲባል በቋሚ ኮሚቴዎች በኩል የሚደረጉ ክርክሮች ጭምር፣ ምክር ቤቱ በሚያቋቁመው ቴሌቪዥን በቀጥታ ለህዝብ ይተላለፋል፡፡ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በምክር ቤቱ የክትትልና ቁጥጥር ተግባር ላይ በቀጥታ እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡"



*አቶ ታገሰ ጫፎ፣ /የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ/*
*ሪፖርተር ጋዜጣ ሐምሌ 7 ቀን 2011 ዓ.ም*

"እነሱ አዲስ አበባ ላይ ብቻ ቁጭ ብለው እንቅስቃሴ አለማድረጋቸው ነው፡፡ አባሎቻቸውን ወርደው እስከ ቀበሌና እስከ መጨረሻው የኢትዮጵያ ጫፍ ድረስ ሄደው ህዝብ አደራጅተው ነው አሁን ወዳሉበት አቋም የመጡት፡፡ ህዝቡን ያውቃሉ፤ ህዝቡን አወያይተው ፍላጎቱን ለመረዳት ጥረት አድርገዋል፡፡ ሌሎችም ፓርቲዎች ከኢ.ዜ.ማ ጋር ለመቀላቀል የምርጫ ቦርድ ሰርተፍኬት ቢቀዱ የተሻለ ነው የሚል ምክር አለኝ፡፡ ይህን የምለው ኢ.ዜ.ማ ስለሆነ አይደለም፤ አቅምና ህገመንግስታዊ ድጋፍ ያለው በመሆኑም ጭምር ነው፡፡"



*አቶ ተመስገን ዘውዴ /የቀድሞው ፓርላማ አባል/*
*አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሐምሌ 6 ቀን 2011 ዓ.ም*

"..... እግር ኳሱን የሚጫወቱና የሚከታተሉት በአብዛኛዎቹ የወጣቱ ክፍል በመሆኑ ልዩ ትኩረት ይሻል.....፣... እግር ኳሱ የፖለቲካ መፈንጫ፣ መናኸሪያ ለመሆን እየተቃረበ ነው.....፤ ስለዚህ የ2012 የውድድር ዘመን ከመጀመሩ በፊት መንግሥት ማብለጫ ከመስጠት በዘለለ የተለየ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል የሚል እምነት አለኝ.... "... ምነው በእንቁላሉ .." እንደሚባለው ይሄ ክፉ አዝማሚያ በቶሎ ካልተቀጨ እግር ኳሱ ለሀገር አንድነት ሳይሆን ለሀገር መበታተን ምክንያት እንዳይሆን የሚል ስጋት አለኝና በደንብ ሊታሰብበት እንደሚገባ ነው አስረግጬ መናገር የምፈልገው፡፡



*አሰልጣኝ ሳምሶን አየለ (ስሁል ሽሬ)*
*ሀትሪክ ጋዜጣ ሐምሌ 10 ቀን 2011 ዓ.ም*

## ግጥም

### ንጋት

ጠጠር ባካፎዳ፣ ከባህር ዳር ለቅመው፣
ደሞ ዳግም ገድፈው፣
በድሜጥሮስ ኩፋል፣ ከባህረ-ሀሳብ
  አቡሻህር ቆጥረው፣
  ዘመን የፈተቱ፣
ጊዜን የበለቱ፣
ከጨረቃ ሌሊት፣
ከጀምበርም መአልት፣
  ቀን የፈተፈቱ፣
ምንኛ ዋተቱ!
ምንኛ ቃተቱ!
አወይ መጥቅዕ መና፣ ወይ አበቅቴ ከንቱ፡፡
ዘመን አይፈረጥጥ፣ ጊዜም አይሸመጥጥ፤
  ቀንም መሸሽቶ አይነጋ፤
ሰው ነው የሚጨልም፤ ሰው ነው የሚነጋ፡፡

***የቀንድ አውጣ ኑሮ ከይስማዕከ ወርቁ***

## አባባል

### የኢትዮጵያ ፋና ወጊ ባለሙያዎች

- የመጀመሪያው ዘመናዊ - ሰዓሊ አገኘሁ እንግዳ
- የመጀመሪያው የአብስትራክት ሥነ-ሥዕል ጠቢብ - ገብረክርስቶስ ደስታ
- የመጀመሪያው የግዕዝ - አማርኛ መዝገበ ቃላት አዘጋጅ - አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ
- የመጀመሪያዎቹ አይሮፕላን አብራሪዎች - አስፋው አሊና ሚሽካ ባቢችፍ
- ለመጀመሪያ ጊዜ ድምፃቸው በዲስክ የተቀረፀ - አፄ ምኒልክና እና እቴጌ ጣይቱ
- የኢትዮጵያ ሬዲዮ የመጀመሪያ ተናጋሪ - አጼ ኃይለሥላሴ
- በኢትዮጵያ ሬዲዮ የመጀመሪያዋ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ተናጋሪ - ልዕልት ፀሐይ

## አስገራሚ ነገሮች

- በአንዳንድ የእስያ አገራት በተለምዶ ሰዎች በሚመገቡት እና በሚመጡት ምግብ ውስጥ የወርቅ ዱቄት ይጨምራሉ፡፡ ይህም የሚደረገው ወርቅ እንደ ቁርጥማት ላሉ ህመሞች ፍቱን መድኃኒት ስለሆነ ነው፡፡ ሳይንስም አረጋጦታል፡፡
- በፊላንድ ደሴት ላይ ላይ ብቻ 60.000 ኃይቆች ይገኛሉ፡፡
  እርድ የተጨመረበት ምግብ መመገብ ለካንሰር የመጋለጥ እድልን ይቀንሳል፡፡
- 1 እርሳስ 50.000 ቃላትን ይፅፋል፤ 35 ማይልስ ርዝመት ያስምራል፡፡
- ብዙ ሰዎች የሚሞቱት ከተወለዱበት ወር አካባቢ ነው ይባላል፡፡
- ብዙ ሰዎች ሸረሪትን ከሞት በላይ ይፈራሉ፡፡

## ስለ ቀለማት

**ወይንጠጅ፡-** የቀይ ኃይልና የሰማያዊን ስክነት በጥምረት ይዟል፡፡ አዕምሮን የማረጋጋት ኃይል አለው፡፡ መንፈሳዊነትንና ፈጠራን ያበረታታል፡፡

**ነጭ፡-** የሰላም ምልክት ነው፡፡ ንፅህናን፣ ተፈጥሮአዊነት፣ የህክምና ቀለም ነው፡፡

**ግራጫ፡-** ተግባራዊነት ያሳያል፡፡ የብቸኝነት፣ የድብርት፣ የእጦት ስሜትን ሊያጭር ይችላል፡፡

**አረንጓዴ፡-** የአካባቢ እና የሰላም ምልክት ነው፡፡ ሚዛናዊነትን፣ ተፈጥሮአዊነት፣ ሁለገብነትን ያሳያል፡፡ አእምሮን የማደስ እና የማዝናናት ኃይል አለው፡፡

**ቢጫ፡-** ብሩህነትና ደስታ እንዲሁም የወደፊት ተስፋን ያሳል፡፡ የማስታወስ ችሎታን ያነቃቃል፤ ግንኙነትን ያበረታታል፡፡

# አንዳርጋቸው ተናግሯል፤ ግን በመጠኑ አደናግሮናል



ጌታቸው ስሜ (ኢንግላንድ)

አንዳርጋቸው ጽጌ "ትውልድ አይደናግር፤ እኛም እንናገር" በሚል ርዕስ በቅርቡ ለንባብ ያበቃው መጽሐፍ የአንዳርጋቸውን ሽራፊ ታሪክና የትግል ዘመኑን ገድል በስፋት የዘገበበት ነው።

ከቅርፅ አንፃር በሚገባ የታሰበበትና የተዘጋጀ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። በቋንቋ አጠቃቀምም ቢሆን፤ በአሁኑ መፅሀፍ ግልፅና ፍሰት ያለው አፃፃፍ ተጠቅሟል። "ነፃነት የማያውቁ ነፃ አውጭዎች" የተባለው መጽሐፉ በይዘቱ እጅግ የገዘፈ ሃሳብ ያዘለ ቢሆንም፤ የተጠቀመበት ቋንቋ ጠጣር ነው። ይህ ጠጣርነት በአሁኑ "ትውልድ አይደናገር፤ እኛም እንናገር" ላይ አይታይም።

አንዳርጋቸው በዚህ መጽሐፉ ከታሪክ ጸሐፍት ጋር በታሪክ አፃፃፍ ላይ አይስማማም። ታሪክ ምንም አልተፃፈም ባይ ነው። ይህንን አባባሉን ስናነብ "እንዴት አንድ ታሪክ ፀሀፊ አንኳ አለ አይለንም?" ማለታችን አይቀርም። መጽሐፉ ከታተመ በኃላ በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫ ይህንኑ እምነቱን ተናግሯል። በመጽሐፉ ላይ በግርጌ እንደማጣቀሻ የሚጠቀምባቸው የእነ ዘውዴ ረታ መጽሐፍት ከታሪክ መጽሐፍ ተርታ አለመቆጠራቸው ይገርማል።

ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያምም ታሪክ እንደ ታሪክ መመዘኛ አልተፃፈም ይሉና ነገር ግን አንዳንድ ታሪክ ጸሐፊዎች መኖራቸውን ይጠቅሳሉ። ለምሳሌ በታሪክ ተመራማሪነታቸው ፐ/ር ስርግው ሀብለስላሴን አንዱ ናቸው ይሉናል። አንዳርጋቸው ግን አንድም ታሪክ ጸሀፊ የለም ባይ ነው። በእሱ ዕይታ የእሱ ትውልድ አባል የሆኑትና በም ዕራብ ዩኒቨርሲቲ ታሪክ ያጠኑትም ታሪክ አልፃፉም ።

## ምን አዲስ ነገር አለ?

አንዳርጋቸው ምን አዲስ ነገር ነገረን? ብዬ ሳስብ አዲስ ነገር የነገረን፤ የእሱን አያት ቅድመ አያት ፣ ዘመዶች በጋብቻ፣ በጦርነት፣ በስራ እንዲሁም በሌሎችም መስተጋብሮች ከሌሎች ብሔሮች ጋር እንዴት አብረው እንደኖሩና በማህበረሰብ ግንባታ ኢትዮጵያ አንዴት እንደተሸመነች ይተርክልናል። ማህበረሰቦች የተመሰረቱት እንዲህ ነው ወይም ኢትዮጵያውያን የተሰራነው በዚህ መልኩ ነው ብሎ ቀጥታ ሳይሆን የሚነግረን፤ በትረካው ውስጥ የተሰራንበትን ፈትል ያሳየናል። የማስታወስ ችሎታው ተጨምሮበት ትረካውን የሚስብ አድርጎታል።

የአንዳርጋቸው አባት በልጅነታቸው በጦርነት ምክንያት የተለዩዋቸውን እናታቸውን ፍለጋ አሰላ ከተማ ሄደው ከብዙ ድካም በኂላ በቆጂ የሚባል ትንሽ ከተማ እንዳገኙዋቸው የሚተርከው ክፍል እጅግ ያስደምማል። በጦርነት ምክንያት ወላጆች ከልጆች እንዴት እንደሚለያዩና ልጆች ከወላጆቻቸው እቅፍ ተነጥቀው እንዴት በአሰቃቂ ሁኔታ እንደተገደሉ ያሳየናል። ይህ የታሪካችን አካል በጦርነት ኖረን በጦርነት የመፈላለግ ክፉ መንፈስ እንዳለቀቀን ያሳያል። የእናቶች ጣር አንዳርጋቸው በተረከበት የጣሊያን ወረራ ወቅት አላበቃም። የአንዳርጋቸው ወላጅ በተራቸው ወልደው ልጆቻቸውን በቀይ ሽብር እንዴት እንዳጡ ይተርክልናል። የወላጆች ዋይታ በኢትዮጵያ ሳያቋርጥ እስካሁን መቀጠሉ እጣ ፈንታችን ይመስላል። የአንዳርጋቸው እናት ልጃቸው ከሞት ከተረፈ ቤተክርስትያን እርቃናቸውን ሶስቴ ለመዞር የተሳሉት ስለት፤ በወቅቱ የአገራችንን እናቶችና አባቶች ዋይታና ሰቆቃ በሚገባ የሚያንፀባርቅ ነው።

ስለቤተሰቦቹና ስለ አዲስ አበባ የተረከበት መንገድ ለየት ስለሚል የሚስብ ነው። በአዲስ አበባ አመሰራረት ላይ ሞጋች የታሪክ እሰጥ እገባ ያጋጥመዋል የሚል ሃሳብ አለኝ። በአዲስ አበባ አመሰራረት ላይ የሌሎች ታሪክ ጸሐፊዎች አስተያየት ቢጨመርበት፤ ታሪክን ከተለያየ አቅጣጫ ለማየት እድል ይሰጣል።

በአድዋ ጦርነት ሙስሊሞች ሬሳቸው አልተቀበረም ይለናል። አንዳርጋቸው እንዲህ ዓይነቱ ታሪክ በታሪክ ጸሐፍት አልተነገረም ይላል። ተሸፋፍኖ መቅረት ስለሌለበት መነገር ይገባዋል በማለት ለበርካታ ጌዜ በመፅሀፉ በዋቢነት የሚጠቅሰውን የጄ ስፔንሰር ትሪንግሃምን Islam in Ethiopia ያነሳል። አልተነገረም ቢባል እንኳ፤ በአሁኑ ወቅት መነገር የለበትም ሲሉ የሚሞግቱ በርካታ ሰዎች አሉ። እንደ ምክንያትም የሚያቀርቡት የውይይትና የመተቻቸት ባህል ባልዳበረበት፣ ታሪክ ለመማማርና ያለፈውን ለማወቅ ሳይሆን እንደዚህ ዓይነቱ ትረካ ለአሁኑ ቁርሾ እንደ ግብዓት የሚቀርብ እርሾ የመሆን እድሉ በሰፋበት በአሁኑ ወቅት፣ በጎሳ (በዘውግ) ፖለቲካ አገራችን እንደ ቆዳ ተወጥራ ባለችበት ወቅት እንዲህ ዓይነቱን ሆድ የሚያስብስ ትረካ መተረክ አግባብ አለመሆኑን ነው። አንዳርጋቸው በመፅሀፉ ምረቃ ላይ ስለዚሁ ጉዳይ ተጠይቆ ሲመልስ "ምንአልባት ሙስሊሞች ያልተቀበሩበት ምክንያት በ48 ሰዓት መቀበር እንዳለባቸው እምነቱ ስለሚያዝ አልተቀበሩ ይሆናል" ይላል።

አንዳርጋቸው የጣሊያንን ፋሺስት ለመ ዋጋት በተደረገው ጦርነት የተራው ተዋጊ በተለይ የሴቶች ጀግንነት አልተተረከም ይለናል። ተገቢ ጉድለታችንን ያየበት መንገድ ስለሆነ፤ ታሪክ ጸሐፍት ሊያተኩሩበት ይገባል የሚለው አሳማኝ ነው። ለዚህ እንደ አብነትም በቼክ ተወላጁ በፓርስላክ ተፅፎ በተጫኔ ጆብሬ የተተረጎመውን "የሀበሻ ጀብዱ" ያነሳል። ይህ መፅሀፍ አብቹ ስለተባለው ጀግና ወጣት መተረኩ ከተለየ አቅጣጫ የተፃፈ መሆኑን ያሳያል ሲል ያሞካሻል። ተገቢ ውዳሴ ነው። አንደ እኔ የሃበሻ ጀብዱ የተባለውን መፅሀፍ ጋሽ አሰፋ ጫቦ እንደሚለው (Mandatory Reading) መሆን አለበት። ለአቅመ ንባብ የደረሰ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ሊያነበው ይገባል።

## የኢህአፓው ጎራ

አንዳርጋቸው ገና ከአፍላ ወጣትነት እድሜው ጀምሮ የተሳተፈበትን የተማሪዎች እንቅስቃሴና የኢህአፓ ተሳትፎው በመፅሀፉ ግማሹን ክፍል ሸፍኗል። አንዳርጋቸው የነገረን በዚያን ጊዜ በነበረው የፖለቲካ አሰላለፍ በአመራርም በአባልነትም ከተሳተፉት ሰዎች ትርክት ብዙም አይለይም ባይ ነኝ። አንዳርጋቸው ለኢህአፓ አመራሮች በነበረው ቀረቤታ ያየውን የሚገልፅበት መንገድ ሌሎች በራሳቸው እይታ ካስቀመጡበት መንገድ በስልት ይለያይ እንጂ፤ ልክ እንደ ሌሎቹ የኢህአፓን፣ የመኤሶንና የደርግን ታሪክ እንደጻፉት ሁሉ እሱም ኢህአፓን ሲከላከል እናየዋለን። በእኔ እይታ ከሌሎቹ የሚለየው ኢህአፓ ላጠፋው ጥፋት በተገቢው መንገድ እውቅና መስጠቱና ሚዛናዊ ለመሆን መሞከሩ ነው። በዚህ በኩል በሌሎቹ ጸሐፍት የማይታይ ጥፋትን አምኖ ሓላፊነት የመወሰድ ድፍረቱን አደንቃለሁ።

መጽሐፉ ተጀምሮ እስኪያልቅ በሻምበል ፍቅረስላሴ ወግደረስ የተፃፈውን ‹‹እኛና አብዮቱ›› የሚለውን መጽሐፍ ይተቻል። "አብዮታችን" የሚለውን የመንግስቱ ኃ/ማርያምን መጽሐፍ እየጠቀሰ ይተቻል። በመኤሶንና በኢህአፓ መካከል የነበረውን ትንቅንቅ አሱ በሚያየው መንገድ ገልፆታል። የኢህአፓ ተሳትፎው በተረከበት ክፍል የኢህአፓ ዋነኛ አመራር የሚባለው ተስፋዬ ደበሳይ በመኪና የሚያመላልሰው አንዳርጋቸው ስለነበር፤ በሚገባ ስለባህርዩ ፅፏል። በእርግጥ አንዳርጋቸው የተስፋዬ ደባሳይን ስብዕና ለማሳየት ሞክሯል። ሸጋ ፀባይ የነበረው ትሁት ሰው እንደነበር ይገልፅልናል። ምንአልባት በተስፋዬ ደበሳይ የግል ባህርይ ላይ ብዙም የተፃፈ ነገር ስለሌለ አዲስ ነገር ነው ብዬ አምናለሁ። ሌላው አስገራሚ ነገር አንዳርጋቸው ተስፋዬ ደበሳይን "የእኔ መሲህ" ሲል ይገልፀዋል። ስለተስፋዬ ሲተርክም በትግል ስሙ "ሙሴ" እያለ የሚጠራውን ተስፋዬን "መሲሁ" እያለ ይተርካል። ምንያህል አግዝፎና መሲህ አድርጎ እንደሚመለከተው ያሳየናል። ይህ አገላለጹ የግራ ሃይል ፖለቲከኞች ግለሰብ መሪንና ድርጅትን እንደ ►

ታቦት እንደሚያመልኩ አንድ ማሳያ ነው ማለት ይቻላል፡፡

አንዳርጋቸው እንደሚለን በወቅቱ ብዙኃኑ የእዛ ዘመን የግራ ፖለቲከኛ በማርክዚዝም ሌኒኒዝም ጥራዝ ነጠቅ ፍልስፍና የተጠመቀ ቢሆንም፤ አንደ ተስፋዬ ደበሳይ ያለ ሰው የግራውን ፖለቲካዊ ፍልስፍና ብቻ ሳይሆን የምዕራቡን ፍልስፍና ጠንቅቆ በጥልቀት የተረዳና የሚተነትን መሆኑ ለየት ያደርገዋል፡ ፡ ስለተስፋዬ ደበሳይ አሟሟት የገለጸበትም መንገድ ክፍሉ ታደሰና ሌሎች ጸሐፍት ከነገሩን በመጠኑ የሚለየው፤ ተስፋዬ ራሱን ከፎቅ ላይ ሲወረውር ምስሉ እንዳይታወቅ የሞተበት መንገድ ልብ ይሰብራል፡፡ አንዳርጋቸው ተስፋዬ ደበሳይ መሆኑን ያወቀው ሬሳው በቲቪ ሲታይ የሚያደርጋትን ጃኬት በማየቱ ወዲያው እሱ መሆኑን መለየት በመቻሉ ነው፡፡ አንዳርጋቸውን ጨምሮ ብዙዎቹ በዚህ ጉዳይ ላይ የፃፉ እንደነገሩን የተስፋዬ ደበሳይን ማንነት ሬሳውን አይተው ለደርግ ያረጋገጡት መኢሶኖች ናቸው፡፡ ደርግ ተስፋዬ ደበሳይን ማን እንደሆነ በስም እንጂ አያውቀውም፡፡

ተስፋዬ ደበሳይ ከመሞቱ ጥቂት ደቂቃ በፊት አምባሳደር ትያትር አካባቢ መጀመርያ ተስፋዬ ደበሳይን ያየው የአንዳርጋቸው ዘመድ ዘሪሁን የሚባል የመኢሶን አባል የሆነ ወጣት ነው፡፡ በዚህ ትረካው ላይ የሚያስገርመው ይህ ዘሪሁን የተባለው ወጣት ተስፋዬ ደበሳይን ሲያየው ከመደንገጡ የተነሳ ራሱን ሳተ ይለናል፡ ፡ ይህ አዲስ ነገር ነው፡፡ በክፍሉ ታደሰም "ያ ትውልድ" መጽሐፍም ሆነ በሌሎችም በኢህአፓ ላይ በተፃፉት አልተነገረም፡፡

ሌላው በኢህአፓ ውስጥ በአንጃ የመከፋፈል እሰጥ እገባ እስካሁንም በህይወት ባሉት አባላቱ በጎራ የከፋፈለና አጨቃጫቂ ነው፡ ፡ በቁጥር ጥቂት የሆኑ ብቻ ናቸው ይህንን በአንጃነት መፈራረጅ ለማንም አይጠቅምም ሲሉ በወቅቱ የተደረገውን እንዳለ የሚኮንኑት፡ ፡ በአመራሮቹ በእነ ብርሃነ መስቀልና ጌታቸው ማሩ እንዲሁም ከእነሱ ጋር የወገኑትን በሙሉ በጠላትነት የመፈረጅ አባዜ ነበር፡፡ አንጃ በሚል በተፈረጁት በእነ ብርሃነ መስቀል ና በፈራጆቹ በእነ ተስፋዬ ደበሳይ፣ ክፍሉ ታደሰ፣ ዘሩ ክህሸን ፣ ግርማቸው ለማ መካከል የተፈፀመውን የጭካኔ ድርጊት አንዳርጋቸው ይኮንነዋል፡፡ እነ ብርሃነ መስቀል የተፈረጁበት መንገድ አግባብ እንዳልሆነ አንዳርጋቸው ይገልፃል፡፡

አንጃና ፋሺስት በሚል ፍረጃ ጌታቸው ማሩን በሰቃቂ ሁኔታ ካሳንቺዝ አካባቢ አንገቱ ተቆርጦ እንዲገደል የተደረገው ዲፌንስ በሚባል የኢህአፓ ገዳይ ቡድን አማካይነት መሆኑን ይነግረናል፡፡ በዚህ በኩል አንዳርጋቸው ገለልተኛ ሆኖ አስተያየቱን በመስጠቱ ከሌሎቹ ይለየዋል፡፡ ህይወት ተፈራ በ"ታወር ኢን ዘ ስካይ" መፅሀፏ ላይ ስለ ጌታቸው ማሩ አገዳደል የገለፀችበትን ትእይንት የሚያረጋግጥ ነው፡፡ ህይወት ተፈራ የገዛ ጓደኞቹ የጌታቸው ማሩን ፊት በአሲድ ጉዳት በማድረስ ጭካኔ እንደፈፀሙበት አስነብባለች፡፡

አንዳርጋቸውን በአንጃ መፈራረጁ አስፈላጊ አለመሆኑንና ከመኢሶንም ጋር ቢሆን መነጋገር ይቻል ነበር ሲል ይጠቅሳል፡፡ "የመኢሶን አመራሮች መጠርጠር የሚባል ነገር




አያውቁም፤ ገራገር ናቸው፤ ኢህአፓ ከእነዚህ ጋር በመቀራረብ እንዴት መስራት አቃተው?" ሲል ይጠይቃል፡፡ "ከድርጅታዊ መገንተኝነት የፀዳ ሀቀኛ መልስ የሚያስፈልገው ጥያቄ ነው" ሲል ሚዛናዊነቱን ያሳየናል፡፡ አንዳርጋቸው በአንድ ወቅት የመኢሶን መሪ የነበረውን ኃይሌ ፊዳን ለጥቂት ሰዓታት አግኝቶ እንዳናገረው ገልፆ፣ "ትልቅ ሰው" ይለናል፡፡ ይህ ዓይነቱ አስተያየት ለብዙዎቹ የኢህአፓ አፍቃሪዎች አይዋጥላቸውም፡፡ ይህንን የተዛባ አመለካከት አንዳርጋቸው በመጠኑ ሰብሮታል፡፡

አንዳርጋቸው በዚህ ብቻ አያበቃም፡፡ እስከ ዛሬ በኢህአፓ ላይ ተመርኩዘው ከተፃፉት ለየት ያለ መረጃ ሰጥቶናል፡፡ እሱም በኢህአፓ ውስጥ በተለይ በዞንና በኢንተር ዞን፣ በህዋስ ውስጥ አመራር ላይ ያሉት እሱ በሚያውቀው የአዲስ አበባ አደረጃጀት ሁሉም ባይሆኑም በርካታ የሚባሉት አመራር ላይ ያሉት ብቃት እንዳልነበራቸው ይገልፅልናል፡፡ ይሁንና በተራ አባልነት እጅግ ብቃት የነበራቸው አባላት ቢኖሩም፤ ቦታውን ማግኘት አልቻሉም ሲል ይተቻል፡፡ ኢህአፓ በየትኛውም አደረጃጀቱ ምሉዕ እንደሆነ ሲነገር ከነበረው ትርክት ለየት ያለ መረጃ ፈንጥቋል፡፡ አንዳርጋቸው አክሎም "ብቃት ያላቸው ግለሰቦችን ከታች ወደላይ በመሳብ በየጊዜው የድርጅቱ መዋቅር ብቃት ባላቸው ሰዎች መሙላት የሚቻልበት መካኒዝም አልነበረም፤ ከበላይ የመጣን ትዕዛዝ ደፍረን ለመሞገት አንፈልግም፤ ከላይ ያሉት ከኛ የተሻሉ ያውቃሉ በሚል የበላይ አካላትን አምላኪነትና አደርባይነት ጥያቄያችንን አፍነን ቀረን" ይላል፡፡ እሱም የትጥቅ ትግሉን አሳዛኝ ውጤት ካየ በኃላ፤ የማያምንበት ነገር ሲፈፀም ዝም ብሎ እንደማያይ ለራሱ ቃል መግባቱን ይነግረናል፡፡ በዚህ በኩል በኢህአፓ ሰራዊት ውስጥ ሲታገል የነበረው አስማማው ኃይሉ የተፃፋው "ኢህአሰ (የኢህአፓ ሰራዊት ህዝባዊ አብዮታዊ ሰራዊት) ከ1964 እስከ 1970 ዓ.ም" ኢህአፓውያን ድርጅታቸውን የሚያመልኩበትን መንገድ ሞና ሲዛን ሰዓሊው ያመለካትን ያህል ነው ሲል ይተቻል፡፡

ሌላው የኢህአፓ አመራሮችና ዋነኛ አቀንቃኞች ከሚወቀሱበት አንዱ በሶማሊያና በኢትዮጵያ ጦርነት ወቅት ኢህአፓ ለሶማሊያ ያደረገው ድጋፍ ነው፡፡ ይህንንም አንዳርጋቸው ትክክል አይደለም ሲል ይተቻል፡፡ ኢህአፓ ከደርግ ጋር የሶማሊያን ጦር አብሮ በመዋጋት አጋርነቱን ማሳየት ነበረበት ይለናል፡፡ ለዚህም አንደ ማስረጃ ሌሎች በተመሳሳይ ጦርነት ውስጥ የገቡ አገሮች ተቀናቃኝ ፓርቲዎች ልዩነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የአገራቸውን ጠላቶች በጋራ መክተዋል ሲል ያስረግጣል፡፡ ይህ የአንዳርጋቸው ወቀሳ ተገቢና ብዙሃኑን ኢትዮጵያዊ የሚያስማማ ነው፡፡


## ኤርትራና ወላጅ አባት

አንዳርጋቸው አፍላ ጎረምሳ ሆኖ ከአባቱ ጋር በኤርትራ ጉዳይ እየተከራከሩ ሳለ እንደ ዘመኑ ግራ ፖለቲከኛ ወጣት የኤርትራን ህዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን መብት እንዳለው ለአባቱ ያስረዳል፡፡ አባቱ የአንዳርጋቸው ክርክር አልዋጥ ስላላቸውና ስለተበሳጩበት በበቆሎ የተወጠረውን ጉንጩን እንዴት በቡጢ እንደነረቱት ሲነግረን ያስፈግገናል፡፡ በወቅቱ በግራ ርዕዮትና በብሄር ብሄረሰብ መብት እስከመገንጠል ትርክት የከነፈውን ትውልድ ምልከታ ያሳየናል፡፡

አንዳርጋቸው በኤርትራ ላይ ከቀድሞ ጀምሮ ከኢትዮጵያ በኩል የተያዙ አቋሞች፣ የአጎራባች አገሮችና የአረብ አገሮች ጣልቃ ገብነት፤ ኢትዮጵያን በጂኦ ፖለቲካዊ ተፈላጊነቷ ጥርስ የተነከሰባት አገር እንደሆነች በጥልቀት ተንትኖታል፡፡ በተማሪው እንቅስቃሴ ከዚያም በኃላ በተለያዩ ግራ ዘመም ድርጅቶችና የብሄር ድርጅቶች ንጉሱና በዙሪያቸው ያሉ ባለስልጣናት የኤርትራን ጉዳይ በጨቋኝ አቋም እንደያዙት አድርገው በማቅረብ ይታወቃሉ፡ ፡ እስከ ዛሬም በዚህ ትረካ የሚያላዝኑ አሉ፡ ፡ አንዳርጋቸው ሲገልፅ "እንደ እነ አክሊሉ ሃብተወልድ አይነት ሰዎችም ላይ የእኔ ትውልድ ከሚገባው በላይ ያሳየው ጥላቻ ሚዛኑን የሳተና በእውቀት ላይ ያልተመሰረተ ነው" ሲል የዘውዴ ረታን "የኤርትራ ጉዳይ" ጠቅሶ ይተቻል፡፡

በሌላ ጎኑ ኢህአፓ በታክቲካል አቀራረቡ በኤርትራ ጉዳይ ላይ ከሕወሓት ብዙም አንደማይለያይ እናያለን፡፡ ለምሳሌ ኢህአፓ ብሄረሰቦች መብታቸውን ለማስከበር እስከ መገንጠል የሚደርስ መብት እንዳላቸው የሚያምንና ለዚህም ሲታገል የነበረ ድርጅት መሆኑን በአንዳርጋቸው መጽሐፍ ተጠቅሷል፡ ፡ ሕወሓትም በተመሳሳይ መልኩ ማኒፌስቶው ላይ አስፍሮታል፡፡ አሁንም በስራ ላይ ባለው ህገ መንግስትም እንዲሰፍር ተደርጓል፡፡ ይህ መብት በህገ መንግስት ደረጃ መሰጠቱ እስከአሁንም ለገባንበት ቀውስ አስተዋፅኦ አድርጓል በሚል የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ይኮንኑታል፡፡

አንዳርጋቸው በ664 ገፅ በቀነበበው መፅሀፉ ያካተታታቸው መረጃዎችና ትረካዎች አጓጊና እስመጨረሻው ሳንሰላች እንድናነብ ይገፋፉሉ፡፡ የማስታወስ ብቃቱንና የማደራጀት ችሎታውን በመጽሐፉ ላይ ባሰፈረው ርእስ ጉዳይ አንጻር መረዳት ይቻላል፡፡ ወጣቶችም ፍላጎት ካላቸው በመጽሐፉ እንደ ዋቢ መጽሐፍት የተጠቀመባቸውን መጽሐፍቶች አሳደው ቢያነቡ እጅጉን ይጠቀማሉ፡፡ ከአሁኑ እትም ቀጥሎ በሚያሳትመው ቅፅ 2 አዲስ ነገር ይነግረናል የሚል እምነት አለኝ፡፡



ተሾመ ሺፈራው

# "ኢትዮጵያ ወይም ሞት!"

የ"ኢትዮጵያ ወይም ሞት"ን አጭር ትዝታ አንስተን ወደ ረጅሙ የፖለቲካ ወግ እንግባ፡፡ ኤርትራውያኑን ከጣሊያን ቅኝ ግዛት ነፃ አውጥቶ ወደ እናት ሀገራቸው ኢትዮጵያ ለመመለስ ንጉሰ-ነገስቱ የደከሙትን ድካም መቸም የምንረሳው አይደለም፤ በአክሊሉ ሀ/ወልድ አስፈፃሚነት የተባበሩት መንግስታት ጉባኤ ላይ እየተመላለሱ 'ኤርትራን ስጡን' ብለው መከራቸውን ተቀብለዋል፡፡

አሻጥረኛው 'ህብረት' ተብየውም የተለያዩ አሽከር ልዑካኑን (ተወካይ ሃገራቱን) ወደ አስመራ በመላክ ኤርትራውያኑ ምርጫቸው "ከኢትዮጵያ ጋር መዋሀድ ነው ወይስ ነፃ መሆን ነው?" የሚለውን ጥናት አስደርጓል፡፡ በተለይ-በተለይ በመልክዓ-ምድር አሰፋፈር ደጋማ የሚባሉት ክርስትያን ኤርትራውያኑ ባስታወሱት ቁጥር ልብ የሚነካ፤ በታሪክ ሲዘከር የኖረና የሚኖር አቋም ነበራቸው፡፡ "ኢትዮጵያ ወይም ሞት" በማለት ለእናት ሀገር ኢትዮጵያ ያላቸውን ጥልቅ ፍቅር ገልጸው ነበር፤ አንድ አድርጉን ብለውም ተማፅነዋል፡፡ መቸም ታሪክ ራሱን በመጥፎው ነገር መድገም ይቀናዋልና ደገኛ ኤርትራውያኑ "ኢትዮጵያ ወይም ሞት" ብለው በአደባባይ የጮሁትን ጩኸት እኛው ራሳችን ኢትዮጵያኑ "ኢትዮጵያ ወይም ሞት" ከምንልበት፤ ከኢትዮጵያዊነት ከምንለያይ "ሞት" ይቅድመን ከሚባልበት ክፉ ዘመን ላይ ቆመናል አዎ! ኢትዮጵያ ወይም ሞት!

ኢትዮጵያውያኑ ኢትዮጵያ ወይም ሞት የሚለውን መፈክር አደባባይ ይዘው የሚወጡበት ቀን የነጋ ይመስላል፤ ምክንያቱም "የኦዴፓ ዘመኗ ኢትዮጵያ" ሁለት ጫፍ በደረሱ የሃሳብ ገመዶች ከወዲያ ወዲህ እየተሳበች፤ እየተንተተች ነው፡፡ ሰላም (መረጋጋት) እንዳማረሽ ይቅር የተባለች የምትመስለው ይህች ሀገር በሁለት መንታ ሀሳቦች መሃል እየተንገላታች ነው፡፡ የ 'ዜግነት' (ኢትዮጵያ ወይም ሞት በሚለው) እና የ 'ማንነት' በሚል ተቃራኒ ርዮት መካከል እየዋለለች ነው፡፡ የፖለቲካ ልሂቃን ነን በሚሉ አጥፊና አልሚ ኢትዮጵያውያን የህልም መለያየት፤ የዓላማ ተቃርኖአቸው ወደታችኛው ሰፊው ህዝብም ተርፎ መላ ኢትዮጵያውያንም በዚሁ ሁለት ሀሳብ የተከፈለ ይመስላል፡፡

ኢትዮጵያ በዜግነት(ኢትዮጵያ ወይም ሞት በሚለው) እና በማንነት ፖለቲካ መሀል ቆማለች፤ የመጭው ኢትዮጵያዊያኑ ዕድል የሚወሰነው ከሁለቱ የፖለቲካ አቋሞች በአንደኛው መሆኑ የገባቸው የሀሳቡ ባለቤቶች ለፍፃሜ ጨዋታ ሜዳ የገቡ ይመስላሉ፡፡ መቸም ዳር ቆሞ ለሚያስተውል ተመልካች ነገርየው ሁሉ የሚያሳዝን ነው፡፡ ምክንያቱም ከእኛ፤ ከኢትዮጵያውኑ ማንነት፤ ከኖርነው ባህል አንፃር ይሄ 'ጉድ' የሚፈጠር አይመስልም ነበር፡፡

ምስጋና ለድሮው ሕወሓት ለዛሬው ት.ህ.ነ.ግ (ያው ወደ ብሄር ትግል ተመልሷል ብዬ ነው) ይሁንና ይህችን ታላቅ ሀገር፤ በ national identity (ፅንፋዊ ብሔርተኝነት) መካከል የምትወዛወዝ ትንሽ ሀገር፤ ልፍስፍስ ህዝብ አድርጎ ነው የሄደው፡፡

"ባንበላው እንኳ ጭረን እናጥፋው!" አይነት በራስ ወዳድነት ተረት ተኮትኩቶ ያደገው ትህነግ፤ ዘላለም በማይኖርበት መንግስቱ ለዘላለም "ፈተና" ላይ ጥሎን ወደ ምሽጉ መከተቱን ዛሬ እያየን ነው፡፡

ኢትዮጵያን "ኢትዮጵያ" ያደረጋት፤ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በአንድ "የኢትዮጵያዊነት" ስም አስተሳስሮ የኖረውና አቃፊ (Inclusive) በመባል የሚታወቀው National History (የጋራ ብሔራዊ ታሪክ) የአቃፊነት ጉልበቱ ሳስቶ፤ የወል ፀጋነቱ ጥኑ ፈተና ላይ ወድቆ በተቃራኒው New Nation Building የሚሉት አዲስ ፍልስፍና እየተገዳደረው ይገኛል፡፡

ይሄ፤ ከጎሳ ፖለቲካ እቅፍ ውስጥ ሾልኮ የወጣው የአዲስ አገር ምስረታ 'project'፣ ገና ከጥዋቱ ጀምሮ እንደሚመለክ የወንዝዳር ውቃቤ ደም አፍስሱልኝ እያለ ነው፡፡ ታላቁን የብሔራዊነት ስሜት እንደረጋ ሰራሽ ሸክላ "አነካክቶ" በእሱ ፍርስራሽ ላይ ነፍስ ለመዝራት የሞት ሽረት ተጋድሎ በማድረግ ላይ የሚገኘው "የማንነት" ፖለቲካችን፤ ከጎዳን በላይ ገና የሚጎዳን፤ በአዲስ የሀገር ምስረታ ስም ብዙ ዋጋ ሊያስወጣን፤ ሄዶ…ሄዶ "ኢትዮጵያዊነትን" አስጥሞ በማንነት ፍሊጋ መዘዝ "ብሄርተኝነት" ኢትዮጵያን እንዲገዛ፤ ይሄን "ስታሊናዊ" ሀሳብ በተሸከሙ ታማኝ አሽከሮቹ በኩል ለማስፈፀም "ጉድ፤ ጉዱ" ተጀምሯል፡፡

በ'New nation building' (በአዲስ ሀገር ምስረታ) ሂደት ውስጥ ትልቅ ፈተና አለ፤ የጉዳዩ አጥኚዎች በአዲስ ሀገር ምስረታ ውስጥ ምንግዜም የሚጎዳ ባህል፤ ታሪክ፤ ማህበረሰብ ወይ መደብ መኖሩ አይቀሬ ነው፡፡ ምክንያቱ ደግሞ በ"አዲስ የሀገር ምስረታ" ላይ የሚቀነስ የነበረ ማንነት፤ የሚዋጥ የማኅበረሰብ ክፍል፤ የሚገፋ ሀገራዊ ዕሴት መኖሩ የሚጠበቅ ነው፡፡ ይሄ ጥፋት የሚከሰተው ደግሞ ልክ አሁን በሀገራችን ለማድረግ እየተሞከረ እንዳለው የነበረን "ኢትዮጵያዊነት" ሙሉ ለሙሉ ትቶ አዲስ "የማንነት" ፖለቲካ ስርዓት ለማነፅ በሚደረግ ሩጫ ነው፡፡ ስለዚህ በአዲስ የሀገር ምስረታ ወቅት የነበረውንና አዲሱን ጎን-ለጎን አስታርቆ የሚሄድ ስርዓት ካላበጁ በቀር፤ "የማንነት" የጎሳ ፖለቲካ ብቻ ካልሆነ ሞቼ እገኛለሁ ብሎ "ምድርን ቁና" ማድርግ ሀገርን ከማፍረስ የዘለለ ግብ የለውም፡፡

የማንነት (የብሔር) ፖለቲካ መዘዞቹ ከኢትዮጵያ ነባረ የታሪክ ዳራ አንጻር የማንነት (የብሔር) ፖለቲካ የመሰረት ድንጋይ "እናስቀምጥ" ባዮቹ፤ አዲስ ሀገር እንስራ ማለታቸው እንደሆነ መቸም ግልፅ ነው፡፡ በእርግጥ "ብሔርተኛ" ማሕበረሰብን ማፍራት ግቡ አድርጎ ጉልበቱን አፈርጥሞ የተነሳው የ"አዲስ ሀገረ - መንግስት ግንባታ" (ስራ) ዛሬ አልተጀመረም ባይ ነኝ፡፡ በተለይ በ60ዎቹ መግቢያ አካባቢ ወዲህ (ጀምሮ) የብሔር መበደል አለ ብለው መፈክራቸውን ይዘው በአደባባይ ብቅ በማለት የነሱን ዘመን ወጣት አይን የገላለጡት፤ በተለይ ንግግሩም፤ ፅሁፉም ደም- ደም በሚሸተው ዋለልኝ መኮንን "ስብከት" የተመሰጡት የዛን ጊዜ ጎረምሳ ተከታዮቹ፣ ኢትዮጵያ ከዚያ በፊት አይታ ወደ ማታውቀውና በ "ብሔር" ላይ የታነፀ አዲስ የሀገር ምስረታ ስራን "አንድ" ብለው መነሳታቸውን ታሪክ መዝግቦ አስቀምጦልናል፡፡ የሚገርመው፤ በተለይ ከንጉሰ ነገስቱ አሳዛኝ ስንብት በኋላ (ወዲህ) ኢትዮጵያን "በብሔርተኛነት" ቀርፆ ለማውጣት የተደረገው "ግብግብ" ነው እንደ ጎማ እየተንከባለለ ከእኛ ላይ የደረሰ፤ የሃምሳ አመት ጥያቄ እንበለው፡፡

በእውነቱ ከሆነ፤ ለብሔሮች እኩልነት ዘብ መቆሙ አይደለም የማንነት ፖለቲካ በብዙዎች "ለጎሪጥ" መታየቱ፤ የተገፋ ማንነት በራሱ ቋንቋ እና ታሪክ ኩራት እንዲሰማው መደረጉም አይደለ የብሔር ፖለቲካ 'መርሁ' ስሜታችንን ሊገዛ ያቃተው፤ ይልቁን አፋፍ ላይ ቆሞ ከሚነፋው 'የብሔር ነፃነት' መለከት በስተጀርባ ያለው 'ረቂቅ ተንኮሉ' ምክንያት ነው ፍልስፍናው የተቀባይነት ቀውስ ውስጥ ገብቶ እንዲገላታ ያደረገው፡፡ ለዚህ ነው ይህ ሀሳብ ኢትዮጵያን አይመጥናትም እየተባለ "የብሔር ፖለቲካ" ሲጥ እንደደፋች ውሻ ሁሉም 'ሃይ' 'ሃይ' የሚለው፡፡ እንግዲህ ይሄን "የማንነት ፖለቲካ"፣ ድብቅ ሴራውን ገልጠን፣ ክንብንቡን አውልቀን "የውስጥ ገመናውን፣ ►

ድብቅ-ጥልቅ ምኞቱን ስንመረምር ሁለት መመዘኛ መርዞችን ቀምሞ አዘጋጅቷል።.

መዘዝ አንድ፡- የጎሳ መንግስት ለማንገስ በሚደረግ "ውክቢያ" ውስጥ ሁለት ተጠባቂ ማህበረሳባዊ (ብሔራዊ) ስጋቶች ይዞ እንደሚመጣ በቋንቋ እና ማንነት ፖለቲካ ላይ መሰረታቸውን የጣሉ ሕዝቦች ላይ ጥልቅ ጥናት ያደረጉ የፖለቲካ ተመራማሪዎቻችን ያስቀምጣሉ። በEthinic State (ብሔር ተኮር ስርዓተ-መንግስት) ላይ ሰፊ ጥናታቸውን ያደረጉ "አጥኚዎቻችን" በEthinc State ስርዓት ውስጥ ከሚመጡ ድብቅ ተንኮሎች የመጀመሪያው በክልሎች መካከል ጤናማ ያልሆነ የ "ማህበረ-ፖለቲካ" ውድድር ውስጥ ማስገባቱ ነው ይላሉ። አስተዳዳሪዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታን ሳይሆን፤ ቋንቋን የድንበሩ መለኪያ ባደረገው በእኛው አይነቱ የብሔር(የማንነት) ስርዓተ - መንግስት ውስጥ እንደተባለውም በክልሎች መካከል በልጦ እና ተሽሎ ለመገኘት እርስ - በርስ "ሊያጠላልፍ" በሚችል ደረጃ አስጊ ውድድር ውስጥ ገብተው መገኘታቸው አይቀሬ ስጋት ነው።

ይሄ አይነቱ በክልል መንግስታት (አስተዳደር) መካከል የሚፈጠረው ፉክክር፤ሲውል-ሲያድር ወደ ፍላደጎት (የጥቅም) ግጭት ውስጥ ይከታቸዋል። በተለይ በእኛው ሀገር አሻጥረኛ ህገ-መንግስት ሁኔታ የፌደራሉ መንግስትን "በክልል አስተዳደሮች ላይ ጣልቃ እንዳትገቡ" ብሎ "ኮድኩዶ" መያዙን ስናስበው፤የእውነትም በክልሎች መካከል የሚፈጠረው የፍላጎት ግጭጥ ሲያድግ የክልል -ለክልል ግንኙነትን ጨርሶ ሊያስቆም የሚያስችልና ድንበር ወደሚያሰማመር አሳዛ ፍፃሜ ሊያደርስ ይችላል።

ይሄ በማንነት (በጎሳ) ስርዓት ውስጥ የሚጠበቅ የክልሎች "የሻከረ ግንኙነት" አደጋ (ስጋት) ከንድፈ ሀሳብ አልፎ አሁን በተግባር እያየነው ነው። በክልሎች መካከል በጦር ሰራዊት አደረጃጀት አንዱ ከአንዱ ተሽሎ ለመውጣት የሚደረገውን "የሀይል" ፉክክር ስናይ ነገርየው የማይቀር ስጋት ነው ብለን እንድናምን ያስገድዳል። የሚያሳዝነው በብሔር ፖለቲካ መዘዝ "ኮተት" ብሎ የሚመጣው የመጀመሪያው "የክልሎች መሽካከር" መዘዝ ይሄው ዋጋ ማስከፈሉን ጀምሯል።

መዘዝ ሁለት፡- መቸም የጎሳ (የብሔር) ፖለቲካ በሽታ "ራስ ወዳድ" ተፈጥሮ ያለው መሆኑ ነው። የዚህ አይነቱ ስርዓት "ደካማነቱ" በአንዱ የበላይነትና በሌላው የበታችነት ስርዓተ-ማህበር (ማህበረሰባዊ አወቃቀር) ላይ ራሱን ያቆመ መሆኑ ነው።

"ኢትዮጵያ አታስፈልገንም" ብሎ የሚያምነው "የማንነት ፖለቲካ" ፍልስፍና ስለሌላው ሓላፊነት የማይሰማው ፍፁም አሳማዊ (ራስ ወዳድ) ባህሪ ስላለው የአናሳውን ብሔር መብት ያኮስሳል። ለምሣሌ ቤንሻንጉልን እናንሳ፤ በሙጫና እጣን ሃብቱ ይታወቃል ቤንሻንጉል። በዚሁ ክልል ከአራት በላይ ቋንቋዎችና ብሔረሰቦች አሉ።

ሆኖም የግፍ ሁሉ ምንጭ (መነሻ) በሆነው ህገ መንግስት መሰረት፤ የክልሉ ቀዳሚ ባለቤቶች የክልሉ ባለቤት ተብለው እውቅና ለተሰጣቸው ደረጃ "አንድ" ዜጎች ነው። ይህ ማለት እንግዲህ ለተሻለ ህይወት ወደ ክልሉ በመሄድ ህይወትን የመሰረቱ ኢትዮጵያዊያኑ "እንደ መጤ" ወይም እንደ ሁለተኛ ዜጋ ስለሚታዩ፤ የሰው ልጆችን እኩል የሚያደርገው "ሰውነት" የሚባለው ገዥው ሃሳብ ገደል ይገባና "በባለቤቱ እና በመጤው" መካከል ለማብረድ የሚያስችግር የጥል "ሣት" ይለኩሳል።

እናም ቋንቋን የአንድ ክልል (አካባቢ) ባለቤትነት መመዘኛ አድርጎ በተነሳ (በተመሰረተ) ስርዓት ውስጥ የሚፈጠረው ይህ አይነቱ "የመጤ እና የባለቤትነት" ግጭት ሲያድግ እጅግ አሳዛኝ ወደሆነው Ethnic Unrest ይከተል ይሉናል የፖለቲካ ተንታኞች። ይሄ በተለያዩ ምክንያቶች "በክልሌ መጣህብኝ" አይነት ከሰውነት በታች በሆነ ተራ (ሀሳብ) በሚፈጠር "ግብግብ"፤ ከክልል በማፈናቀል ይጀመርና መጨረሻም ሀገርን ወደ መከፋፈል እያንደረደረ የሚያስገባ፤ የተከፋፈለች መንግስት የሚፈጥር አጥፊ ልክፍት ነው።

ሁለተኛው "በባለ መሬቱና በስደተኛው" መካከል የሚቀሰቀስ የጎሳ ግጭት (Ethnic Unrest) ሀገር "ብትንትን" የማድረግ ጥኑ-ሃያል ጉልበት ያለው "ክፉ" መርዝ ነው።

እንደ መደምደሚያ፡- ወደ ኤርትራውያኑ ጉዳይ እንመለስ፤ ለሰባ አመታት ያክል (ትንሹን አመታት በእንግሊዛውኑ፣ ብዙውን አመታት በሮማውያን) ጫማ ስር የነበሩት ኤርትራዊን (በተለይ ደጋ ነዋሪው ክርስቲያን ህዝብ) "ኢትዮጵያ ወይም ሞት!" በሚለው ጥኑ አቋማቸው እናት ሀገሩ ኢትዮጵያን "በፌደሬሽን" ስም ተቀላቅላዋለች፤ ያው በሁለት አመታት ብቻ የኋላ ኋላ ግን ራሱን "የነፃነት ግንባር" ብሎ በሰየመው ሀይል ከሚወዷት ኢትዮጵያ ለዝንታለም ተነጣጥለው ቀርተዋል።

በእርግጥ እነሱ ኤርትራ "እምብርት" ላይ ቆመው ነው "ኢትዮጵያ ወይም ሞትን" ብለው የዛቱ፤ ለዛም ነው እናታቸውን ተነጥቀው ተቆርሰው የቀሩ። እኛ ግን "ኢትዮጵያ ወይም ሞት" ስንል መሀል ኢትዮጵያ ምድር፤ ንፁህ ኢትዮጵያዊ ሆነን ነው። አዎ ኤርትራዊ ሆኖ "ኢትዮጵያ ወይም ሞት" ማለትና ኢትዮጵያዊ ሆኖ "ኢትዮጵያ ወይም ሞት" ብሎ መነሳት የሞትና የህይወት ያህል ይለያያል። እናም ያለፈውን "ኢትዮጵያዊነት" ክብር ያላሰነሰ፤ አዲሱን የብሔር ጥያቄም የሚመለስ ሀገር መስራት ይቻል ይሆናል፤ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ኢትዮጵያ የምትባለው ሀገር በእኛ (በብሔርተኞች) ቸርነት ነው የምትኖረው ብለው የተነሱብንን የእኛው ዘመን መሳፍንታውያኑን "ኢትዮጵያ ወይም ሞትን" ብለን እንሞግታቸዋለን፤ እንነሳባቸዋለን።

በአዲስ የዲሞክራሲ ስርዓት ግንባታ ስም፤ በአዲስ የNation building ሰበብ፤ የነበረን ብሔራዊ ማንነት ከምንጩ አድርቆ፤ የቆየውን ኢትዮጵያዊነት ድምጥማጡን አጥፍቶ… አዲሱን 'የብሔር ፖለቲካ' ለማንገስ ከመሽቀዳደም በፊት ሰከን ብሎ አትራፊና አክሳሪውን ማመዛዘን ግዴታ ነው።

ጤናማውና ተቀባይነት የሚኖረው የአዲስ ሀገር ምስረታ 'እንቅስቃሴ'፤ ኢትዮጵያን 'ኢትዮጵያ' አድርጎ ካቆያት ነባሩ National History (ብሔራዊ ታሪክ፤የወል ማንነት) ጋር ጎን-ለጎን ተከባብሮ … ተጠባብቆ የሚሄድ የብሔር ፖለቲካን ስናንፀ ነው፤ ይህ ሁለቱን ነባርና አዲሱን አስታርቆ ማስኬድ በዜግነት('ኢትዮጵያ ወይም ሞት' በሚለው ወገን)እና በጎሳ ፖለቲካ አቀንቃኝ መካከል የሚዋልለውን የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያስታርቅ የመጨረሻ ዘዴ ነው።

የሆነው ሁሉ እንዳለ ሆኖ ግን 'ኢትዮጵያ ወይም ሞት' ሀሳብ ግን በፈተና ውስጥ ነጥሮ የሚወጣ ገዢው፤ኢትዮጵያኑን የሚያሸንፍ ሀሳብ ነው።

**በእውነቱ ከሆነ፤ ለብሔሮች እኩልነት ዘብ መቆሙ አይደለም የማንነት ፖለቲካ በብዙዎች "ለጎሪጥ" መታየቱ፤ የተገፋ ማንነት በራሱ ቋንቋ እና ታሪክ ኩራት እንዲሰማው መደረጉም አይደለ የብሔር ፖለቲካ 'መርሁ' ስሜታችንን ሊገዛ ያቃተው፤ ይልቁን አፋፍ ላይ ቆሞ ከሚነፋው 'የብሔር ነፃነት' መለከት በስተጀርባ ያለው 'ረቂቅ ተንኮሉ' ምክንያት ነው ፍልስፍናው የተቀባይነት ቀውስ ውስጥ ገብቶ እንዲገላታ ያደረገው**

እውነትም፤ ይኼው በብሔር ፖለቲካ ውስጥ ተጠባቂ ተብሎ የተቀመጠው "የመጤና የባለቤት" ግጭት ንድፈ - ሀሳብ፤ ይሄው "ወደ እናት ክልላችሁ ሂዱ" የሚል የጎሰኝነት (የራስ ወዳድነት) አባዜ በማፈናቀል መጀመሩን ከየክልሉ የምንሰማው የምናየው የዕለት-ተዕለት ጉድ-ገመናችን ሆኗል። በተለይ በቤንሻንጉል ክልል ውስጥ "መጤ" ከሚለው በሽታ ጋር በተያያዘ "የጥፋት ምሳሌ" በመሆን የአንበሳውን ድርሻ የሚወስድ የክልል ክፍል ይመስለኛል። ብሔርተኝነት የወለደው

# አራት ቢሊዮን ችግኝ" ቅዠት ወይስ ሌላ?



መታሰቢያ መልአከ ሕይወት

በመጀመሪያ ደረጃ ኢትዮጵያ ውስጥ በሁሉም ክልሎች ያሉ የችግኝ ማፍያ ቦታዎች ላይ ችግኝ ማፍላት አይቻልም፡፡ ከዚያም ሲቀጥል ለአንድ ችግኝ በትንሹ 3 ብር እንኳን ቢከፈል አሁን ለተባሉት የጠ/ሚ/ሩ ችግኞች 12 ቢሊዮን ብር በትንሹ ያስፈልጋል ማለት ነው፡፡ ገፋ አድርገን ከተመለከትነው ደግሞ ችግኞቹን ማጓጓዝ፣ መትከል፣ መንከባከብ የመሳሰሉ ሥራዎች ደግሞ ሌላ ወጪ እንዳላቸው ግልጽ ነው፡፡

እዚህ ላይ ማወቅ ያለብን ጠ/ሚ/ር ዐቢይ ይህንን ሥራ በረጅም ጊዜ ነው ወይስ በአንድ የክረምት ወቅት ለመሥራት ያሰቡት የሚለውን ነው፡ ፡ እንደተባለው አራት ቢሊዮን ችግኝ በአንድ የክረምት ወቅት የሚተከል ከሆነ 100 ሚሊዮን ኢትዮጵያዊ ወጥቶ ችግኙን ቢተክል፣ አንድ ሠው አራት ችግኝ መትከል አለበት ማለት ነው፡፡

ችግኝ እንደሚታወቀው ልክ አዲስ እንደተወለደ ሕፃን ነው፡፡ አዲስ የተወለደ ሕፃን ለረጅም ጊዜ እንክብካቤ ይፈልጋል፤ ችግኝም ከተተከለ በኋላ ዙሪያው ታጥሮ፣ እንስሳት እንዳይረጋግጡት ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል፡፡ ከዚያም አልፎ ውሃ ማጠጣት፣ መኮትኮትን የመሳሳሉ ሥራዎችን በሓላፊነት ወስዶ የሚሰራ ሰው መኖር አለበት፡፡ ሥሮቹ ችግኙ ዛፍ እስኪሆን ድረስ በቂ ኦክስጅን እንዲያገኙ አፈሩ በአግባቡ መኮትኮትም ይኖርበታል፡፡

በአጭሩ ለመግለፅ፤ ችግኝ ተከላ ልክ በመኸር ወቅት እንደሚደረገው እርሻ፣ ከመሬት ዝግጅት እስከ መውቃት ድረስ ስራዬ ብሎ የሚተገብረው ባለቤት እንዳለው ሁሉ፤ ችግኝም በዚህ መልኩ ዛፍ እስኪሆን ድረስ የሚንከባከብ ሰው ግድ ያስፈልገዋል፡፡

ሁላችንም እንደምናውቀው በሕወሓት ኢህአዴግ ዘመን በየዓመቱ ክረምት በመጣ ቁጥር "ችግኝ ተከላ" እየተባለ ከፍተኛ መጠን ያለው የሕዝብ ገንዘብ ሲዘረፍ እንደነበረ አይዘነጋም፡፡

አሁን ሥልጣን ላይ ያሉት ኦ.ሕ.ዴ.ድ (ኦዴፓ) "አሁን የኛ ተራ ነው፣ የሕዝብን ገንዘብ በችግኝ አማካይነት እንዝረፍ" ብለው ዝግጅት የጀመሩ ይመስላል፡፡ እስከ ዛሬ በተለይ የሚሊኒየም በአል ከተከበረ ጀምሮ በየዓመቱ ከፍተኛ የሚባል የችግኝ ተከላ ተካሄደ ሲባል ሰማን እንጂ ምን ያህል ችግኝ ፀደቀ? ዛፍስ ሆነ ወይ? ብሎ የሚከታተል አንድም ተቋም የለም፡፡ 10 ሺ ችግኝ ተተከለ ተብሎ ሪፖርት የሚቀርብበት ሁኔታ መኖሩ ከበቂ በላይ መረጃ አለ፡፡

እንዲያውም ችግኝ ሊተክሉ የሄዱ ሰዎች በሳር የተሸነፈውን ሜዳማ ቦታ መሬቱን እያቆሰሉ ችግኝ እንተክላለን በማለት አፈሩ እንዲሸረሸር ያደረጉበት ሁኔታ መከሰቱን ዞር ዞር ብሎ በማየት ብቻ ማረጋጥ ይቻላል፡፡

የሚሊኒየም በዓል ከተከበረ በኋላ የተተከሉ ችግኞች ወይ ከብቶች ረጋግጠው ከጥቅም ውጭ አድርገዋቸዋል፤ ወይም ደግሞ በሳር ተውጠው፣ ቀንጭረው ቀርተዋል፡፡ በዚህ ችግኝ በማቅረብ ተግባር የተሰማሩ የፓርቲ አባላት በሚሊዮን የሚቆጠር የሕዝብ ገንዘብም ኪሳቸው ከትተዋል፡፡

ኢህአዴግ ሥልጣን በያዘባቸው 28 ዓመታት በዚች አገር በሚያስደንቅ ሁኔታ ያደገ ሳይንስ ቢኖር፤ ከተጠያቂነት ነፃ ሊያደርግ በሚችል መልኩ የሕዝብ ገንዘብ እንዴት መዝረፍ እንደሚቻል ነው፡፡ የችግኙ ፕሮግራምም የዚህ አንድ አካል ነው፡፡

የተከበረውን የሰው አካል የሚያክሙ ዶክተሮች በዓለም እጅግ ዝቅተኛው ገንዘብ የሚከፈልባት አገር ይዘን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ገንዘብ ወደ ፓርቲ አባላት ኪስ እንዲገባ የሚሰራበት አገር ሆናለች ኢትዮጵያ፡፡

የችግኝ ተከላ ውጤታማ የሚሆነው በማኅበራት ወይንም የግል ባለሃብቶች መሬት ተሰጥቶአቸው ፣ ያንን መሬት በችግኝ አልምተው ችግኙ ዛፍ ሲሆን ለመንግስት እንዲሸጡ በማድረግ ብቻ ነው፡፡ ይህ ለባህብቱም እጅግ አዋጭ ሥራ ነው፡፡ የአገራችንን የተመናመነ ደን መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ ያለው ብቸኛ መንገድም ይህ ነው፡፡

ከዚያ ውጭ ችግኝ ባለቤት ሳይኖረው እየተከሉ በሕዝብ ሐብት መቀለድ ቢቆም የተሻለ ነው እላለሁ፡፡ ችግኝ መጠበቅ ያለበት ከቤት እንስሳት ብቻ ሳይሆን በቀንና በሌሊት ከሚንቀሳቀሱ የዱር እንስሳትም ጭምር ነው፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው እያንዳንዱ ችግኝ ታጥሮ ጥበቃ ካልተደረገለት በምንም መልኩ አድጎ ዛፍ አይሆንም፡፡ አገራችን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ እያወጣች የጣውላ ምርት ወደ አገር ውስጥ ታስገባለች፡፡ ያገራችን ተራሮች ደግሞ ደን አልባ ሆነው የድረሱልኝ ጥሪ ያሰማሉ፤ በተጨማሪም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ወጣቶች በስራ አጥነት ሲቸገሩ ይታያል፡፡

ምናለ ወጣቶች በማህበር እንዲደራጁ ቢደረግና መነሻ ብድር ተሰጥቷቸው፣ ተራራማ ቦታዎች በነፃ ተሰጥቷቸው አልምተው፣ ተራራው በደን ሲሸፈን ለክልሉ በመሸጥ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ቢደረግ?

ይህንን ተግባር መፈፀም ከተቻለ በእርግጠኘነት የበረሃ መስፋፋትን እንዋጋለን፣ የዝናብ መጠን ይጨምል፣ የአፈር መሸርሸር ይቀራል፣ የደን ውስጥ ብዝሐ ሕይወት ይበልፅጋል፡፡ ተያይዞም ከካርቦን ንግድ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሬ ማግኘት ይቻላል፡፡

ዓለማችን በአሁኑ ጊዜ በእፀዋት ሊመጠጥ ከሚችል በላይ ጋዝ ወደ ከባቢ አየር እየተለቀቀ በመሆኑ በአገራችን በተራቆቱ ተራሮች ላይ የደን ልማትን ማስፋፋት ከተቻለ በራሱ ለአገራችንን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ ተፈጠረ ማለት ነው፡፡

ወጣቶች ወደ አሸባሪ ድርጅቶች ፊታቸውን የሚያዞሩት መንግስት በቂ ትኩረት ሲነፍጋቸው ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት በየክልሉ ላሉ ወጣቶች በበቂ ሁኔታ የሥራ ዕድል የሚፈጥር በመሆኑ፣ በተጨማሪም ተግባሩ ሲከናወን ያዩ የውጭ ኃይሎች በእርግጠኝነት በቂ ድጋፍ ማድረጋቸው አይቀርም፡፡

በመሆኑም በጠ/ሚ/ር ዐቢይ የሚመራው አዲሱ ኢህአዴግ፤ አሮጌው ኢህአዴግ የሰራውን እኩይ ተግባር መድገሙን ትቶ አገርና ወገንን ሊጠቅም የሚችል ተግባር ላይ ቢያተኩር የተሻለ ነው ፡፡ በአገር መቀለድ ይቁም፡ ፡ ጠ/ሚ/ር ዐቢይ አሕመድ ባላቸው አጭር የስልጣን ዘመን ፤ አራት ቢሊዮን ችግኝ ፕሮጀክት በእኔ እምነት የቅዠት እንጂ የጤና ፕሮጀክት አይደለም፡፡ ይተግበር ከተባለም የተወሰኑ ባለስልጣናት ፎቅ ይሰሩ እንዲሆን እንጂ ውጤት ማየት የሚቻልበት ምንም ሁኔታ የለም፡፡ ምናልባት የችግኙን መትከያ ጊዜ ወደ ተጨማሪ ዓመታት ከፍ በማድረግ " 4 ቢሊዮን ችግኝ በ…… ዓመታት ለመትከል ታስቧል" ቢሉን የተሻለ አመኔታ ያስገኝ ነበር፡፡

**…አሁን ሥልጣን ላይ ያሉት ኦ.ሕ.ዴ.ድ (ኦዴፓ) "አሁን የኛ ተራ ነው፣ የሕዝብን ገንዘብ በችግኝ አማካይነት እንዝረፍ" ብለው ዝግጅት የጀመሩ ይመስላል፡፡ እስከ ዛሬ በተለይ የሚሊኒየም በአል ከተከበረ ጀምሮ በየዓመቱ ከፍተኛ የሚባል የችግኝ ተከላ ተካሄደ ሲባል ሰማን እንጂ ምን ያህል ችግኝ ፀደቀ? ዛፍስ ሆነ ወይ? ብሎ የሚከታተል አንድም ተቋም የለም…**



ኢዮብ ሳለሞት

# የአበራሽን ጠባሳ ያየ በእሳት አይጫወትም !

በአሁን ወቅት እንደሀገር ያጋጠሙን ተግ ዳሮቶች ፤ፈተናዎች ሰዉ-ሰራሽና የተግባቦት ክህሎታችንን ብናጎለብት በቀላሉ ሊፈቱ የሚችሉ እንደ ሀገር፣ እንደ ህዘብ ካለን የታሪክ፣ የባህል፣ የእርስ-በእርስ መስተጋብር ፤ ካዳበርነዉ የግጭት አፈታት ባህሎቻችን በታች ናቸዉ ። ተደጋግሞ እንደተገለጸዉም ህዘብ ለህዘብ ችግር ኖሮ አያዉቅም ። የብሄርን ፣ የቋንቋን ፣ የእምነትን፣ የመልክአ-ምድር ቁርኝትን ያገለደሙ ጠባብ ብሔርተኞች፣ አክራሪዎች፣ ጽንፈኞች፣ ኢሊቶች የግልና የቡድን ፍላጎታቸዉን፣ ጥቅሞቻቸዉን ተገቢ ባልሆነ መልኩ ለማስከበር አልያም ተወዳድሮ ሮጦ ፤ ለፍቶ ባበረከቱበት መጠን የሚያገኙበት ስርአት ቢዘረጋ ዉራ ስለሚሆኑ ልምዳቸዉ ዕውቀታቸዉ ፤ መለያቸዉ ተጥግቶ፣ ተሞዳምዶ ብቻ ማትረፍን ሲለሚያሳይ ወይም የህግ የበላይነት የሚከበርበት፣ አሳታፊ ፣አካታች ዜጎች የበኩላቸዉን ሚና እየተወጡ በጋራ የሚያበለጽጉበት ስርአት ቢሰራ ከተጠያቂነት ማምለጥ እንደማይችሉ ተረድተዉ በርካታ ዘመናትን በመዋለድ ፤ በክፉ በደግ በመደራረስ ፤ በጋራ ስጋት ነፍሱ ዝሎ በጋራ እድል ጮቤ ረግጦ ተፈጥሮአዊ ልዩነቶች (ብሄር፤ቋንቋ) ሳይገድቡት በአብሮነት የጋራ እሴት ያመነጨን ህዘብ የተቆርቋሪነት ካባ ደርበዉ ፤ በሀሰተኛ የቀኝ-ግዢ ትርክት ደምቀዉ አደናግረዉ ፤ አምታተዉ በሚፈጠሩ ቀዉሶች በግለኝነት ፤ በስግብግብነት ያበደ ፍላጎታቸዉን እናስከብራለን በሚል ቀቢፀ-ተስፋ የማይፈነቅሉት ድንጋይ የለም ።

በአራቱም ማዕዘናት ጠባብ ፖለቲከኞች ፤ ጽንፈኞች፤ አክራሪዎች ጋብቻ ፈጽመዉ የመንግስትን አስተዳደራዊ መዋቅሮች አንዳሻቸዉ እየፈነጩ በጽጥታና የፍትህ ተቋማት ዉስጥ እየዋኙ ህዘብን ሲያፈናቅሉ ፤ ሲገድሉ ፤ ሀሰተኛ የተዉሶ ትርክት መርዘኛ ቅስቀሳ ሲረጩ ሓላፊነት የሚሰማቸዉ ዜጎች እጃቸዉን አጣጥፈዉ መቀመጥ የለባቸዉም ። ጠባብ ፖለቲከኞች ጥቂት ተፈጥሮአዊ ልዩነቶችን አንደሃጢአት ቆጥረዉ የቀዉስ ምንጭ ለማድረግ ሲሯሯጡ ሃላፊነት የሚሰማቸዉ ዜጎች ግዙፉን ኢትዮጲያዊነት ተጨባጩን የጨዋዉና አስተዋዩ ሰፊዉ-ህዘብ የተገመደበትን አብሮነት ፤ አንድነት መሰረት አድረገዉ የልማት ፤የብልጽግና እርሾ አድርገዉ መጠቀም አለባቸዉ ። እምቅ የተፈጥሮ ሀብት ፤ ምቹ የአየር ንብረት ፤ የተማረ የሰዉ ክህሎት ፤ ዲስፒሊን ፤ የመሳሪያ አቅርቦት ተዋቅረዉ አደጋ ከተከሰተ በኋላ መግለጫ ከማዥጎድጎድ ተቆጥበዉ አስቀድመዉ የስጋት ቀጠናዎችን በመለየት፣፤ የቅደመ-መከላከል ስርአቶችን በመዘርጋት፣ ፤ ህበረተሰቡን በማሳተፍ ገና አደጋ ሲጠነስስ አፍንጫቸዉ የማሸተት ፤ የማነፍነፍ ጉልበት ኖሮት በተለያዩ ስልቶች መረጃዉ ኖሮዋቸዉ አደጋ ከምንጩ የሚያደርቁበት ፤ የህዘብን ሕይወት የሚታደጉበት ቁመና ላይ እንዲደርሱ ሁላችንም ብንረባረብ የተሻለ ይሆናል። አንድ ሃይል ይዘንና እነዚህን አቀናጅተን ለሁላችንም የምትበቃ፣ የምታሳትፍ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቿ የግጭት መናኸሪያነታቸዉ ታሪክ ሆነዉ በጥናትና -ምርምር ታግዘዉ በሚወለዱ የቴክኖሎጂ አቀርቦቶች የማህበረሰቡን የአኗኗር ዘይቤ የሚያቀሉበት፣ ፖለተከኞቿ ዘር ከልጓም ሳይስባቸዉ በርእዮተ-ዓለም ከደህነት ማምለጫ የኢኮኖሚ ፍልስፍና ፤ በአማራጭ ፖሊሲ ፤ በአመለካከት ጥራት ዙርያ ተደራጅተዉ የሚታገሉበት ሁኔታ ቢፈጠር እንዲሁም የፍትህ ተቋማት በፖለቲካ አመለካከት፣ በወንዜ ልጅ ፣ በጎጥና በፖለቲካ አመለካከት መደራጀታቸዉን እርግፍ አድርገዉ ቢተዉ ይመረጣል። ሙያዉ በሚጠይቀዉ ወጥ ፎኖተ-ካርታ ተዘጋጅቶ ባለድርሻ አካላት (መንግስት፤መንገስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ፤ ፓርቲዎች ፤ የሃይማኖት ተቋማት ፤ የሀገር ሽማግሌዎች ፤ ወጣት አደረጃጀቶች ፤ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ..ወ.ዘ.ተ ) እዛ ላይ ግዚያችንን ፣ ገንዘባችንን፣ እዉቀታችንን ፣ ክህሎታችንን ብናፈስ የምንፈልጋትን ዲሞክራሲያዊት ሀገር ለመገንባት ሚስማር አቀበልን ማለት ነዉ ።

> **. . . በአራቱም ማዕዘናት ጠባብ ፖለቲከኞች ፤ ጽንፈኞች፤ አክራሪዎች ጋብቻ ፈጽመዉ የመንግስትን አስተዳደራዊ መዋቅሮች አንዳሻቸዉ እየፈነጩ በጽጥታና የፍትህ ተቋማት ዉስጥ እየዋኙ ህዘብን ሲያፈናቅሉ ፤ ሲገድሉ ፤ ሀሰተኛ የተዉሶ ትርክት መርዘኛ ቅስቀሳ ሲረጩ ሓላፊነት የሚሰማቸዉ ዜጎች እጃቸዉን አጣጥፈዉ መቀመጥ የለባቸዉም . . .**

ወቅታዊ ተግዳሮታችንን እንደ ምቹ ሁኔታ ተጠቅመዉ ሃያላኖቹ (አሜሪካ፤ሩስያ፤ቱርክ ፤ሳዉዲ ፤ኢራን ፤ ቻይና ...) በተለያየ ፓኬጅ ( በብድር አቅርቦት ፤ በእርዳታ ፤ በእዳ ቅነሳ ፤ በወታደራዊ ድጋፍ ፤ በዲሞክራሲ ስርአት ግንባታ ..) ይቀርቡናል አቡጀዲዉ ሲገለጥ ግን ብሄራዊ ፤ጥቅም የጂ-ኦ ፖለቲካ የበላይነት ፤ ጥሬ-ሀብት ጎልተዉ ይነበባሉ ። በመካከለኛዉ ምስራቅ ፤ በኤደን ባህረ ሰላጤ ፤ በምስራቅ አፍሪካ በደንብ አይተናል ። ቅደመ-አያቶቻችን የቀረቡላቸዉን የጥቅል-አግልግሎት በጥንቃቄ በመክፈት ዉስጣዊ ቁርሾአቸዉን በሀገር-በቀል የግጭት አፈታት ባህል ፍቀዉ ብሄር፣ ቋንቋ ፣ እምነት፣የመልክዓ-ምድር አቀማመጥ ፤ የሃያላኖቹ በተናጥል የሚደርጉት ጉቦና ምልጃ ሳይበግራቸዉ በመረጃ የበላይነት ፤ በወታደራዊ ስልት ፤ በአዉደ-ዉግያ ጀግንነት ሁለንተናዊ ድል በመጎናጸፍ የአለምን የቀለም ቅኖና የሰበረ ፣ ጭቁኖችን አነቃቅቶ ድል እንዲጨብጡ ምክንያት የሆነ ገድል በጋራ አስተዋጽኦ ፈጽመዋል።

ሀገር እንደ ሀገር እንድትቀጥል ቋንቋችንን፣ እምነታችንን፣ እሴቶቻችንን እያበለጸግን እንድንቀጥል መሰረት ጥለዋል። መሳፍንቶች ራሶች የአልጋ (የስልጣን) ጥማቸዉን ገትተዉ ዉስጣዉ ችግሮቻቸዉን ፈተዉ ዓለም ዓቀፉን አሰላለፍ ተገንዘብዉ ፤ ንቃተ-ህሊናዉን አዳብረዉ የሃያላኖቹ አካሄድ ገብቶዋቸዉ ከነተግዳሮቶቻቸዉ አንደሀገር ለሚያያጋጥማቸዉ ተግዳሮት በጋራ ቆመዋል።

እኛም በዘመናችን ያጋጠመንን ተግዳሮት በድርደር በሰጥቶ መቀበል ሁላችንም አሸናፊ ሆነን የምንወጣበት መንገድ በአሻጥርና በሴራ የበለጸገዉን የፖ ለቲካ ባህላችንን በሂደት በማስወገድ ከምንም በላይ ከግለሰብም ከቡድንም ከፓርቲም ጥቅም በላይ የሀገር ህልዉና በማስቀድም ልዩነቶቻችንን የምናስተናገድበትን የተግባቦት ክህሎት በማሳደግ በዓለም-አቀፍ ደረጃ ለሚጠብቀን ተግዳሮት በጋራ እንቁም።

ልዩ ዘገባ



ፍቅርተ ተሾመ

# በወቅታዊ ጡዘቶች የተናጠች ሃገር

ይህች ሃገር በአንድ ጆሮዋ የርዕዮተ ዓለም ገመድ በሌላኛው የፖለቲካ ነጋዴዎች በሦስተኛው ጆሮዋ ለፍቶ አዳሪ ሰላም የተራቡ ዜጎች እሮሮ ገመዶች ተጠምዳ ወዲህ እና ወዲያ ስትናጥ አመታትን እያስቆጠረች አለች፡፡ ይህ ሁሉ መናጥ አሬራው ላይ ደርሶ የሚደፋ እርባና ቢስ ወደ መሆን ተዳርሷል፡፡ አሳላፊው ሆዬ ቅቤውን ለዘመድ፣ አይቡንም ለወዳጅ በጓሮ በር በኩል ተደብቆ ሰጥቶ አሬራው ላይ ሲደርስ ተሰላፊው ሁሉ አላየሁም የታል፤ ቅቤው ከነአይቡ የታለ የወጣው እኛን ከአሬራው የደረሰን ብሎ ቢጠይቅም ናጭ እና አሳላፊ የነበረ ሁሉ ቦታውን በጓሮ በር ለቆ በበሩ በኩል ግን ተሰላፊ ሆኖ አላየሁም የታል እኔስ የድርሻዬ ለምን ተቀንሶ! ፤ ማነው ወንበሩ ላይ አንተ መልስ እንጂ እኛም መብት አለን ይላል አሁን ይሄንን ጉድ ማን ምን ይለዋል፡፡ እኒህ በኢትዮጵያ ውስጥ ሰብሳቢ ያጡ የሚመስሉ የችግር ሽንቁሮች ውይይት፣ እውቀት እና ስራን በአስቸኳይ በቅንጅት የሚፈልጉ ናቸው፡፡ ወቅቱ ለውይይት በር የተከፈተበት ለዚህም ሲባል መንግስት ሆደ ሰፊ ሆኖ ጉልበተኞች ከአመፅ ተቆጥበው ጠመንጃውን አውርደው ሃሳብን አንግበው፣ ተቺዎችም ሃሳባቸውን ይዘው ሁሉም ለመድረኩ ተሳታፊ ሆኖ እንዲወያይና የሃሳብ ግርገባ እንዲደረግ ከአመቻቸ ሰነባብቷል፡፡ ህዝብም ይህን ይለማመድ እና ያበጥር ዘንድ ስራ እንዲሆነው እና በተነዳበት እንዳይሄድ ሁኔታዎች ተመቻችተው የሂደቱ ጀማሪም ሆነዋል፡፡

## የሃሳብ ልዩነቶች

ኢትዮጵያ በሃሳብ ልዩነቶች እየተናጠች ባለችበት በዚህ ወቅት በዋናነት በሁለት የተለያዩ ፅንፎች ስር የሚገኙ ሃገሪቷ ያለችበትን ይዘት ይህ ነው የሚሉ እና መፃኢ ቁመናዋን የሚደነግጉ ሃሳቦች ይቀነቀናሉ፡፡ እኒህ የሃሳብ ልዩነቶች ሁሉም በየፊናቸው ህዝቡን ምሁራዊ ማለትም በጥናት እና ምርምር የተደገፉ እንደአስፈላጊነቱም በስሜት ላይ የተሞረከዘ ውይይቶችን በየቦታው መስተዋል ጀምሯል፡፡ እኒህ ውይይቶች እውነት በሃሳብ ልዕልና ላይ ተመርኩዘዋል? ወይስ አንድ አይነት ሃሳብ ያዘሉቱ ለብቻቸው ተሰባስበው በዚያው ተስማምተው ይለያያሉ? እኒህንና የመሳሰሉትን ሃሳቦችን ‹‹ከፍተኛ ትምህርት ለሰላም ውይይት እና ለሃገራዊ አንድነት›› በሚል ርዕስ ኢንሺኤቲቭ አፍሪካና አክሽን ፎር ሶሻል ዴቨሎፕመንት ኤንድ ኢንቫይሮንመንታል ፕሮቴክሽን ኦርጋናይዜሽን ከመቐለ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር የውይይት መርሃ ግብር ባሳፍነው ሳምንት አዘጋጅተዋል፡፡ መነሻ ይሆን ዘንድም በዩኒቨርሲቲው መምህራን ፅሁፎች የቀረቡ ሲሆን ተማሪዎች እና ሌሎች መምህራን በውይይቱ ተሳትፈውበታል፡፡ በውይይቱ መምህራን ሃሳቦችን አንሸራሸረዋል፤ ተማሪዎች አስተያየት እና ጥያቄዎችን ሰንዝረዋል፡፡ በዩኒቨርሲቲው እንዲህ ያሉ ውይይቶች በተደጋጋሚ የሚዘጋጁ ሲሆን በወቅታዊው የሰላም እጦት እና አነጋጋሪ የርዕዮተ ዓለም ርዕስ ጉዳዮች ላይ ተደጋጋሚ ውይይቶችን ማድረጉ ብሩህ ነው፡፡ በቅርቡም በፕሮፌሰር ሕዝቂያስ ገቢሳ አቅራቢነት ብሔር ተኮር ፌደራሊዝምን ርዕስ ያደረገ ጥናታዊ ፅሁፍ ላይ የነበረው የመምህራን ውይይት የሚታወስ ነው፡፡

አሁን ላይ በአመራሮች ደረጃ እየተመላለሱ የሚገኙት የአማራ እና ትግራይ ክልል የቃላት መገፋፋት ፍልሚያው ፖለቲካዊና አርቴፊሻል ነው፡፡ ይሄ ደግሞ እኔ እንደ ትምህርት አለም ሰው ከብዙ እንቅስቃሴዎቼ እና በሀገሬ በአግባቡ ተዘዋውሬ የጀመርኳቸውን ፕሮጀክቶች በነፃነት እንዳልመራመር አድርጎኛል ገቶኛል በማለት ውይይቱን ያስከፈቱት የዩኒቨርሲቲው ምክትል ፕሬዘደንት ፕሮፌሰር ፈቲን አባይ እኛ ለሰላም ምን አስተዋፅኦ ማድረግ እንችላለን የሚለው በዕለቱ ያሰባሰበው ጉዳይ እንደመሆኑ አፅንኦት ሰጥተውበታል፡፡ ‹‹አሁን ያለው ችግር ባለቤትነቱ የእኔ እና የአንተ የአንቺ ወይንም የአማራ እና የትግራይ ህዝብ አይደለም ስለዚህ ይህንን ችግር የተማረ ህዝብ እንደሌላት ሃገር አብረን ስንጠፋ በዝምታ ነው ማለፍ ያለብን? የለብንም!፣

ማስወገድ እንችላለን? አንችልም! ታዲያስ? መቆጣጠር እንችላለን? አዎ! እንዴት ለሚለው፤ እውቀትን በመጠቀም፡፡

እናንተን የመሳሰሉ ወጣት ተማሪዎች በመላው ሃገሪቷ ይገኛሉ፡፡ ላለብን አስፈሪ ችግር ስትራቴጂዎች ነድፈን ለመፍትሄ መፋጠን አለብን ይሄ ፖለቲከኞችን መተቸት አይደለም እነርሱ ራሳቸውን ሊተቹ ይገባል እኔ የምናገረው እና እኛ እንስራ የምለው ለሰላም የራሴን እና የራሳችንን አስተዋፅኦ ለማድረግ ነው››፡፡ ‹‹ከቆምኩበት ቦታ እንዳልንቀሳቀስ ከተገታሁ ይሄ ችግር አይደለምን? ምኑን ህይወት ሆነ›› በማለት አክለዋል፡፡

## ሰላማዊ ውይይት

ሰላማዊ ውይይት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ ያለው ሚና እና ባህል በተመለከተ ከማህበራዊ ፋይዳ አንጻር በዩኒቨርሲቲው የሶሾሎጂ ክፍለ ትምህርት መምህር የሆኑት ዶ/ር ቀለመወርቅ ታፈረ መነሻ ፅሁፋቸውን አቅርበዋል፡፡

ይህ ጉዳይ አሁን ያለውን ገጽታ ለመግለፅ ታሪካዊ ይዘትን ወደ ኃላ ተመልሶ ማየቱ አስፈላጊ እንደሆነ እና ይሄም ከአሁኑ ሁኔታ ▶

**ዩኒቨርሲቲዎች የልሂቃን መናኸሪያ እንደመሆናቸው የመፍትሄም ምንጭ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ሆኖም አሁን ላይ ተቋማቱ በራሳቸው የችግር መነሻ የውጊያ ቦታዎች ሆነዋል፡፡ የህዝብ ሃብት የሆኑት ዩኒቨርሲቲዎችም የፖለቲካ ፓርቲዎች ሃብት እስኪመስሉ ድረስ የፖለቲከኞች መዋጊያ ስፍራ እስከመሆን ደርሰዋል. . .**

**ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ይህን የሰላም ውይይት መርሆች ነው ማስረፅ ያለበት፡፡ የስነዜጋ እና ስነምግባር ትምህርት በስፋት መሰጠታቸው ጥሩ ሆኖ ሳለ በቂ አይደለም፡፡ በአስቸኳይም በሰላም እና ግጭት አፈታት ዙሪያ ያተኮሩ ኮርሶችን ለመስጠት መዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡**

አንፃር በእጅጉ የተለየ እንደሆነ በመግለፅ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምስረታ ታሪክ ላይ ተንተርሰው የሰላማዊ ውይይት ይዘቶችን ዳስሰዋል፡፡በዘመናዊው ትምህርት የከፍተኛ ትምህርት ምስረታ በንጉሡ ጊዜ እንደሆነ ይታወቃል ይህም በቁጥር ጥቂት ሲሆን በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተጀምሮ ሐረማያ እያለ እየተስፋፋ ሄዷል፡፡ ከ1983 በፊት የፖለቲካው ርዕዮት አሃዳዊ እንደነበር ይታወቃል፡፡ ስለዚህ በወቅቱ የነበሩት መንግስታት አሲሚሌሽን ሞዴል የአስተዳደር ስርዓት ይጠቀማሉ፡፡ ይህም አንድ ሃገር፣ አንድ ባንዲራ፣ አንድ ህዝብ አንድ ቋንቋ የሚል ነበር የሚጠቀሙት ስለዚህ የነበሩት ጥቂት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በዚህ ርዕዮት ላይ የተቃኙ ነበሩ ማለት ይቻላል፡፡ በጊዜው በዩኒቨርሲቲዎቻችንም የነበሩት የለውጥ ጥያቄዎች ሃገራዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ነበር የሚያጠነጥኑት የመብት፣ የዴሞክራሲ፣ የፆታ እኩልነት፣የመሬት ለአራሹ ጉዳዮች ነበሩ በተማሪዎች የሚቀርቡት ጥያቄዎች፡፡ እነኚህ ጥያቄዎች ቢኖሩም ብሔርተኝነት አልነበረም ማለት ግን አይቻልም፡፡ በህቡዕ እና በአደባባይም ጥያቄዎቹ ሲቀርቡ ቆይተዋል፡፡ በኋላም ከ1983 ወዲህ ባለው ጊዜ ስርዓቱ ከአሲሚሌሽን ወይንም አንድ አገዛዝ ወደ ህብረ ብሔራዊነት ተቀይሯል፡፡ በዚህ ላይ ግን በመሃል የነበረው የሽግግር ጊዜ በርካታ ችግሮችን አስተናግዷል፡፡ ሰላማዊም ኢ-ሰላማዊ ጥያቄዎች እና ሃሳቦች ይነሱበት ነበር፡፡ በመሆኑም የውይይት መድረኮች ለግጭት የተጋለጡ ሆነዋል፡፡ እነዚያ ሃሳቦች አሁንም ዩኒየኒስት ወይንም የአንድነት አቀንቃኞች እና ፌደራሊስ ወይንም የፌደራሊዝም አቀንቃኞች ሆነው ትግሎቹ አሁንም ይሰተዋላሉ፡፡ በሁለት ዝሆኖች ጥል የሚጎዳው ሳሩ ነው እንደሚባለው ሁሉ የዚህ ችግር ገፈት ቀማሽ ደኃው ህብረተሰብ ነው፡፡

ዩኒቨርሲቲዎች የልሂቃን መናኸሪያ እንደመሆናቸው የመፍትሄም ምንጭ መሆን ይገባቸዋል፡፡ ሆኖም አሁን ላይ ተቋማቱ በራሳቸው የችግር መነሻ የውጊያ ቦታዎች ሆነዋል፡፡ የህዝብ ሃብት የሆኑት ዩኒቨርሲቲዎችም የፖለቲካ ፓርቲዎች ሃብት እስኪመስሉ ድረስ የፖለቲከኞች መዋጊያ ስፍራ እስከመሆን ደርሰዋል፡፡ ህዝብ በሃብቱ መወሰን ይችላል ለአንዳንድ ችግሮች መንስኤ የሚሆኑ ድርጊቶችም ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ በመኖራቸው ህብረተሰቡ በገዛ ሃብቱ ሰላሙን ያጣል ይሄኔ ህዝብ ያለ እናንተ ሰላም ነበርኩና ሰላሜን ስጡኝ ዩኒቨርሲቲ የሚባለው ነገርም ቅርብኝ ያስብሉታል፡፡

## ሃገራዊ አንድነት

ሃገር በቀል ተቋማት እና እውቀቶች እየተዳከሙ መጥተዋል የሚለው አሁን ላለው ችግር ዋነኛ ምክንያት ነው፡፡ ይህም ሆኖ እየተሸረሸሩ የመጡት ማህበራዊ እሴቶች የሚታደጋቸው አካል መጥፋቱ እንደ ችግር መወሰድ አለበት፡፡ ሰዎች የራሳቸውን ባህላዊ እሴቶች እና እንዲሁም አስተሳሰብና አሰራሮች ችላ በማለት የዘመናዊውን ባህል አስተሳሰብ እና አሰራርን መላመድ እና መተግበርን መርጠዋል፡፡ እነዚህም አስተሳሰብ እና አሰራር ማምጣት በራሱ ችግር አልነበረም ችግር የሚሆነው የሚመጡትን ነገሮች በኮፒ እና ፔስት እንደወረደ ነው የምንናስኬዳቸው ማለትም የራስ ቀለም እና ወዝ አለመስጠቱ አንዱ አስረጂ ነው፡፡ ለምሳሌ የምዕራባዊያኑን አይነት ዴሞክራሲ ማስፈን እንፈልጋለን ነገር ግን ዴሞክራቲክ ተቋማት ማቋቋም ሲባል ግን እንቸገራለን ወይ ብዙ ጊዜ ይፈጅብናል ስለዚህ ሁሌም መንታ መንገድ ውስጥ ነው ምንሆነው፡፡

በአንድ በኩል የራሳችንን አጥተናል በሌላ በኩል ዘመናዊው አሰራር መሬት ላይ ማውረድ አልቻልንም፡፡ ከሁለቱም ያልሆንን መሃል ሰፋሪ ነው ምንሆነው፡፡ ስለዚህ ዩኒቨርሲቲዎች በዚህ ዙሪያ ጥናቶችን እና ምርምሮች እንዲሁም የፖሊሲ ሃሳቦችን ማመንጨት ይኖርባቸዋል፡፡ መንግስትም ጠበቅ ያለ ተገቢውን ቁጥጥር አድርጓል ማለት ያዳግታል፡፡ ይቅርና በፖለቲካ አክቲቪዝም ስም የሚንቀሳቀሱ ሰዎችን እንኳን አደብ ማስገዛት አልተቻለም፡፡ በዚህ ሃገር ከህግ በላይ ለመሆን አክቲቪስት መሆን ይበቃል ምክንያቱም የፈለጉትን ፅፈው እና ተናግረው የሚነካቸውና ሃይ የሚላቸው ሰው የለም፡፡

በዚህ ላይ የመንግስት ቸልተኝነት ጥግ ድረስ ነው ማለት ይቻላል፡፡ አንዳንዴ ከመንግስት አሰራር ውጭ ሊካሄዱ ይችላሉ ግን ቁጥጥሩ ይላላባቸዋል፡፡ ለምሳሌ በክልል አከባቢ ስፖርት ለወዳጅነት ፣ ለፍቅር ፣ለጤንነት፣ ለሰላም ሲባል ነው ያደግነው ሆኖም አሁን ሁኔታው አደገኛ እና አስጊ ነው፡፡ ከስያሜ አንስቶ ከማንነት ጋር የተያያዙ ናቸው እና ምናለበት ሌላ ስያሜዎችን ብንፈልግ ለምሳሌ ታሪካዊ ቦታዎች፣ ጀግኖች እና ልዩ ልዩ እሴቶችን ማሳያ የሚሆኑ አሉ ይሄ ጉዳይ የሚያሻው ጉዳይ ነው፡፡ መዘዙም የዛኑ ያህል አስጊ ነው፡፡ በተደራቢም ሚድያዎች ሰሞኑን እያንፀባረቁ ያሉት ነገር ሃላፊነት ማጣትን ያሳያል፡፡

## ዩኒቨርሲቲዎች ስለ ውይይት

የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በተለይ ጀማሪዎች ትኩረትን ይፈልጋሉ፡፡ አንዳንዶቹ እንደውም የመጀመሪያ አመት ተማሪዎች ገና ከቤተሰባቸው ተለይተው የሚመጡ ናቸው አሁን ባለው ሁኔታ ተማሪዎች አካዳሚክ ከሆነው ነገር ውጭ የሚሰጣቸው ነገር እና እገዛ እጅጉን ያነሰ ነው፡፡ ለምሳሌ የተማሪዎች የድጋፍ አገልግሎት በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች የሚያስፈልግ በጣም ሊሰራበት የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ ወጣቱን በአግባቡ ከተንከባከብነው የእውቀት ችግር ክፍተት እንብዛም ስለማይታይበት የምንፈልገውን መፍትሄ አመንጪ ትውልድ እናገኛለን፡፡ ስለዚህ ወጣቶችን መንከባከብ ላይ የሚሰራ ስራ መስራት አለብን፡፡ ይሄ ደግሞ ችግሩ ከመከሰቱ በፊት እንጂ ችግሮች ከተከሰቱ በኂላ መሆን የለበትም አንዱ ችግራችን ይህ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ችግሮች ሲፈጠሩ መሯሯጥ ይስተዋላል ይሄ ግን አይደለም መሆን ያለበት፡፡ አስቀድመን አናቅድም ችግር ሲከሰት እንሯሯጣለን፡፡ ምዕራባውያን ለሃምሳ እና መቶ አመት ያቅዳሉ፡፡ እኛም እንዲሁ ማሰብ ያለብን ለአሁኑ ወጣት ሳይሆን ከአምስት እና አስር አመት በኃላ ወጣት ስለሚሆነው ነው፡፡ እንዲያው በትንሹ ራቅ አድርገን ማሰብ ካለብን፡፡

ሰላም የማምጣት ኃላፊነት የሁሉም ነው በአንዱ አከባቢ የሚፈጠረው የሰላም እጦት በእኔ አከባቢ ሰላም ስለሆነ ግድ የለኝም የሚል አካሄድ አይሰራም፡፡ በግጭት ፍልስፍና ጎረቤትህ ሲታመስ አንተ ጋር ለተወሰነ ጊዜ ሰላም የሆነ ይመስልሃል ግን ሞልቶ የሚፈስ ነገር አለ ወደ ራስ ቤትም መግባቱ የማይቀር ነው፡፡ አይደለም በኢትዮጵያ ውስጥ ይቅርና በአለም አቀፍ ደረጃ እንኳን ጎረቤት ሃገሮች ውስጥ ችግር ሲከሰት እንኳን ሰላምን መሻት ግድ ነው፡፡ በነገራችን ላይ ሰላም የግጭቶች ሁሉ መጨረሻ ነው፡፡ ማንኛውም ግጭት የሶማሊያም ይሁን የዩጎዝላቪያ መጨረሻው ሰላም ነው ሆኖም በርካታ የህይወት እና የንብረት ዋጋ ያስከፍላል፡፡ ያ አይነት ሰላምን ሳይሆን እኛ መመኘት ያለብን ሰላማዊ ንግግርን ተጠቅመን ችግሮችን መፍታት ይኖርብናል፡፡ ለዚህ ደግሞ እድሎች አሁንም አሉንና፡፡

ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ይህን የሰላም ውይይት መርሆች ነው ማስረፅ ያለበት፡፡ የስነዜጋ እና ስነምግባር ትምህርት በስፋት መሰጠታቸው ጥሩ ሆኖ ሳለ በቂ አይደለም፡፡ በአስቸኳይም በሰላም እና ግጭት አፈታት ዙሪያ ያተኮሩ ኮርሶችን ለመስጠት መዘጋጀት አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲህ ሲደረግ ብቻ ነው የተሟላ ሰብእና ያለው ወጣት መፍጠር የሚቻለው፡፡ ለሰላም ሁሉም ዘብ መቆም አለበት፤ ሃገሪቷ በቂ ችግሮችን አሉዋት እዚህ ህዝብ ላይ ረሃቡና ድህነቱ ሳያንሰው ጦርነት መጨመር ከባድ ያደርገዋል፡፡ ስለዚህ አብረን እንዋኛለን ወይ አብረን እንሰምጣለን በማለት የሶሾሎጂው መምህር ለውይይት መነሾ የሚሆኑ አንኳር ማህበራዊ እይታዎቻቸውን

አስቀምጠዋል።

የዕለቱ ርዕሰ ጉዳይ የሃገራዊ አንድነት ጉዳይ እና አንድ የፖለቲካ እና የኢኮኖሚክ ማህበረሰብ መፍጠር የህገመንግስቱም አንኳር አላማዎች ውስጥ የሚካተቱ ናቸው። ይህን መሰረት በማድረግ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እኒህን ጉዳዮች የመደበኛ ስራቸው አካል አድርገውታል የሚል ጥያቄን ለመመለስ ህጋዊ ድንጋጌዎችን ማየት ተገቢ ነው። በዩኒቨርሲቲው የህግ ትምህርት ክፍል አስተባባሪ የሆኑ ዶ/ር ደስታ ገብረ ሚካኤል ህጋዊ ይዘቱን አብራርተዋል። በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ መሰረት የቅድመ ምረቃን እና ድህረ ምረቃን ትምህርት የሚሰጥ እንደሆነ ያስቀምጣል። በአዋጁ እንደ ትምህርት አላማም ህገመንግስቱን በሚደግፍ መልኩ ትምህርት አሰጣጡ የምርምር ስራዎችንና የማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎችን በጥራት በመስራት ለህዝብ የሰላም እና የዴሞክራሲ ፍላጎትን የማሳካት ሚና እንዳለው ያስቀምጣል።

በአመክንዮአዊ እና ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መርኅ ያለው ምርምር ማድረግን እና ምክንያታዊነት የዩኒቨርሲቲዎች የብቃት መለኪያ ያደርጋል፤ ተቋማዊ ነፃነት ባለበት ይህን በኃላፊነት የመተግበር ተልዕኮ እንዳላቸው በባለሞያው ተገልጧል። ስለዚህ ለትምህርት ሂደቱ መሳካት ሲባል ዩኒቨርሲቲዎች ሃሳብን በነፃነት ሊንሸራሸር የሚያስችል ከሌሎች ተቋማት በበለጠ መብት አላቸው ኃላፊነትም እንዲሁ። አውተንቲክ ውይይት፣ ክርክር እና ተግባቦት ማዕከላት ናቸው። በእርግጥም ውይይት የዘመናዊው የትምህርት አሰጣጥ ፔዳጎጂ አንዱ መንገድ መሆኑ ተዛማጅነቱን ተሳሳቢ ያደርገዋል። ታዋቂው የትምህርት ባለሙያ ፓውሎ ፍሬሪ አስተዋዮችን ለመፍጠር ብቸኛው መንገድ ማስተዋልን የሚፈትነው እና የሚፈልገው ‹‹ውይይት››ን መጠቀም አስፈላጊ ነው ይላል። ይሄ ደግሞ ችግሮችን ማቆም ካስፈለገንና ሃገራዊ አንድነትን ብቻም ሳይሆን ብቁ የሆኑ አስተዋዮችን ለመፍጠር ፔዳጎጂው ወይም የትምህርት አሰጣጡ በራሱ ውይይት ተኮር እና የተለያዩ የውይይት ሃሳቦችን የሚያስተናግድ መሆን አለበት። ተግባቦቱ በራሱ ባህሎችን ያሳተፈ መሆን አለበት። ያለ ውይይት ተግባቦት የለም ያለ ተግባቦት ደግሞ ዋጋ ያለው ትምህርት አለ ማለት አይቻልም ይላል ፍሬሪ አዲስ ምልከታ ለውይይት መቅረብ ይኖርባቸዋል። አንድ አይነት ቀለም ያላቸው ወፎች አብረው ይበራሉ አንዷ ከተነሳች ሌሎችም ይነሳሉ አብረው ይበራሉ ለምን ብለው አይጠይቁም። አንድ አይነት እምነት ያላቸው ሰዎች በአንድ አነጋጋሪ የሆነ ሃገራዊ ጉዳይ ላይ ተሰባስበው ለብቻቸው የተወያዩ እንደሆነ ውጤቱ የከፋ ይሆናል በግላቸው የወሰኑትን ውሳኔ ከነበራቸው በላይ ፅንፈኛ የሆነ ድምዳሜ ይይዛሉ። በግላቸው የሃሳቡን ድክመት ታሳቢ ያደርጉ ከነበረ እንኳን በጋራ ሲሆኑ ግን ይህንንም ድክመቱን ይረሳ እና ፅንፍ ይይዛል። ስለዚህ የተለያዩ ሃሳቦች መንሸራሸራቸው ለመገኘት ያክል ብቻም ሳይሆን የውይይቱ ውጤት የሁሉንም ያማከለ ሁሉንም አሸናፊ ያደረገ ይሆናል።

በመሆኑም እኒህ ሁኔታዎች በሚሟሉበት ጊዜ እምነት እና ማህበራዊ አሴት መገንባት ያስችላል። ማኅበራዊ አሴት መገንባት ሲባል በሶስት ይከፈላሉ። ማህበረሰቡ ከመንግስት ባለስልጣናት ጋር ያላቸው መሰላልን አንዱ ክፍል ነው ሌላው የድልድይነት ሚና የሚጫውት የማህበራዊ አሴት ክፍል ነው ሶስተኛው የጋራ የሆነውን አብሮ አጠንክሮ ማቆየት ነው። ለሶስኛው እንደ ማሳያ ኢትዮጵያን ብንወስድ የክልል አስተዳደር ስርዓት ከመጣ ወዲህ ክልሎች የራሳቸው የሆነ የአስተዳደር ስርዓቶችን ሲዘረጉ እና እርስ በእርስ ያላቸውን ተግባቦት ሲያጠናክሩ በመሃከላቸው ያለውን እምነት ጠንካራ ያደርገዋል ከሌሎች ጋር ያለውን ግን ያላላዋል። ታዲያ ይሄ ብዝሃነትን ሊያማክል የሚችለው ሁለተኛው የድልድልነት ሚና ያለውን ክፍል መጠቀም ሲቻል ነው ይላሉ። በመሆኑም ዩኒቨርሲቲዎች ይህ ብዝሃነት የሚታይበት ተቋም ነው። ጠንካራ ውይይት እና ንግግሮች ከተደረጉበት ደግሞ የተሻለው እና ምርጡ መድረክ ይሆናል ማለት ነው። አሁን ባለው ሁኔታ በአከባቢያችን ተገተን ከራስህ አከባቢ አትልቀቅ የምንባል ከሆነ ግን ሃገራዊ አንድነትን ማሳካት አንችልም።

## ማጠቃለያ

በውይይቱ የመጨረሻ ክፍል ከውይይቱ ተሳታፊዎች የተነሱ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ጥያቄ እና አስተያየቶች ተነስተዋል። በተለየም በአማራ እና ትግራይ ክልላዊ መንግስቶች የነበሩት የቃላት ልውውጦች ስሜታዊ ያደረገኋቸው ተማሪዎች በዚህ ላይ የተመረኮዙ የተለያዩ ሃሳቦችን ሲያነሱ የተሰተዋለ ሲሆን መምህራንም ኮንሰፕቶች ላይ የተሞረኮዙ ጥያቄዎች እና አስተያየቶችን ሰንዝረዋል። ብሔር ተኮር ሃገራዊነት ሲባል ምን ያህል ጥልቀት አላቸው። ለምሳሌ የተለያየ ብሔሮችን የሚወክሉ ግለሰቦች ይኖራሉ ታዲያ ስለ ብሔር ተኮር ሃገራዊነት ስናወራ እነዚህ አካላት ታሳቢ ማድረግ የሚቻልበት መንገድ ምን ሊሆን ነው? ብሔር ተኮር ማንነት ምን ያህል ያስኬደናል ምክንያቱም የደበዘዘ እና ያልጠራ የብሔር አረዳድ ላይ ነን። ገና የገባን ደረጃ ላይ አልደረስንም ገና በጥልቀት ሊታይ የሚገባው ነገር ሆኖ ሳለ ገና የህልም አለም ውስጥ ነን ያለነው ብሔር የሚለውን ሃሳብ ተለዋዋጭነት እና በተለያዩ ብሔሮች የሚገለፁ ማንነት ያላቸውን ሁሉ እና በውስጡ ያቀፋቸው የተዳፈኑ ያልጠሩ ሃሳቦች አሉ።

ሌላው በውይይት ላይ የተነሳው ሃሳብ ውይይት በተፈጥሮው እንዴት እንደሚጀምር ሊታወቅ ይችላል እንጂ እንዴት እንደሚቋጭ ማወቅ አይቻልም የራሱ የሆነ መንፈስ አለው። ልዕልና ያለው ሃሳብ እየገነነ ይሄዳል ደካማው ሃሳብ ደግሞ ማደግ አይችልም እየወደቀ ይሄዳል። በሌላኛው ታዳሚ የተነሳው ሃሳብ የዘረኝነት ጉዳይ ነው ዘር ብለን ስናወራ ሰው ከመሆን መጀመር ይኖርብናል። ሰውነታችንን ሳንቀበል ከጀመርን ችግር ነው ምክንያቱም ሰውነትን ካልተገነዘብን ወይ እንስሳ ነን አልያ ተክል ነን። ከዚህ ተያይዞ የሚጎድለው ነገር ስነ ምግባር ነው እየተሰጠ ባለው የስነ ምግባር እና ስነ ዜጋ ትምህርት ተማሪዎች ስለ መንግስት አወቃቀር እና ህገመንግስት እውቀት አላቸው ሆኖም የስነ ምግባር ትምህርቱ ላይ ግን አሁንም ጎዶሎ አለ። በትምህርት ሂደት ውስጥ የምናሳድገው እውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከት ነው። አሁን ላይ የመጨረሻው አመለካከለት የሚለውን ነገር ከትምህርታችን ውስጥ ጎድሎ የቀረ ይመስላል። ይሄን ለማስተካከል ካሪኩለሙን መፈተሽ ያሻል። እንደማህበረሰብ በሁሉም ሰው ላይ አቋራጮችን መጠቀም የረበበብን ይመስላል። አንድ ተማሪ ወደ ትምህርት ቤት ሲመጣ መፅሃፍ ነው ማንበብ ያለበት ወይንስ አጤሬራ ወይም የተዘጋጁ ማስታወሻዎችን ማንበብ ይበቃናል። እራሳችንን እያታለልን ነው ያለነው ይሄን ራሳችንን በመመርመር ማወቅ ይኖርብናል። ሁሉም ሰው ወደ ሌሎች ይጠቁማል ሌላውን መኮነን ራስን መመርመር አስፈላጊና ተገቢ ነው። ራስን መመርመር ከመጥፎ ጋር ላለመተባበር ያስፈልጋል የመፍትሄ ጅማሮው ነውና። ጥቅም፣ ፍርሃት፣ ራስን አለመሆንና አለአግባብ ለመበልፀግ ከመፈለግ የሚመጣው ማስመሰልና ለመጠጋት መሞከር ሌላኛው አሳሳቢ አካሄድ ናቸው። ቆም ብሎ በአመክንዮ ነገሮች አለማየት እና አለመረዳት ላይ አተኩረን ነገሮችን ለመረዳት ብንሞክር በጋራ ለመኖር ይረዳናል ብለዋል።

ሀገር በህብረ ብሔራዊ ፌደራሊዝም እንደ አዲስ መስርተናል እንጂ የነበረ የምናስቀጥለው ሃገር የለንም። ይሄ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ሀገር ነው የሚሉ ሃሳቦችም በዩኒቨርሲቲው በጥናት ተደግፈው የቀረቡ ሲሆን አሁን ደግሞ ሃገር አንድነትን ከሰላም ጋር አጣምሮ ሊኖር የሚገቡ ሚናዎች ላይ በዩኒቨርሲቲው ቅጥር ውይይት መደረጉ ቀጥሏል። ይህ የውይይት መድረክ በዩኒቨርሲቲው እና ተባባሪ አካላት ቅንጅት ቀጣይ ውይይቶችን ለማድረግ አቅዷል። ከታዳሚዎች በተሰጠው አስተያየትም እንደተገለፀው ሃሳቦች በውይይት ይንገዋለላሉ እንክርዳዶቹም ይደፋሉ። እንክርዳዶቹን ከእህሉ ለመለየት ማበጠሪያ ሰፌድ ተዘጋጅቷል የማበጠር ጥበቡ ለህዝብ ተሰጥቷል።

**. . . በአመክንዮአዊ እና ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መርኅ ያለው ምርምር ማድረግን እና ምክንያታዊነት የዩኒቨርሲቲዎች የብቃት መለኪያ ያደርጋል፤ ተቋማዊ ነፃነት ባለበት ይህን በኃላፊነት የመተግበር ተልዕኮ እንዳላቸው በባለሞያው ተገልጧል . . .**

# "አወዛጋቢው" ዕጩ ፕሬዚዳንት ማናቸው?

ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም በአማራ ክልል ርዕሰ ከተማ ባህር ዳር "የመንፈቅለ መንግሥት ሙከራ" በተባለው አስደንጋጭ ክስተት የክልሉ ርዕሰ መስተዳር የሆኑት ዶ/ር አምባቸው መኮንንን ጨምሮ ሌሎች የክልሉ ከፍተኛ የሥራ ኃላፊዎች ከተገደሉ በኋላ የአማራ ክልል ምክር ቤት እና የክልሉ ገዢ ፓርቲ አዴፓ ለ22 ቀናት ያለፕሬዚዳንትና ሊቀ መንበር መቆየታቸው የሚታወቅ ሲሆን፣ ሰሞኑን በተካሄደ አስቸኳይ ጉባኤ አዳዲስ ዕጩዎችን ወደፊት አምጥቶ በዋና ዋና የአመራር ቦታዎች ለመመደብ ምርጫ ተካሂዷል፡፡

ይሁንና ለክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ፕሬዚዳንትነት የቀረቡት አቶ ተመስገን ጥሩነህ ከዚህ ቀደም በክልሉና በፌደራል መንግሥቱ የአስተዳደር ዘርፎች ውስጥ ስማቸው በጉልህ የሚነሳ ሆኖ ካለመቆየቱ ጋር ተያይዞ ዕጩነታቸው ከተሰማ በኋላ በበርካታ የክልሉ ተወላጆች፣ ጦማሪያንና አክቲቪስቶች "የት ነበሩ?" ከሚለው ጥያቄ ጀምሮ "የማናውቀው ሰው መሾም የለበትም!" እስከሚል የደረሰ የተቃውሞ ሀሳብ በመንሸራሸር ላይ ይገኛል፡፡

ዕጩ ተሿሚ ሆነው በመቅረባቸው ከወዲሁ የክልሉ ተወላጆች ንትርክ ውስጥ የገቡባቸው አቶ ተመስገን ጥሩነህ በብዙዎች ዘንድ "የትነበሩ?" የሚል ጥያቄ ቢቀርብባቸውም ለፕሬዚዳንትነት መታጨጣቸውን ተከትሎ የክልሉ ም/ቤት እና ገዥ ፓርቲው አዴፓ ሰውየውን በሚመለከት ያወጧቸው የግል ማህበር መረጃዎች ግን "የት ነበሩ?"ለማለት ድፍረት የሚሰጡ ሆነው አልተገኙም፡፡ ይልቁንም እኚህ ታላቅ ሰው በልዩ ልዩ የመንግሥት ከፍተኛ የሥራ ሀላፊነቶች ውስጥ የቆዩና ሀላፊነታቸውን በብቃት ሲከውኑ የነበሩ መሆናቸውን ነው መረዳት የሚቻለው፡፡

## አቶ ተመስን ጥሩነህ ማን ናቸው?

በጎጃም ክፍለ ሀገር ቢቸና ደብረወርቅ ከተማ ልዩ ስሙ ወይራ በተባለው አካባቢ የተወለዱት አቶ ተመስገን ጥሩነህ በአማራ ክልላዊ መንግሥት ሥር በሚገኙ ልዩ ልዩ መ/ቤቶችና ተቋማት ለረዥም ጊዜ በከፍተኛ የሃላፊነት ቦታዎች ሲሰሩ ከመቆየታቸውም ባሻገር በፌደራል መንግሥቱ ታላላቅ ተቋማት አስቸጋሪ በሚባሉ የሥራ ኃላፊነቶች ውስጥም እጅግ አንፀባራቂ ውጤታማ ግልጋሎቶችን ሊያበራክቱ የነበሩ እንደሆኑ በስራ ጓደኞቻቸውና በቅርበት በሚያውቋቸው ዘንድ ምስክርነት ሲሰጥላቸው ይሰማል፡፡ በተለይ ለአዳዲስ ቴክሎኖጂዎችና የሳይንስ ግኝቶች ቅርብ በመሆን ሀገራችን ከእነዚህ የዓለም በረከቶች የድርሻዋን ተቋዳሽ እንድትሆን እጅግ ጠንካራ እንቅስቃሴና ጥረት በማድረግ ውጤታማ ተግባራትን መከወናቸው እንዲሁም ባለትዳርና ከመሆናቸውም በተጨማሪ በግል ባህሪያቸው ቁጥብና ነገሮችን በጥልቀት



የመመርመር ዝንባሌ የሚንፀባረቅባቸው እንደ ሆኑ ይነገርላቸዋል፡፡

## አቶ ተመስገን በአማራ ክልል ውስጥ

ቀደም ባለው ጊዜ ይበልጡንም ከዶ/ር አምባቸው መኮንን ርዕሰ መስተዳደርነት መምጣት በፊት በነበረው የክልሉ መንግሥታዊ የአስተዳደር መዋቅር ውስጥ በልዩ ልዩ የሥራ ሀላፊነቶች ሲሰሩ የቆዩት አቶ ተመስገን ጥሩነህ በክልሉ ካገለገሉባቸው የስልጣን ሹመቶች በቀዳሚነት የሚጠቀሰው የርዕሰ መስተዳድ የፀጥታና ቴክኖሎጂ አማካሪ ሆነው የሰሩበት ነው፡፡

በዚያ የሥልጣን ዘመናቸው የአማራ ክልል የፀጥታ ሁኔታ ፍፁም ሠላማዊና የተረጋጋ፣ የህዝቡ ደህንነትም የተረጋገጠና ከስጋት የፀዳ እንዲሆን ለማስቻል በተሰራው አድካሚ ሥራ ውስጥ ቀዳሚ ተሳታፊ የነበሩ ከመሆናቸው ባሻገር የክልሉ ፀጥታ ሀይል የዘመናዊ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ እንዲሆን ይበልጡንም የግንኙነት መረቡ የዘመነና አለም የደረሰበትን የቴክኖሎጂ ልህቀት የሚረዳና የሚጠቀም እንዲሆን ማስቻል ላይ ብርቱ ጥረት ሲያደርጉ እንደቆዩ ተነግሮላቸዋል፡፡

የአማራ ገጠር መንገዶች ባለስልጣን ምክትል ሥራ አስኪያጅ ሆነው በተሾሙባቸው ጊዜያት በመንገድ እጦት ችግር ለከፋ ጉዳት ተደርጎ የነበረውን የክልሉ ህብረተሰብ ተጠቃሚ ያደረጉ ትልልቅ የመንገድ ፕሮጀክቶችን ከእቅድ ጀምሮ እስከ አፈፃፀም ድረስ ሲመሩና በቅርብ ሆነው ሲከታተሉ የነበሩ ሲሆን፣ ወደ አማራ ገጠር መንገዶች ኮንስትራክሽን ኤጀንሲ ዋና ስራ አስኪያጅነት ከተዘዋወሩም በኋላ በቀደመው ሀላፊነታቸው ጊዜ የጀመሯቸውን ተግባራት አጠናክረው በመቀጠል የክልሉን ሰፊ የህብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ እንዲሆን አስችለዋል፡፡

ከዚያም የምስራቅ ጎጃም ዞን ዋና አስተዳዳሪ በመሆን በውልደትና ዕድገት በሚያውቁት የአካባቢው ተወላጅ መሀል ተገኝተው በርካታ ማኀበራዊ ልማቶችን፣ የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን፣ የትምህርትና ጤና ተቋማትን እንዲገነቡ ከማስቻል አልፈው ዞኑ በፀጥታና ዘላቂ ሰላም በኩል የላቀ ውጤት የታየበት እንዲሆን ማድረጋቸው በግል ማህደራቸው ሰፍሮ ይገኛል፡፡

የአማራ ክልል ፖሊስ ኮሚሽን ኮሚሽነር ሆነው በሰሩበት ወቅትም የክልሉ ህዝብ ለህግና ተጠያቂነት መርሆዎች ተገዢ እንዲሆን በማስቻል፣ ፖሊስና ህብረተሰቡ የአንድ ሳንቲም ሁለት ግልባጮች እንጂ ሆድና ጀርባ እንዳልሆኑ ግንዛቤ በመፍጠር፣ የፖሊስ ሀይሉን አቅም በማሳደግ ክልሉ የህገወጦች መፈንጫ እንዳይሆንና ህግና ስርዓት የሁሉም ነገር ገዢ መሆናቸውን በተግባር በማስመስከር በኩል ውጤታማ እንደነበሩ ይጠቀሳል፡፡

## በፌዴራል መንግሥቱ ውስጥ፡-

አቶ ተመስገን ጥሩነህ ከአማራ ክልል ልዩ ልዩ የሥራ ሃላፊነቶች ለቀው ወደ ፌደራል መንግሥቱ ከፍተኛ የሥራ ዘርፎ ሲመጡ በቅድሚያ የሰሩበት መ/ቤት የመረጃ መረብ ደህንነት ኤጀንሲ (ኢንሳ) ሲሆን፣ በዚህ መ/ቤት ውስጥ እስከ ዋና ዳይሬክተርነት የዘለቀ ትልቅ ሀላፊነት ነበራቸው፡፡ ከአሁኑ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ጋር በዚህ መ/ቤት ውስጥ አብረው መስራታቸውና የጠበቀ ወዳጅነት እንደነበራቸውም ይነገራል፡፡ በዚህ ተቋም ውስጥ በነበሩ ጊዜ አቶ ተመስገንና ዶ/ር ዐቢይ በህወሓት ሰዎች ብርቱ ተፅዕኖዎች እንደነበሩባቸውና አሁን መቀሌ መሽገዋል የሚባሉት የተቋሙ ሀላፊ ከዋና ዳይሬክተርነት ሀላፊነታቸው ያለበቂ ምክንያት እንዲነሱ ጫና ማሳደራቸውም ሲነገር ይደመጣል፡፡

በኢትዮ ቴሌኮም ሥራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ የነበሩት አቶ ተመስገን በሀገር መከላከያ ሠራዊት ውስጥ የመረጃ ዋና መምሪያ እንዲሁም የኤሌክትሮኒክስ እና የቴክኖሎጂ መረጃ መምሪያ ሀላፊ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን በውትድርና ዘርፍም እስከ ሻለቃ ማዕረግ መድረሳቸው ይጠቀሳል፡፡ ሰሞኑን የአማራ ክልል መንግሥት ፕሬዚደንት እንዲሆኑ በእጩነት መመረጣቸው እስከታወቀበት ድረስ ከአዲሱ የለውጥ መንግሥት ጋር በተለይም መረጃና ደህንነትን በሚመለከቱ ወሳኝና ቁልፍ ጉዳዮች የዜግነት ግዴታቸውን ሲወጡ የነበሩት አቶ ተመስገን የጠ/ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደህንነት አማካሪ ሆነው ሲያገለግሉ እንደነበርም ታውቋል፡፡

በኮምፒዩተር ሳይንስ የትምህርት ዘርፍ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የያዙትና በተቋም የለውጥ አመራር ሣይንስ ሁለተኛ ዲግሪያቸውን የተቀበሉት አቶ ተመስገን ጥሩነህ የፊታችን ሰኞ በባህርዳር ከተማ የአማራ ክልል ም/ቤት አዳራሽ በሚከናወን ሥነ ሥርዓት ቃለ መሀላ ፈፅመው የአማራ ክልል መስተዳድር ፕሬዚዳንትነት ሹመትን በክብር ይቀበላሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

## “እንደ ሀገር ...

*ከገጽ 5 የዞረ*

ዛሬ ክልል እንሁን እያሉ የሚጮኹት ሰዎች በጥቅም የተያዙ ናቸው። ተበታትነን ልናልቅ እኮ ነው። በእኛ አገር ያለው ሰንደቅ ዓላማ ብዛት ራሱ ያሳዝናል። ሁሉም ክልል ነኝ እያለ የራሱን ባንዲራ ይሰቅላል። ምን ማለት ነው ይሄ? አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የአገር ሉዓላዊነት ሳይሆን የብሔር ሉዓላዊነት ነው፤ “የብሔር የበላይነት” ነው የሚታየው። አገር ማለት እንደ ዳቦ ወይም ውሃ ተሰልፈህ የምታገኘው ነገር አይደለም። ከዚህ በኋላ ሁሉም በየፊናው እየተሰለፈ ልከፋፈል እንዳይል መንግስት አስተካካይ ህግ መቅረፅ አለበት።

**ግዮን፡- ባለፈው የመጣህ ጊዜ ለውጡ ጋምቤላን አላከተተም ብለህ ነበር፤ በቅርቡ ደግሞ በርካታ የክልሉ ሓላፊዎች ተነስተው በአዳዲስ ተተክተዋል። አሁንስ ለውጡ ገና ጋምቤላ አልደረሰም?**

ኦባንግ፡- ለእኔ አሁንም ጋምቤላ ለውጥ የለም። ከዚህ በፊት ማለትም ከአስራ ስድስት ዓመት በፊት አገር ውስጥ በነበርኩበት ጊዜ ያለው ሲስተምና ሰዎች አሁንም በስራ ላይ አሉ። የተለወጠ ነገር የምለው ለዚህ ነው። በርግጥ የክልሉ ፕሬዚዳንትና ም/ፕሬዚደንት ተለውጠዋል፣ ያ ለውጥ ደግሞ ሕዝብ የሚፈልገው ዓይነት ለውጥ አይደለም። የጥቂት ሰዎችና የፌደራሉ መንግስቱ ፍላጎት ብቻ ነው የተተገበረው።

ለማ መገርሳ የኦሮሚያ ክልል ፕሬዚደንት ሆነው ሲሾሙ፤ እዛ አካባቢ ያሉ ብዙ ሰዎችና የአሰራር ሲስተሙ ተለውጦ እንደነበር እናስታውሳለን። ሙስጠፋ በሶማሌ ክልል ፕሬዚደንት ሆኖ ከተመረጠ በኋላ በዛ ክልል ውስጥ የተለያዩ መንግስታዊ መዋቅር ላይ ከነበሩ አመራሮች ውስጥ 92% የሚሆነውን አባሮ በአዲስ ነው የተካው። ጋምቤላ ግን አሁንም ሁሉም እንዳሉ ናቸው፤ ማንም አልተነካም። ጋምቤላ ውስጥ ሰዎቹ ሹመኛ የነበሩት በዕውቀት ሳይሆን በብሔር ነበር።

**ግዮን፡- በክልሉ የምትለው ዓይነት ጠንካራ ዕርምጃ ለመውሰድ ያስቸገረው በሰው ኃይል ዕጥረት ነው?**

ኦባንግ፡- የሰው ኃይል ዕጥረት ፈፅሞ የለም፤ መች በሩ መጀመሪያውኑ ተከፈተለትና? ከላይ ያሉት አመራሮች ናቸው የችግሩ ምንጭ። እነዚህ ሰዎች እኮ በሕዝብ አይደለም የተመረጡት፤ እንዴት እንደተመረጡ እንኳን አናውቅም። የተወሰኑ በሙስና የተዘፈቁ ሰዎችን አባረህ ሌሎቹን መተው እኮ በራሱ ብቻውን የጋምቤላ መሪ አያስብልም። ልማት የሚባል ነገር በክልሉ የለም፤ መሬቱን እነማን እንደተቀራመቱት ይታወቃል።

አሁን በጋምቤላ ሰላም የሚባል ነገር የለም፤ በየቦታው ሰዎች እየሞቱ ነው። እዚህ አዲስ አበባ ያሉ መንግስታዊ አመራሮችም ሆኑ ህዝቡ ይህን አያውቁም። ግን እውነቱን ለመናገር በየሁለት ቀኑና በየሳምንቱ በጋምቤላ ሰዎች መሞታቸው የተለመደ ክስተት ሆኗል።

**ግዮን፡- የመሞቻቸው ምክንያት ምንድን ነው?**

ኦባንግ፡- በአገሪቱ የመጣው ለውጥ እንዲቀለበስ የሚፈልጉና ሕወሓት ያሰማራቸው ሰዎች በየቦታው የሞከሩት እንቅስቃሴ አልሳካ ሲላቸው፤ አሁን ወደ ጋምቤላ ፊታቸውን እያዞሩ ነው። እነዚህ ለጥፋት የተመዱበትና ጋምቤላ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች አጠገባቸው ደቡብ ሱዳን ስላለ እንደፈለጉ እየገቡ እየወጡ ነው የሚንቀሳቀሱት። እነሱ የተለያዩ ችግሮችን እየፈጠሩ፣ የሰዎች ሕይወት እንዲጠፋ አድርገዋል።

ከዚህ በፊት እንደሚባለው የአኝዋክና የኑዌር ብሔር ግጭት አይደለም። እነሱ ተጋብተውና ተዋልደው ለዘመናት የኖሩ ናቸው። ፖለቲከኞቹ ራሳቸው ስልጣን ላይ ተደላልድው ለመቀመጥ፣ ከዛም ከፍሲል ባለፈው የኋላ ጥፋታቸውና ሌብነታቸው ተጠያቂ ላለመሆን ሁልጊዜ ችግር እየፈጠሩ ናቸው። ከጥቂት ቀናት በፊት የሆኑ ግሩፖች አሮጊት ገድለው፣ እጇን ቆረጡ፤ ግን እነዚህ ገዳዮች ተያዙ። ሟች የአኝዋክ ብሔር ተወላጅ ነች። ፖሊስ ጣቢያ ድረስ በመሄድ እነዛን የታሰሩትን ገዳዮች በግድ ወሰዱ። ይሄ ምን ዓይነት ነገር ነው? ህግ ባለበት ቦታ እንዴት እንዲህ ይሰራል? ከዚህ በፊት በአኝዋኮችና በኔዌሮች መሀል ግጭት ሲፈጠርና ሲታሰሩ አኝዋክ እስረኞችን ዕሥር ቤት ድረስ ሄደው የመረሸን ነገር ነበር።

አሁንም ከዛ አልፀዳም። አኝዋኮች ኑዌር ወዳሉበት ቦታ አይሄዱም፣ ኑዌሮችም አኝዋክ ወዳለበት ቦታ አይመጡም። ይሄንን ልዩነት ያሰፉትን ያቀጣጠሉት ጥቂት ሰዎች ናው። ለውጡ እንዲቀለበስ ከሚፈልጉት ከእነዚህ የፖለቲካ አመራሮች ባሻገር በደቡብ ሱዳን የሪክ ማርቻል ግሩፕ ውስጥ ያሉ ሰዎችም ጋምቤላ ላይ የተለየ ፍላጎት አላቸው።

**ግዮን፡- ምንድን ነው የእነዚህ የደቡብ ሱዳን ኃይሎች ፍላጎት?**

ኦባንግ፡- ኢትዮጵያ እንደ ሀገር መቀጠል ካልቻለችና ከተበታተነች እኛ ጋምቤላ ሄደን እንቀመጣለን፣ በዛ ደግሞ እንጠቀማለን ብለው ነው የሚያስቡት። እነሱ ጋምቤላ የኢትዮጵያ ሳይሆን የደቡብ ሱዳን ነው እያሉ ናቸው። የራሳቸው አገር ችግርን ትተው ኢትዮጵያ ላይ ትኩረት አድርገዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ከደቡብ ሱዳን በጣም ከፍተኛ ሕዝብ በስደት ወደ ጋምቤላ እየገባ ነው። እዚህ ላይ የፌደራል መንግስቱ ያለው አቋምና አመለካከት አልገባኝም።

ጋምቤላ ውስጥ ያለው ነገር ያሳዝናል። የክልሉ ነዋሪ 360 ሺኅ ነው፤ ስደተኞቹ ግን 700 ሺህ ደርሰዋል። ለዜጎቹ የሚቆረቆርና ኃላፊነት የሚሰማው መንግስት እንዲህ ዓይነት የጎረቤት አገር ነዋሪዎች ፍልሰት ሲከሰት የሚስደው ዕርምጃ ሊኖር ይገባ ነበር። ነገ ሪፈረንደም ይካሄድ ቢባል፣ እነዚህ ስደተኞች ድምፃቸውን ለሱዳን በሚያደላ መንገድ የማይሰጡበት ምክንያት አይኖርም። አኗኗራቸውም ራሱ ህጋዊ መስመር የተከተለ ሳይሆን እንደፈለጉ እየገቡና እየወጡ፣ ባሻቸው መንገድ ነው የሚኖሩት።

**ግዮን፡- ይሄንን የስደተኞቹን ፍሰት ለማስቆም ምንድን ነው መደረግ ያለበት ትላለህ?**

ኦባንግ፡- የኢትዮጵያ ምድር እኮ ጋምቤላ ብቻ አይደለም። መንግስት፤ ስደተኛ የሚፈልግ ከሆነ ለምንድነው ነው ወደ ትግራይ የስደተኞች ካምፕ የማይወስደው? ለምንድን ነው ወደ ኦሮሞና አማራ ክልሎች የማይወሰደው? ደቡብ ውስጥ ባሉ የተለያዩ ቦታዎች ስደተኞቹ እንዲሰፍሩ የማይደረገውስ ለምንድን ነው? ኢትዮጵያ ከሚገቡ ስደተኞች ሀምሳ ፐርሰንቱን ጋምቤላ ብቻ የምትሸከመው ለምንድን ነው?

ዛሬ በክልሉ የሚታዩትን ተደጋጋሚ ግጭቶችን የሚፈጥሩት ደግሞ እነሱ ናቸው። ነዋሪውን ሰላም እየነሱ ያሉት ስደተኞች ናቸው። ስደተኛ የትም አገር እንደሚደረገው በትክክለኛ መንገድ ተመዝቦና መጠለያ ለሚሰጠው አገር ህግ ተገዢ ሆኖ ነው መኖር ያለበት። እኔ በሰብዓዊ መብት ዙሪያ የምሰራ እንደመሆኔ መጠን ሰዎች እንዲጎዱ አልፈልግም። ግን እንዲሁ ደቡብ ሱዳንና ጋምቤላ ስለሚመሰሰሉ፣ ወይም መሬቱ ለም ስለሆነ ነው የሚሉ አስተያየቶችን እሰማለሁ፤ ይሄ ስህተት ነው። ስደተኛ በትክክለኛ መንገድ ስደተኛ ሆኖ ነው መግባት ያለበት፤ እዚህ ሰዎች እኮ ዜጎች አይደሉም። ይሄን ህጋዊ መስመር ተከትሎ ማስኗዝ የመንግሥት ሓላፊነት ነው፤

ከዚህ በፊት ስልጣን ላይ የነበሩት የኢትዮጵያ መሪዎች የጋምቤላ ጉዳይ አይጨንቃቸውም። ሩቅ ያሉ፣ ጫካ የተቀመጡ፣ ኋላ ቀር ሰዎች አድርገው ነው የሚመለከቱን። አሁንም ይሄ ነገር ቀጥሏል። በጣም ነው የማዝነው፤ ጋምቤላ ውስጥ የተሰራው ስራ ኦሮሚያ ውስጥ ቢሆን ይፈቅዱ ነበር ወይ? አማራ ክልል ቢሆን ይፈቅዱ ነበር ወይ?

**ግዮን፡- የጋምቤላ ተወካይና አመራሮች ይህ ነገር እንዳይከሰት ብሎም ለክልላቸው ሕዝብ ተቆርቋሪ መሆን ያልቻሉት ለምንድን ነው?**

ኦባንግ፡- በዚህ ረገድ የጋምቤላ ህዝብ ሁሌም የአቅማቸውን ይሞክራሉ። መንግስት ግን የክልሉን የጩኸት ድምፅ አይሰማም። የጋምቤላ ሕዝብ የሚፈልገውን መሪ ሕዝቡ እንዲመርጥ የፌደራል መንግስት ቢያደርግ ምናለበት? ሕዝብ ደንቆሮ አይደለም፤ የሚጠቅመውንና የሚጎዳውን ጠንቅቆ ያውቃል። በህዝብ የሚመረጠው ትክክለኛው መሪ ነው እንዲህ ዓይነት ነገሮችን ማስተካከል የሚችለው።

ፌደራል መንግስት እዚህ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መስራት አለበት። በተለይ እነዚህ ስደተኞች ነገ የከፋ ችግር ሊፈጥሩ ይችላሉ። በቅርቡ በአማራ ክልል የደረሰው አሳዛኝ ችግር ጋምቤላ ውስጥ ላለመሳካቱ ማረጋገጫ የለንም። ጋምቤላ ውስጥ በኢትዮጵያዊያኑና ከደቡብ ሱዳን በመጡት ነገ ጦርነት በመሀላቸው ሊፈጥሩ ይችላሉ ብሎም መስጋት ተገቢ ነው። ስለዚህ መንግስት ሲሪየስ እርምጃ በፍጥነት በጉዳዩ ላይ መውሰድ አለበት ብዬ ነው የማምነው።

**ግዮን፡- ጋምቤላ ያለችበትን ችግር በስፋት እያየህ ነውና ካለህበት ከሰብዓዊ መብት ተሟጋችነቱ ወደ ፖለቲካው በመግባት መፍትሄዎችን ለማበጀትና የራስህን አስተዋፅኦ ለማድረግ አላሰብክም?**

ኦባንግ፡- ከበፊትም ጀምሮ ፖለቲከኛ▶

መሆን የእኔ ፍላጎት አይደለም፤ በያዝኩትና በጀመርኹት መንገድ እስከ መጨረሻው መጓዝ ነበር ሀሳቤ፡፡ ግን በዚህ ደረጃ ሰዎች ሲሰቃዩ ሳይ ግን ሳልወድ በግድ ፖለቲከኛ መሆንን እንዳስብ እያደረገኝ ነው ማለት እችላለሁ፡፡ ሰዎችም ፖለቲከኛ እንድሆን እየገፋፉኝ ነው፡፡

**ግዮን፡- ካለህ ዓለም አቀፍ ግንኙነትና ተሰሚነት አኳያ የጋምቤላ ችግርን ሊፈታ የሚችል አማራጭ ሀሳብ ይዞ የሚቀርብ የፖለቲካ ፓርቲ የመመስረትስ ሀሳብ የለህም?**

ኦባንግ፡- አስባለሁ፡፡ እንዳልከው በዛ መንገድ ብጓዝ ብዙ ነገሮችን ማስተካከል እችላለሁ፤ ይሄ ምንም ጥያቄ የለውም፡፡ ግን ከዚህ በፊት የፖለቲካ ስልጣን የመያዝ ፍላጎት የለኝም፡፡ ከምንም በላይ ደግሞ ለኢትዮጵያ አይጠቅምም በምለው የብሔር ፖለቲካ ውስጥ ራሴን መክተትም አልፈልግም፡፡ በጋምቤላ ዙሪያ የሚሰራ ፓርቲ ባቋቁም፣ የሃሳብና ሲቪሊያን ድርጅት ሳይሆን የብሔር ተቋም ነው የሚሆነው፡፡ እንዲህ ዓይነቱን ዘር ላይ የተመረኮዘ የጥላቻ ፖለቲካ ደግሞ እኔ አልወድም፡፡

**ግዮን፡- ቀደም ሲል በገለጽከው መሠረት ጋምቤላ የነዋሪዎቿን ብዛት እጥፍ በሆነ የደቡብ ሱዳን ስደተኛ መወረሯን ተከትሎ በግልህም ሆነ አንተ በምትመራው ድርጅት አማካይነት ምን ለመሥራት አስበሃል?**

ኦባንግ፡- በእሱ ዙሪያ ብዙ ነገር ለመሥራት ዕቅድ አለኝ፡፡ ችግሩን በተመለከተ ከክልሉ ባለስልጣናትም ሆነ ከፌደራል መንግስት ጋር ለመነጋገር እያሰብኩ ነው፡፡ ቀደም ባለውና ስልጣን ላይ ባለው በነበረው ቡድን እኛ የተረሳን፤ በአናሳ ብሔረሰብ የምንገለፅ፣ ጫካ የምንኖር ተደርገን ነው እንታሰብ የነበረው፡፡ ኢህአዴግ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉልና አፋርን የመሰሉ ሕዝቦችን "አናሳ" ፣ "አጋር" በሚሉ ከስድብ በማይተናነሱ ቃላት ነበር ነበር ሲገልፃቸው የኖረው፡፡

ቤቱን ያልጠረገ ሰው ሌላ ሰው መጥቶ ሊጠርግለት አይችልም፡፡ ራሱን ያላፀዳ ሰው ሌላን ሰው ማፅዳት አይችልም፡፡ ሶማሌን ለምሳሌ ብንወስድ ሙስጠፋ ስልጣን ከያዘ በኋላ ክልሉ ምን ዓይነት ቅርፅ እንደያዘ እያየን ነው፡፡ ሶማሌን ያፀዳው ዐቢይ አይደለም፤ ሙስጠፋ ነው፡፡ በርግጥ መለስ ዜናዊና ኃ/ማርያም ደሳለኝ ስልጣን ላይ በነበሩበት ሰዓት የሶማሌ ክልል እንደዛ አልነበረም፡፡ አሁን ግን ሶማሌ ክብር አግኝቷል፡፡ ጥሩ መሪ በቦታው ላይ ከተቀመጠ ነገሮችን ማስተካከል እንደሚቻል ነው ከዚህ የምንረዳው፡፡

ክክልል ተሻግረን አጠቃላይ የኢትዮጵያን ገፅታ ብንመለከት፣ ኑሯችን እንደ ሀያኛው ክ/ዘመን አይደለም፡፡ እንደ አውሬ ነው የምንኖረው፡፡ ለራሳችን፣ ለሆዳችን ብቻ ነው የምንጨነቀው፡፡ "አማራ"፣ "ኦሮሞ" እያሉ በተወሰነ ቅጥር ውስጥ መሽከርከር ሆኗል ስራችን፡፡ ዜግነት ጠፍቶ በዘር ማሰብ ፋሽን ሆኗል፡፡ የሰውን ልጅ ክቡር ስብዕና ሁሉ ረስተናል፡፡ ከመቶ አመት በፊት የሚኖሩት አያቶቻችን ከእኛ የተሻሉ ነበሩ፡፡ ይህ የከፋ ፖለቲካ በተንሰራፈበት ሂደት ውስጥ ራሴን በፖለቲከኛ መክተት ለእኔ ከባድ ነው፡፡ የማየው ነገር ሁሉ ያሳዝነኛል፡፡

መሪ መሆን ለራስ መኖር ማለት ሳይሆን



የሕዝቦችን ሕይወት ማሻሻል ነው፡፡ አሁን ለምሳሌ ጋምቤላ ትምህርት የሌለበት፣ ንፁህ ውሃ የሌለበት በርካታ ቦታ አለ፤ የጋምቤላ ሕዝብ ሐብት እያለው ድሃ የሆነ ሕዝብ ነው፡፡ ያለውን ለም መሬት በትክክልና በአግባቡ እንድንጠቀም የሚያስችል መሪ፣ ሰውን በሰውነቱ ብቻ የሚያከብር መሪ ብናገኝ ኖሮ የጋምቤላ ሕዝብ እንዲህ በድህነት ቸነፈር አይመታም ነበር፡፡ አሁን ያሉት መሪዎች በድንጋይ ይውረዱ አይደለም የምለው፤ ሕዝቡ ራሱ በትክክል አስተዳዳሪዎቹን ይምረጥ ነው ሀሳቤ፡፡ ጋምቤላ የሚሰርቅ፣ የሚዘርፍ መሪ ሳይሆን፤ በትክክል የሚወክለውና ህዝብን የሚያገለግል መሪ ነው የምትፈልገው፡፡

ሌላው አራት ኪሎ፣ መስቀል አደባባይ፣ ቦሌና ብዙ የዋና ከተማዋ የተለያዩ ቦታዎች የሚታዩ የጎዳና ተዳዳሪዎች፣ ሴተኛ አዳሪዎችም እኮ የራሳችን ወገኖች ናቸው፤ ሕይወታቸውን መቀየር የሁላችንም ሓላፊነት ነው፡፡ ከእኔነት ስሜት ወጥተን በዚህ ደረጃ አገራዊ ችግሮችን መመልከት መቻል አለብን፡፡ እኔ በቅርበት ስለማውቅ የጋምቤላን ጉዳይ አነሳሁ እንጂ ሁሉም ቦታዎች ችግሮች አሉ፡፡

ሲንጋፖር በጣም ድሃ ሀገር ነበረች፤ ግን ትክክለኛና ጥሩ መሪ በማግኘቷ ዛሬ በከፍተኛ ሁኔታ ተለውጣለች፡፡ ኢትዮጵያውያን እስከ ዛሬ ድረስ የብሔር መሪ እንጂ ትክክለኛ የአገር መሪ አላገኘንም፡፡ ይሄ በጣም የሚያሳዝን ነው፡፡ መሪዎቻችን ከተወከሉበትና ከመጡበት ብሔር ፖለቲካ ርቀው ለኢትዮጵያ ነው ማሰብና መስራት ያለባቸው፡፡ አጋጣሚ ሆኖ የጋምቤላ ፖለቲካ ውስጥ ከገባሁ የምሰራው በዚህ መንገድ ነው፡፡

ከምንም በላይ ደግሞ የአንድ ብሔር የበላይነት በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ መቅረት አለበት፡፡ ከላይ እስከ ታች ያለውን ስልጣን ከአንድ ብሔር በተውጣጡ ሰዎች መያዝ ፈፅሞ መወገድ ይኖርበታል፡፡ ከዚህ በፊት እንደኢትዮጵያ አየር መንገድ ዓይነት ትልልቅ ተቋማት ከሓላፊ እስከ ተራ ሰራተኛ በአንድ ብሔር ተፅዕኖ ላይ እንዲወድቁ የተደረገበት አሰራር ነበር፡፡ አገር የሚቆመው በስራና በእውቀት እንጂ በብሔር ወይም በጎጠኝነት አይደለም፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲህ ዓይነት ነገር እየተለመደ ነው፡፡ ይሄ በፍጥነት መቀረፍ አለበት፡፡ በሁሉም የአገሪቱ ክልሎች የህግ የበላይነት ተግባራዊ መሆን ይኖርበታል፡፡ ጋምቤላም ከዚህን መሰሉ ችግሮቿ ፀድታ እንድትኖር ከተፈለገ ልክ እንደ ሶማሌ ደህና መሪ ያስፈልጋታል፡፡

**ግዮን፡- ወደፊት ኦባግን በምን እንጠብቀው?**

ኦባንግ፡- አሁን ላይ ርግጠኛ ሆኖ መናገር ይከብዳል፤ ሁሉንም ጊዜው ይናገራል ባይ ነኝ፡፡ ግን በምችለው መጠን ሕዝባችንን ማገልገል እፈልጋለሁ፡፡ ዛሬ በሽታ በሆነው የብሔር ፖለቲካ ውስጥ ግን ማለፍን አልፈልግም፡፡ ከዛ ውጭ ኢትዮጵያዊነትን ከሚያስቀድሙ ሁሉ ጋር ከመስራት ወደ ኋላ አልልም፡፡ በምንም መስፈርት አገር ይቀድማልና፡፡

**ግዮን፡- በስተመጨረሻ በአገራችን ባለው ፖለቲካ ላይ ከሚታዩት ችግሮች አኳን ምን መደረግ ይኖርበታል ትላለህ? ለመሪዎቻችንም ሆነ ለሕዝቡ የምታስተላልፈው መልዕክትስ ምንድን ነው?**

ኦባንግ፡- ከምንም በላይ "የእኔ ብሔር"፣ "የእኔ ወገን" የሚሉ ሰዎች እንደተሳሳቱ አስረግጬ መናገር እፈልጋለሁ፡፡ ማንም ሰው "የእኔ ዜጋ" ወይም "ኢትዮጵያዊ ወገኔ" ተጎዳ ነው ማለት ያለበት፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተበደለ ሰው የለም፡፡ "እኛ ተበድለናል" እየተባለ ይጮኻል፤ በዳዮቹስ ከየት ነው የመጡት? ከሌላ አገር ነው? በዳይም፣ ተበዳይም እኛው ነን፡፡ ሁላችንም እንደተበደልን ተማምኖ፣ ስላለፈ በደላችን እያወሩ ከመነቋቆር ይልቅ እንዴት ነው ያለፈው ቁስላችንን አክመን ወደ ፊት የምንሄደው? የሚለው ላይ ነው መነጋገርም መስራትም ያለብን፡፡

ሁሌም እንደምናገረው ሰው በእውነቱ የሚከበርበት ፣ የህግ የበላይነት ያለበት አገር እንድትኖረን መግባባት አለብን፡፡ ብሔርን ትተን አገርን እናስቀድም፡፡ አሁን ያለንበት የክልል አስተሳሰብ እንዲቀየርና አዋጪው የአንድነትን መንገድ እንድንከተል መንግስትም፣ ሕዝብም ጠንክረን መስራት አለብን፡፡ አሁን ከመጥፎ መንገድ ጫፍ ላይ ነን፡፡

የእዚህችን ሀገር ችግሮች ያመጣነው እኛው ነን፣ ለበሽታችንም ሙድኃኒት ማግኘት የምንችለው ራሳችን ነን፡፡ የዘር ፖለቲካ ያባላል፣ ያጋድላል፡፡ ያለፈው ዓመትና ዘንድሮ ብዙ ልዩነቶች አሉ፡፡ ብዙ ሰዎች ያኔ ጠ/ሚኒስትር ዐቢይን ደግፈዋል፡፡ አሁን ግን ስጋት ላይ ወድቀዋል፡፡ በተለያየ ቦታ ሕዝብ የአንድ ብሔር የበላይነትን አንፈልግም እያለ ነው፡፡ ሲያጋድለን ወደነበረው የ27 ዓመት ፖለቲካ የሚወስዱ ምልክቶች እየታዩ ነው፡፡ እነዚህ ስጋቶች በፍጥነት ካልተወገዱ ሁሌም ባለንበት ስንረግጥ ነው የምንኖረው፡፡

ችግሮቻችንን በትክክል ማየትና መፍታት ካልቻልን ምናልባትም የከፋ ችግር ውስጥ ነው የምንገባው፡፡ ምሁራኖቻችን በአንድ መንፈስ "ከምንም በላይ አገር ይቀድማል" በሚል በጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥተው መስራት አለባቸው፡፡ ሁላችንም ይህቺን አገር በሁለት እግሯ የማቆም ኃላፊነት አለብንና ይህን ዕውን ለማድረግ ጠንክረን እንስራ ነው የምለው፡፡

**ግዮን፡- እናመሰግናለን፡፡**

## በኢጂቶ የምትናጠው ...

*ከገጽ 3 የዞረ*

የሚመራ የጋሞ ዴሞክራሲያዊ ድርጅትና ሌላ አንድ ፓርቲ አራት ሆነው አንድ ላይ ደቡብ ብሎክ ብለው ህብረት ሲያቋቁሙ ይህን ብሎክ ለመምታት ተብሎ ነው በአፋጣኝ ያለምንም ጥናት ለፖለቲካ ተብሎ ደቡብ ክልል የተቋቋመው›› በማለት የክልሉን የአወቃቀር ሥርዓት ከነቀፉ በኂላ የክልል እንሁን ህዝባዊ ጥያቄ መሰረታዊ ምክንያት ያሏቸውን እንዲህ ገልፀዋቸዋል፡፡

‹‹…የሲዳማ አካባቢ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ያለበት ነው፡፡ መሬቶቹ የተበጣጠሱ ናቸው፡፡ ምርታማነቱ እጅግ የወረደ ነው፡፡ ሲዳማ የምርታማነት ችግር እየገጠመኝ ነው ብሎ ለደቡብ ክልል ሲያቀርብ ተቀባይነት አያገኝም፡፡ …ለትምህርት፣ ለግብርና እና በክልሉ ለሚገኙ ለሁሉም ህዝቦች አንድ ዓይነት በጀት ስለሚያዝ ሲዳማ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተጎዳ እንደሆነ ተረድቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አሁን ሀገሪቷ ውስጥ ካሉ ዘጠኝ ክልሎች ውስጥ አራት ክልሎች ብቻ ናቸው ሲዳማን የሚበልጡት፡፡ አምስቱን ክልሎች ሲዳማ ይበልጣል፡፡ ከህዝቡ ቁጥርና ጥያቄው ብዙ ዓመታትን የቆየ ከመሆኑ አንፃር፣ ካለው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አንፃር ሲዳማ ክልልነት ይገባዋል…›› ብለዋል የሲአን ሊቀመንበሩ አቶ ዱካሌ ላሚሶ፡፡

### ኢጄቶ እና መንግስት፤

በሲዳማ ብሔር ተወላጆች ዘንድ የላቀ ተቀባይነት አለው የሚባለው የሲአን ሊቀመንበር የጠቀሷቸው ችግሮችና የመብት ጥያቄዎች አሁን የዞኑን የክልልነት ጥያቄ እየመራ ነው በሚባለው የወጣቶቹ ኢጄቶ በግልፅ ሲስተጋባ ይደመጣል፡፡

የብሔሩ ተወላጆች የመብት ጥያቄ የሆነው የክልል እንሁን አጀንዳ በተነሳባቸው መድረኮችና አጋጣሚዎች በምክንያትነት የሚቀርቡ መሠረታዊ ነጥቦች የሲአን ሊቀመንበሩ ካነሷቸው ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡ በዞኑ ህዝብ ጥያቄ ‹‹ አጣብቂኝ ውስጥ ገብተዋል›› የሚባሉት የደቡብ ክልል አስተዳደርና ማዕከላዊው መንግስትም ለጥያቄው አፋጣኝ ምላሽ ለመስጠት ሀገራዊ ሁኔታዎች ምቹ አለመሆናቸውን በምክንያትነት ቢያነሱም በሲዳማ ተወላጆች የመብት ጥያቄ ተገቢነት ላይ ግን የጋራ ዕምነት ነው ያላቸው፡፡

የሲዳማ ወጣቶቹ ኢጄቶ 11/11/11 የሲዳማ ነፃነት ቀን መሆኑንና ህዝቡ በራሱ የሚያረጋግጥበት ዕለት መሆኑን ይፋ ካደረገ በኂላ የክልሉን መንግሥት የሚመራው የደቡብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ደኢህዴን) በጉዳዩ ላይ ለቀናት ውይይት ሲያደርግበት ቆይቷል፡፡ ለ3 ቀናት ተብሎ የተጀመረው ስብሰባ ወደ 5 ቀናት ተራዝሞም በጉዳዩ ላይ የጋራ አቋም ለመያዝ ባለመቻሉ ወደ 10 ቀናት የፈጀው የደኢህዴን ስብሰባ ሐምሌ 8 ቀን 2011 ዓ.ም አመሻሽ ላይ ሲጠናቀቅ ባወጣው መግለጫ ‹‹…. በክልል የመደራጀት ጥያቄን በጥናት ላይ ተመስርቶ ምላሽ ማግኘት እንዳለበት ድርጅቱ በአስረኛ ድርጅታዊ ጉባኤው በወሰደው አቋም መሰረት በዝርዝር ህዝቡን ያሳተፈ ጥናት ሲያደርግ ቆይቷል›› በማለት አስታውቆ የህዝቡን የጋራ ዘላቂ ጥቅም የሚያረጋጠውን አማራጭ በመውሰድ የክልል አደረጃጀት ጥያቄዎች በሚመለሱበት አግባብ ላይ አቋም መውሰዱን ገልጧል፡፡ ከመግለጫው ጥቅል ሀሳብ ለመረዳት እንደሚቻለው ደኢህዴን የክልል እንሁን ጥያቄዎች ህገ መንግሥታዊና የዜጎች መብት መሆኑን ቢያምንም ጥያቄውን በአፋጣኝ ለመመለስ ግን አሁን ያሉ ሀገራዊ ሁኔታዎች ምቹ አይደሉም፡፡

በተመሳሳይ ጠ/ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድም በቅርቡ በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የ2011 በጀት ዓመት የአፈፃፀም ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት ከም/ቤቱ አባላት በደቡብ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ህዝቦች ክልል እየተነሱ ያሉ የክልል እንሁን ጥያቄዎች በሚመለከት ለቀረቡ ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽ ጥያቄዎቹ ህገ መንግስታዊ መሆናቸውን ነገር ግን ጥያቄውን ከህግ ውጪ ለማስፈፀም የሚደረግ እንቅስቃሴ ተገቢ እንዳልሆነ አመልክተዋል፡፡

“ክልሉን እያስተዳደረ ያለው ደኢህዴን ጥያቄውን ተቀብሎ በህግ እየመረመረ ነው፡፡ …ደኢህዴን የመጨረሻ ውጤቱን እስከሚያሳውቅና ምርጫ ቦርድ ዝግጅቱን እስከሚያጠናቅቅ በደቡብ ክልል ውስጥ የመሆን ጥያቄ ያቀረቡ ህዝቦች በትዕግስት ሊጠብቁ ይገባል” ያሉት ጠ/ሚኒስትሩ “በህጋዊ መንገድ የቀረበውን ጥያቄ ከህጋዊ መንገድ ውጪ ለማስፈጸም የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን መንግሥት አይታገሣቸውንም›› ሲሉ የመንግሥትን አቋም በግልፅ አስቀምጠዋል፡፡

### ከሰላማዊ ጥያቄ ወደ ግጭት፤

በክልሉ እና በማዕከላዊ መንግሥቱ በኩል የተያዙት አቋሞች ምናልባትም ለጥያቄዎቹ በጊዜያዊነት የተሰጡ ምላሾች እነዚህ ቢሆኑም በተለይ ኢጄቶ እና ቁጥራቸው አስር የሚደርሱ በሲዳሞ ዞን የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲች ግን ለጥያቄያቸው የመንግሥትን አዎንታዊ ምላሽ ከመጠበቅ ይልቅ ህዝቡ በራሱ ክልሉን የመመስረት መብቱን እንደሚጠቀም አስታውቀዋል፡፡ ይህ ሁኔታም መብቴ ነው በሚለው ህዝብና ህጋዊውን ሂደት መከተል አለበት በሚለው የመንግሥት አካል መካከል ፍጥጫ እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡ በዞኑ በተለይም በክልሉ ርዕሰ ከተማ ሐዋሳ ደም መፋሰስን የሚያስከትል ግጭት ሀሙስ እለት ተከስቷል፡፡

የክልሉ ገዢ ፓርቲ ስብሰባውን አጠናቆ መግለጫ በሰጠበት ዕለት (ሐምሌ 8) ከማለዳ ጀምሮ እስከ ምሳ ሰዓት የዘለቀ ሰልፍ በሐዋሳ ከተማ ተካሂዷል፡፡ በሁሉም የከተማዋ አቅጣጫ በርካታ ቁጥር ያላቸው የሲዳማ ተወላጆች በእግር፣ በሞተር ሳይክል፣ በባጃጅ እና በልዩ ልዩ ተሽከርካሪዎች (የመንግሥት ታርጋ ባላቸው መኪኖች ጭምር) ሆነው በአደባባይ ያሰሙት የደስታ መግለጫ ሰልፍ “እንኳን ደስ ያለን ሲዳማ ክልል መሆኑ ተረጋጠ” የሚል መንፈስ ያለው ሲሆን ከሰልፉ በኂላ ጦር መሳሪያ የወደሩ የክልሉ ልዩ ሃይል አባላትና አልፎ አልፎ ባለቀይ ቆቡ የመከላከያ ሀይል በከተማዋ ጎዳናዎች መታየታቸው ሂደቶቹ አስፈሪ መልክ እንዲኖራቸው አድርጓል፡፡

ኢጄቶ በ11/11/11 የሲዳማ ነፃነት ቀን ብሎ ያወጀውንና መንግሥት ህገወጥ ያለውን እንቅስቃሴ ህዝቡ በራሱ እውን ያደርገዋል እያሉ በስፋት እየሰበኩ ያሉ የዞኑ የፖለቲካ ሀይሎች የነገሮችን አቅጣጫ ተገንዝበው ህዝቡን ከማረጋጋትና መንግሥትም ለሀይል ዕርምጃ እንዳይቸኩል ከማሳሰብ ይልቅ የእልሁን መንገድ መርጠው መታየታቸው በርካታ ታዛቢዎችን ግራ አጋብቷል፡፡ አንዳንዶችም በቅርቡ የትግራይ ገዢ ፓርቲ ሕወሓት ባወጣው ድርጅታዊ የአቋም መግለጫ የሲዳማን የክልልነት ጥያቄ በአዎንታዊ ጎኑ ጠቅሶ መንግሥት በአፋጣኝ ምላሽ እንዲሰጥበት መጠየቁን መነሻ በማድረግ ከዚህ የእልህ ጉዞ ኂላ “የትግራይ በጥባጮች” ሳይኖሩበት አይቀሩም የሚል ሀሳብ ሲሰነዝሩ ይደመጣሉ፡፡ ▶

**. . .በተለይ በ11/11/11 ሀሙስ ከማለዳው ጀምሮ በሀዋሳና አካባቢው የተከሰተው ግጭት ብዙ ጉዳት ማስከተሉ እየተነገረ ነው፡፡ ይበልጡንም በሀዋሳ አቶቴ እና ወ/አማኑኤል አደባባይ በተባሉት ቦታዎች ሰልፍ በወጡ የሲዳማ ተወለጆችና በጸጥታ ሀይሎች መካከል በተፈጠረ ግጭት ጉዳት መድረሱ እየተነገረ ነው . . .**

በሰላማዊ መንገድ ሀገር ቤት ገብተው ህጋዊና ሰላማዊ የፖለቲካ ትግል እንዲያደርጉ በአዲሱ የለውጥ መንግሥት በሩ ከተከፈተላቸው የፖለቲካ ድርቶች መካከል አንዱ የሆነውና "በጥባጮቹ ህወሓቶች ከጀርባ ሆነው ይዘውሩታል" በሚል የሚታማው የኦሮሞ ነፃነት ግንባር/ኦነግ/ እታገልለታለሁ ከሚለው ክልልና ህዝብ ውጪ በሆነ አጀንዳ ውስጥ ገብቶ ለሲዳማ የክልልነት ህዝባዊ ጥያቄ ድጋፍ የሰጠ የሚመስል መግለጫ ማውጣቱም በበርካታ የሀገሪቱ የፖለቲካ ልሂቃንና ዜጎች ዘንድ ሰፊ ጥርጣሬን የፈጠረ ሆኗል፡፡

‹‹የሲዳማ ሕዝብ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብቱን ተጠቅሞ የሚስደውን ማንኛውንም ውሳኔ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር ያከብራል›› ያለው የኦነግ መግለጫ የሲዳማ ብሔር ተወላጆች የክልልነት ጥያቄ ብዙ ዋጋ የተከፈለበትና ህገ መንግሥቱን የተከተለ በመሆኑ ይህን ጥያቄ ለማስቆም በመንግሥት በኩል የሚወሰድ እርምጃ እንዳይኖር በፅኑ እንደሚያሳስብ አስታውቋል፡፡ ይህ የኦነግ አቋምና ቀደም ሲል የተጠቀሰው የህወሓት መግለጫ ተመሣሣይ እንደምታ ያላቸው መሆኑን የታዘቡ ወገኖች እየተሰራ ያለው ስራ የተቀናጀና የተጠና በመሆኑ ውጤቱ ብዙ ዋጋ እንዳያስከፍል ያላቸውን ስጋት ገልፀዋል፡፡

በሌላ በኩል ይህን የክልል እንሁን ጥያቄ በህገ መንግስቱ መሰረት ምላሽ እንዲሰጥበት መብት የተሰጠው ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ባለፈው ረቡዕ ጉዳዩን አስመልክቶ ባወጣው መግለጫ ለክልል እንሁን ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት ሳይችል የቆየበትን ምክንያት ገልፆ ጥያቄውን የሚያቀርቡ አካላት እስከ ሐምሌ 19 ቀን 2011 ዓ.ም ድረስ የተደራጀና ህጋዊ አካሄድን የተከተለ ጥያቄያቸውን ለቦርዱ እንዲያቀር አሳስቧል፡፡

‹‹ህዝበ ውሳኔ የሚከናወነው የህዝብ ፍላጎትና ውሳኔ ህጋዊ እና ነፃ በሆነ አግባብ መስጠቱን ለማጋገጥ ነው ›› የሚለው የቦርዱ መግለጫ የሲዳማን ህዝብ የክልልነት ጥያቄ በህዝበ ውሳኔ ለማፅደቅ ምን ምን ዓይነት ቅድመ ሁኔታዎች መሟላት እንዳለባቸው በዝርዝር ገልፆ ቦርዱ ይህን በህገ መንግሥቱና በምርጫ አዋጁ የተሰጠውን ሀላፊነት ከአለም አቀፍ የምርጫ መሠረታዊ መርሆዎች ጋር በማጣመር ሀላፊነቱን ለመወጣት ከፍተኛ ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ አስታውቋል፡፡

## ሕገ-መንግስቱ ምን ይላል?

በኢፌድሪ ሕገ መንግስት አንቀፅ 39 የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መብት በሚል የተቀመጠው ዝርዝር ድንጋጌ "1.ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከ መገንጠል ያለው መብቱ በማናቸውም መልኩ ያለገደብ የተጠበቀ ነው፡፡ 2.ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ ሕዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመፃፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግ እና ባህሉን የመግለፅ፣ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ መብት አለው፡፡ 3.ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ ሕዝብ ራሱን የማስተዳደር ሙሉ መብት አለው፡፡ ይህ መብት ብሔሩ፣ ብሔረሰቡ፣ ሕዝቡ በሰፈረበት መልክዓ ምድር ራሱን የሚያስተዳርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋም እንዲሁም በክልልና በፌደራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብትን ያጠቃልላል›› በሚል በግልፅ የተቀመጠ ነው፡፡ ዛሬ ሲዳማም ሆነ ሌላው ብሔረሰብ ክልል የመሆን መብት እንዳለው አምኖ ይህንኑ ተግባራዊ ለማድረግ እየተንቀሳቀሰ የሚገኘውም ህገ መንግስታዊ መብቱ በመሆኑ ነው፡፡ የሲዳማው ኢጄቶ የሲዳማ ህዝብ መብቱን በራሱ የሚያረጋግጥብን "የነፃነት ቀን" ያወጀውም በህገ መንግስቱ የተቀመጠ መብት ስላለው እንደሆነ ገልፆል፡፡

ይሁንና ማዕከላዊው መንግሥትና የክልሉ አስተዳደር መብትን ተግባራዊ ማድረግ የሚቻለው ሕጋዊ የአፈፃፀም ሂደቶችን ጠብቆ እንጂ እንዲሁ ተነስቶ መብቴን አስከብራለሁ ማለት እንደማይቻል ሲገልፁ ቆይተዋል፡፡ የሲዳማ ህዝብ ይህን የክልልነት ጥያቄ በተደራጀና ሁሉንም የብሔሩን ተወላጆች ባሳተፈና ፍላጎታቸውን ባማከለ መልኩ በህጋዊና ሰላማዊ መንገድ መቅረብ ያለበት እንደሆነና ጥያቄውን ተቀብሎ ዝርዝር አፈፃፀሙን የመምራት ስልጣን ያለው ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ብቻ መሆኑ በመንግሥት በኩል ተገልጾአል፡፡ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ እንደ አዲስ እየተዋቀረና የአፈፃፀም ብቃቱን እያደራጀ በመሆኑ ሲዳማዎች ለጥያቄያቸው ህጋዊ ምላሽ ለማግኘት ጥቂት መታገስ እንደሚኖርባቸውም ሲያስታውቅ ቆይቷል፡፡ በኢጄቶ የሚመራው የሲዳማ ብሔሮች እንቅስቃሴ ግን ለዚህ የመንግሥት መግለጫና ማሳሰቢያ ቦታ የሰጠ አይመስልም፡፡ እንደውም በተቃራኒው የሐዋሳ ከተማንና የዞኑን አንዳንድ ከተሞች በፖስተሮችና ነፃነትን በሚያበስሩ ባነሮች የማጥለቅለቅ እቅድ ነበረው፡፡ በተለይም ካለፈው ረቡዕ አመሻሽ ጀምሮ በሐዋሳና አከባቢዋ የታየው ሲዳማ ክልል መሆኗን በራስ ፈቃድ የማረጋገጥ ማሳያ የሆነው በፖስተር እና ባነር የማጥለቅለቅ እንቅስቃሴ በዞኑ በሚኖሩ የሌላ ብሔር ተወላጆች ላይ የደህንነት ስጋት እንዲፈጠር አድርጎ አካባቢውን ለቀው እንዲወጡ አስገድዷቸዋል፡፡

## ኢጄቶና የፀጥታ ሀይሉ፤

በዩኔስኮ የማይዳሰሱ ቅርስ መዝገቦች ውስጥ "የአለም ቅርስ" ሆኖ የተመዘገበው የሲዳማ ብሔር ዘመን መለወጫ በዓል (ጨምበላላ) በየዓመቱ በድምቀት በሚከበርበት ጉዱማሌ በተባለው ቦታ ማክሰኞ ዕለት ኢጄቶ እና ደጋፊዎቹ ህዝባዊ ስብሰባ ያካሄዱ ሲሆን በስብሰባው ላይ የሲዳማ ሐርነት ቀን ብለው ያስቀመጡትን 11/11/11 መርሃ ግብር እንደሚቀጥሉበትና ከመንግሥትና ከክልሉ ም/ቤት የሚሰጡ መግለጫዎችን እንደማይቀበሉ የጋራ አቋም አንፀባርቀዋል፡፡ የዕለቱን ስብሰባ ሲያጠናቅቁም የሲዳማ አባቶች ምረቃ እና ቡራኬ እንዲያቀርቡ ተደርጎ ያዘጋጇቸው ሶስት ትላልቅ ነፃነትን የሚያውጁ ባነሮች ተመርቀው በተመረጠላቸው ባታ እንዲሰቀሉ ወደማድረግ እንቅስቃሴ ተሻግረው ነበር፡፡ ይሁንና ገና የመጀመሪያውን ባነር በተለምዶ ጥቁር ውሃ በሚባለው የሐዋሳ ከተማ መግቢያ ድንበር ላይ እንደሰቀሉ የፌዴራል ፖሊስና የመከላከያ ፀጥታ ሃይሎች በቦታው ደርሰው ሰልፉን በመበተን ባነሩ ከተሰቀለበት እንዲወርድ አድርገዋል፡፡

"ወደ ሲዳማ ክልላዊ መንግስት እንኳን ደህና መጡ" የሚል ፅሁፍ በጉልህ የሚነበብባቸው ፖስተሮች እያንዳንዳቸው በግምት እስከ 30 ሜትር ርዝማኔ ያላቸው እንደነበሩ የገለፀው የሐዋሳ ምንጫችን የተቀሩት ፖስተሮች በሐዋሳ ከተማ ከንቲባ ፅ/ቤት እና በሲዳማ ዞን አስተዳደር ጽ/ቤት ህንፃዎች ላይ እንዲቀሰቀሉ ዕቅድ ተይዞላቸው እንደነበር አስረድቷል፡፡

በተያያዘ የሲዳማ የክልልነት ጥያቄን እና ይህን ተከትሎ በክልሉ የተፈጠረውን ውጥረት በሚመለከት የዞኑ ዋና አስተዳዳሪ ረቡዕ ዕለት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ "ለሲዳማ የክልልነት ጥያቄ የምርጫ ቦርድን ስራ በትዕግስት መጠባበቅ ይገባል" ብለዋል፡፡

የሲዳማ ዞን ዋና አስተዳዳሪው አቶ ቃሬ ጫዊቻ በዚሁ ጋዜጣዊ መግለጫቸው የክልልነት ጥያቄው በህገ መንግስቱ መሰረት ምላሽ እንዲያገኝ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ስራ በመጀመሩ መላው የሲዳማ ብሔር ተወላጅ በትዕግስት እንዲጠባበቅ ጥሪ አቅርበዋል፡፡ የሲዳማ ዞን አስተዳደር ከክልሉ መንግሥትና ከዴኢህዴን ጋር በመሆን በጥያቄው ዙሪያ በጋራ እየሰሩ እንደሚኙና ምርጫ ቦርድ በአምስት ወራት ውስጥ ህዝበ ውሳኔ ለማድረግ እየሠራ መሆኑን መግለፁን የጠቀሱት ዋና አስተዳዳሪው መላው የሲዳማ ተወላጆችና ወጣቶች ይህን ሁኔታ ተረድተው በትዕግሥት እንዲጠብቁ አሳስበዋል፡፡

ይሁንና የአካባቢው ምንጮች እንደገለፁት በክልሉ ርዕሰ ከተማ ሀዋሳና በአብዛኛው የዞኑ ከተሞች ሲዳማ ክልል መሆኗን የሚያረጋግጡ እንቅስቃሴዎች ከመታየታቸው ባሻገር ህዝቡም ደስታውን በተለያየ መንገድ እየገለፀ ነው፡፡ በዚህም ግጭት ተከስቷል፡፡ በሌሎች ብሔሮች ተወላጆች ላይ የተፈጠረውን የደህንነት ሥጋት ለማረጋጋት የተወሰደው እርምጃ በተለይ በሃዋሳ ግጭት አስከትሏል፡፡ ይህንኑ ተከትሎም ብዙ ዜጎች ለከፍተኛ እንግልት ተዳርገዋል፡፡ የትራንስፖርት ዋጋም ከእጥፍ በላይ መጨመሩ ተነግሯል፡፡ ሀሙስ ዕለት የትኛውም አይነት የትራንስፖርት እንቅስቃሴ ተቋርጧል፡፡ በዞኑ ከተሞች በተለይም በሐዋሳና አዋሳኝ አካባቢዎች ያለው እንቅስቃሴ ማህበራዊ ቀውስን የማስከተል አቅም እንዳለውም አስተያየት እየተሰጠበት ነው፡፡

በተለይ በ11/11/11 ሀሙስ ከማለዳው ጀምሮ በሀዋሳና አካባቢው የተከሰተው ግጭት ብዙ ጉዳት ማስከተሉ እየተነገረ ነው፡፡ ይበልጡንም በሀዋሳ አቶቴ፣ ጉዱማሌ እና ወ/አማኑኤል አደባባይ በተባሉት ቦታዎች ሰልፍ በወጡ የሲዳማ ተወላጆችና በጸጥታ ሀይሎች መካከል በተፈጠረ ግጭት ጉዳት መድረሱ እየተነገረ ነው፡፡ በአካባቢዎቹ ከፍተኛ የተኩስ ድምጽ የተሰማ ሲሆን እስከ ኬንያ የሚያደርሰው የዲላ መንገድም በተቃዋሚዎች መዘጋቱ ተነግሯል፡፡ የምርጫ ቦርድን ውሳኔ መጠበቅ የተሻለ ስለመሆኑ የተናገሩት የዞኑ አስተዳዳሪን ቤት የማቃጠል ሙከራ ስለመደረጉም መረጃዎች እየወጡ ነው፡፡

# ማዮን መጽሔት

## ኢትዮ ሀበሻ የሕትመትና ማስታወቂያ ኃ/የተ/የግ/ማኅበር

## ክፍት የስራ ማስታወቂያ

**ኤዲተር፣-**
**አዘጋጅ፣-**
**ከፍተኛ ሪፖርተር**

በመጽሔትና ጋዜጣ ላይ የረጅም ጊዜ የስራ ልምድ ያለው/ያላት
በፕሬስ ውስጥ ተሳትፎ ያደረጉ ቢሆኑ ይመረጣል፡፡

**የማስታወቂያ ባለሙያ፣-** በተለያዩ ጋዜጣ ፣ መጽሔት ፣ የማስታወቂያ ድርጅት ውስጥ በማስታወቂያ ሠራተኝነት የሰራ/የሰራች

ደሞዝ በስምምነት የስራ ልምድ በስራ ሰዓት ማስገባት ይቻላል

አድራሻ፣- አራት ኪሎ ግንፍሌ ድልድይ አጠገብ
አምባቸው ሕንፃ 2ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 207

+251 912 165606
+251 118 122333